አዲስ ዘመን
እኀድ
እሁድ
84ኛ ዓመት ቁጥር 082 ኅዳር 22 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# “ብልፅግና ፓርቲ በአምስት ዓመታት አስደማሚ ሁለንተናዊ ስኬቶችን አስመዝግቧል”

*- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) የብልፅግና ፓርቲ ፕሬዚዳንት*

**ጌትነት ምህረቴ**

አዲስ አበባ፡- ብልፅግና ፓርቲ ባለፉት አምስት ዓመታት በሁሉም ዘርፎች አስደማሚ ሁለንተናዊ ስኬቶችን አስመዝግቧል ሲሉ የብልፅግና ፓርቲ ፕሬዚዳንትና የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ገለጹ፡፡

የብልፅግና ፓርቲ ፕሬዚዳንት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የብልፅግና ፓርቲ 5ኛ ዓመት ምስረታ በዓል ሀገራዊ ማጠቃለያ መርሐ ግብር በዓድዋ መታሰቢያ ሙዚየም ትናንት ሲካሄድ እንዳሉት፤ ብልፅግና ፓርቲ ባለፉት አምስት ዓመታት ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ በመተግበር፣ በግብርና፣ በኢንዱስትሪ፣ በፍትህና ጸጥታ ተቋማት፣ በዲፕሎማሲና በኢንዱስትሪ ሪፎርሞች ካመጣቸው ስኬቶች ጎን ለጎን በበጋ ስንዴ፣ በሌማት ትሩፋት፣ በኮሪደር ልማት፣ በአረንጓዴ አሻራ፣ በጽዱ ኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ አስደማሚ ስኬቶችን አስመዝግቧል፡፡

ባለፉት አምስት ዓመታት የኢትዮጵያን የብልፅግና ዕጣ ፈንታ የሚወስኑ ፈርጀ ብዙ ሥራዎች ተተግብረው የሚታይ ውጤትና ፍሬ ማምጣት ጀምረዋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ፓርቲው ኢትዮጵያን የላቀ ከፍታ ላይ ለማድረስ ሙሉ ዕይታ ይዞ በሁሉም ዘርፎች በርካታ ስኬቶችን ያስመዘገበ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ብልፅግና እንደ ማንኛውም የፓርቲ ስም ሳይሆን ብልፅግና የልብ መሻታችንን ለሕዝባችን የምንገልጽበት ስያሜ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ይህ ስያሜ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ በድህነት አረንቋ ለተዘፈቁ ሀገራት ስም ሳይሆን የኢትዮጵያውያን ሁሉ የወል እውነት ነው ብለዋል፡፡ ምክንያቱም ከዚህ ችግር መውጣት የማይሻ ኢትዮጵያዊ የለም ነው ያሉት፡፡

ብልፅግና ፓርቲ ህልሙንና ራዕዩን ሙሉ ለሙሉ ማሳካት ሲችል

“ ብልፅግና ፓርቲ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ማዕከሉ የተደራጁ ወንጀሎችን በመመርመር ለፍትህ ሥርዓቱ አጋዥ መረጃዎች ይሰጣል

*- ለጎረቤት ሀገራት አገልግሎት የመስጠት አቅም እንዳለውም ተጠቆመ*

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የፎረንሲክ ምርመራ ማዕከል እንደሀገር ሊፈጸሙ የሚችሉ የተለያዩ የተደራጁ ወንጀሎችን መመርመርና ለፍትህ ሥርዓቱ አጋዥ የሆኑ መረጃዎችን የመስጠት አቅም እንዳለው የፌዴራል ፖሊስ አስታወቀ። ማዕከሉ ለጎረቤት ሀገራት አገልግሎት የመስጠት አቅም እንዳለውም ተገልጿል፡፡

የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ምክትል ኮሚሽነር ጀነራል መስፍን አበበ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የፎረንሲክ ምርመራ ማዕከሉ በቀጣዩ ዘመን እንደሀገር ሊፈጸሙ የሚችሉ የተለያዩ የተደራጁ ወንጀሎችን መመርመርና ለፍትህ ሥርዓቱ


ምክትል ኮሚሽነር ጀነራል መስፍን አበበ

አጋዥ የሆኑ መረጃዎችን የመስጠት አቅም ያለው ነው፡፡

የፎረንሲክ ምርመራና የምርምር ልህቀት ማዕከሉ የፎረንሲክ አቅምን ሊያሳድጉ የሚችሉ ዘመኑን የዋጁ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም በሚያስችል መልኩ ተደራጅቷል ያሉት ጀነራል መስፍን፤ በዘመኑ በሚስተዋሉ የወንጀል አይነቶች ላይ ምርመራዎችን ማካሄድ የሚያስችል የቴክኖሎጂ ግብዓቶች ተሟልተውለታል ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ ሕገ-ወጥ የአደንዛዥ እጽ ዝውውር ወንጀልን መከላከል የሚያስችል ጠንካራ የምርመራ ማዕከል መሆኑን ጠቅሰው፤ በማዕከሉ ወደ ውጭ ተልኮ ሲከናወን የነበረውን የዘረመል (ዲኤንኤ) ምርመራ በሀገር ውስጥ መስጠት እንደሚያስችል ገልጸዋል፡፡

ማዕከሉ ለክልልና ለፌዴራል ብቻ ሳይሆን በአካባቢው ለሚገኙ የሌሎች ሀገራትም ጭምር አገልግሎት መስጠት ያስችላልም ብለዋል፤ ጎረቤት ሀገራትን ጨምሮ የአፍሪካ ሀገራት

ማዕከሉ የተደራጁ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል













# ትክክለኛውን የአትሌቲክስ መሪ ለማግኘት ከማን ምን ይጠበቃል?

**ብርሃን ፈይሳ**

**ዜና ትንታኔ**

ስፖርት ወዳዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ አትሌቲክስ እንደ ዓይኑ ብሌን የሚሳሳለት ስፖርት ነው፡፡ አትሌቲክስ የኢትዮጵያን መልካም ገጽታ

ትክክለኛውን የአትሌቲክስ ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል



ዜና



# ‹‹ አምቦ አሁን የሰላምና የልማት ማዕከል ሆናለች ››

- አቶ ሀጫሉ ገመቹ
የአምቦ ከተማ ከንቲባ

**ኢያሱ መሰለ**

አዲስ አበባ፡- በትግል ማዕከልነት የምትታወቀው አምቦ አሁን የሰላምና የልማት ማዕከል መሆኗን የአምቦ ከተማ ከንቲባ አቶ ሀጫሉ ገመቹ አስታወቁ፡፡ በኦሮሚያ ክልል ደረጃ የሚከበረው 19ኛው የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በአምቦ ከተማ ዛሬ በድምቀት እየተከበረ ነው።

የአምቦ ከተማ ከንቲባ አቶ ሀጫሉ ገመቹ በዓሉን አስመልክቶ በተዘጋጀው የባዛርና ኤግዚቢሽን መክፈቻ መርሃ-ግብር ላይ ባደረጉት ንግግር ፤ አምቦ ከተማ ከትግል ማእከልነት ወደ ልማትና ሰላም ማእከልነት እየተሸጋገረች ነው፤ ከተማዋ አስተማማኝ ሰላምና ጸጥታ ስላላት በክልል ደረጃ የሚከበረውን 19ኛውን የብሔር ብሔረሰቦች ቀን እንድታስተናግድ መመረጧን አስታውቀዋል፡፡

የምንገኘው በብዙ ፈተና ተከበን ነው ያሉት ከንቲባው፤ በዚህም ምክንያት ጆሯችን ብዙ ያልተረጋገጡ ነገሮችን ይሰማል፡፡ ከርቀት ሆነው አምቦና አካባቢውን የግጭትና የብጥብጥ ማዕከል አድርገው የሚመለከቱ አሉ፡፡ እውነታው ግን አምቦ ከተማም ትሁን መላው ምዕራብ ሸዋ ዞን የግጭት ሳይሆኑ የልማትና የሰላም ማዕከል ናቸው ብለዋል።

በክልል ደረጃ የሚከበረው የብሄር ብሄረሰቦች ቀን በአምቦ ከተማ የሚከበር መሆኑም አካባቢው ሰላም እንደሆነ ለዓለም ምስክርነት የሚሰጥ እንደሆነ ያመለከቱት ከንቲባው፤ ምእራብ ሸዋና አምቦ ከተማ በተረጋጋ ሰላም ውስጥ እንጂ በጦርነት ውስጥ እንዳልሆኑ የሚያሳይ ነው ብለዋል፡፡

ከውጭና ከውስጥ የገጠመንን ፈተና ሁሉ ተቋቁመን ልትፈርስ ጫፍ ላይ የደረሰችን ሀገር መታደግ ችለናል። ለዚህም የአዳዲስ አመራሮች መምጣትና የብልጽግና ፓርቲ መመስረት አስተዋጽኦ ከፍያለ እንደነበር ገልጸዋል። የክልሉ አመራሮች የኦሮሞ ሕዝብን አሳታፊ ያደረገ ፍኖተ ካርታ በማስቀመጥና ታግለው በማታገላቸው ትልቅ ለውጥ መመዝገቡን ጠቁመዋል፡፡

ኢትዮጵያ የተለያዩ ብሔረሰቦችን ሃይማኖቶችንና ቋንቋዎችን የያዘች ትልቅ ሀገር ነች ያሉት አቶ ሀጫሉ፤ እነዚህን ልዩነቶች አቻችላ ጠላቶቿን በጋራ ክንድ በመመከት ህልውናዋን አስጠብቃ ኖራለች፡፡ አባቶቻችን በዚህ መልክ አስከብረው ያቆይዋትን ሀገር እኛም ጠብቀን ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ እየሠራን ነው ብለዋል፡፡ ትናንታችንን በትውስታ፤ ዛሬያችንን በሥራ ማሳለፍ ይኖርብናል ነው ያሉት፡፡

ዓመት በዓሉን በማስመልከትም በዞኑ የተለያዩ አካባቢዎች የልማት ሥራዎች መጎብኘታቸውን፤ የደም ልገሳና የጽዳት ሥራዎች መከናወናቸውን ፤ እስከ በዓሉ እለት ድረስ የሚቆይ ባዛርና ኤግዚቢሽን መከፈቱንም ጠቅሰዋል፡፡

ከተለያዩ የክልሉ ዞኖች የመጡ የባዛሩ ተሳታፊዎችም የንግድ ልውውጥ ከማድረግና ምርቶቻቸውን ከማስተዋወቅ ባሻገር የአምቦን የሰላምና የልማት ገጽታ የሚያስተዋውቁ አምባሳደሮች እንደሚሆኑ ገልጸዋል፡፡ የአምቦ ከተማ ነዋሪዎችም የእንግዶቻቸውን ደህንነት ጠብቀውና በክብር አስተናግደው እንዲሸኟቸው ተስፋ አለኝ ብለዋል፡፡

# አበረታች የሆነው የጤና መድህን ተደራሽነት

**ነፃነት አለሙ**

በአሁኑ ወቅት የጤና መድህን ተጠቃሚው ቁጥር ከ53 ሚሊዮን በላይ መድረሱን ከኢትዮጵያ ጤና መድህን አገልግሎት ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡ ከአስር ዓመት በላይ ያስቆጠረውን ይህን የጤና መድህን አገልግሎት ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ ለማድረግ የተለያዩ ስራዎች እየተሰሩ እንዳለም መረጃው ያሳያል፡፡ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች አገልግሎቱን ለማዳረስም በርካታ ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ ከዚህ አኳያም በክልሎች ያለው የጤና መድህን አገልግሎት ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለማንሳት ተሞክሯል፡፡

በሀረሪ ክልል ጤና ቢሮ የህክምና አሰጣጥ ስራ ሂደት ኃላፊ የሆኑት ዶክተር ኢማን ዘይዳን እንደሚሉት፤ በክልሉ የጤና መድህን አገልግሎት መተግበር የጀመረው ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ነው፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜም የተሻለ አፈፃፀም እያሳየ መምጣቱን የገለፁት ኃላፊዋ፤ በ2016 ዓ.ም ክልሉ ላይ ባሉት ዘጠኙም ወረዳዎች መተግበር ተችሏል ይላሉ፡፡ 46ሺ 196 አባዎራዎችንም አባል ማድረግ እንደተቻለ ይገልፃሉ፡፡

በዘጠኙም ወረዳዎች አንዳንድ መድኃኒት ቤቶችን በመክፈት መድኃኒቶችን በአቅራቢያቸው እንዲያገኙ ለማድረግና ቅሬታዎችን ለመፍታት የተሄደበት መንገድ እንደነበር አንስተው፤ ጥሩ አፈፃፀም እንደነበረ ጠቁመዋል። አቅም የሌላቸውን 7ሺ 478 የህብረተሰብ ክፍሎች ከየወረዳው በመለየት በጊዜውና በወቅቱ ወደ ክልሉ ፋይናንስ ቋት በማስገባት ያለምንም እክል አገልግሎቱን እንዲያገኙ መደረጉንም ያስረዳሉ፡፡

የጤና መድህን ዋና አላማው ከመታመም አስቀድሞ በመክፈል እርስ በእርስ መረዳዳትን ማዳበር ነው ያሉት ኃላፊዋ፤ በክልሉ ያሉ ባለሀብቶችና የግሉ ዘርፍ በየዓመቱ የተለያየ አስተዋፅኦ እንደሚያደርጉም ገልፀዋል፡፡ በ2016 ከተሰበሰበው 24 ሚሊዮን ብር ወደ 2 ሚሊዮን የሚሆነው የግል ባለሀብቶች ድጋፍ መሆኑን አስታውሰው፤ የእነሱ ትብብር ክልሉን የተሻለ አፈፃፀም እንዲኖረው ማድረጉን አስረድተዋል፡፡

የአባልነት መታወቂያ ዕድሳቱ ላይ በዘመቻ የሚሰጠው የተፋጠነ አገልግሎትም አበረታች መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ነገር ግን እንደሀገር የመድኃኒት አቅርቦት ላይ ያለው ክፍተት አባላቱ ላይ ቅሬታ እየፈጠረ መሆኑ ተግዳሮት እንደሆነባቸውም ገልፀዋል፡፡

በሱማሌ ክልል ጤና ቢሮ የጤና መድህን አስተባባሪ የሆኑት አቶ በድሪ አብዲ በበኩላቸው፤ የ2017 ዓ.ም የጤና መድህን ንቅናቄ በክልሉ መጀመሩን ገልፀው፤ በዚህ ዓመት እንደተያዘው አርባ አዳዲስ ወረዳዎችን ተደራሽ ለማድረግ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ በህዳር ወርም አዳዲስ አባላትን የመመልመል ስራ እንደሚጀመር ጠቁመዋል፡፡

አዲሱን የቁርጥ ክፍያ አከፋፈል ለመተግበር ዝግጅት ላይ መሆናቸውን የገለፁት አስተባባሪው፤ ከፍተኛ፣ መካከለኛና ዝቅተኛ ተብሎ በገቢ መጠን መሰረት የሚከፈል መሆኑን አስታውሰዋል፡፡ ከአንድ መቶ አርባ ጤና ጣቢያዎችና ከ18 ሆስፒታሎች ጋር ውል መፈራረማቸውንም ያስረዳሉ፡፡

በክልሉ ያለው የጤና መድህን ተጠቃሚ ቁጥር አንድ መቶ ሰማንያ ሶስት ሺህ መሆኑን ገልፀው፤ በዚህ ዓመት ደግሞ አንድ ሚሊዮን ለማድረስ መታቀዱን ጠቁመዋል። በገንዘብ ደረጃም አምና አርባ ሚሊዮን እንደተሰበሰበ ገልፀው፤ በቀጣይ ሰባ ሚሊዮን ለማድረስ መታቀዱን አብራርተዋል፡፡

ዲጂታል የማድረግ ስራም በአንድ ወረዳ እንደተጀመረ ይገልፃሉ፡፡ ከዛ ባሻገር አገልግሎቱ ከሌሎች ክልሎች ዘግይቶ የተጀመረ መሆኑና ማህበረሰቡ ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ የሚተዳደር መሆኑ ተግዳሮት እንደሆነባቸው ገልፀዋል፡፡

በ2016 በከተማ አስተዳደሩ የተሻለ አፈፃፀም እንደነበረና ተጠቃሚውን ወደ 78በመቶ ለማድረስ መቻሉን የገለጹት ደግሞ ወ/ሮ ሜሪ አብዱ በድሬዳዋ ጤና ቢሮ የማህበረሰብ ጤና መድህን አገልግሎት አስተባባሪ ናቸው። እንደእርሳቸው ገለፃ 50ሺ 985 አባዎራዎችን አባል ማድረግ ተችሏል፡፡ በ2016 ዓ.ም ወደ 58ሚሊዮን ብር መሰብሰቡንም አስታውሰዋል፡፡

ከተማ አስተዳደሩም ለ10ሺ 908 አባወራዎች ድጋፍ እንደሚያደርግ ገልፀው፤ ለዚህም ወደ 10 ሚሊዮን ብር ከአስተዳደሩ ገቢ መገኘቱን ጠቁመዋል፡፡ አስራ ስድስት ጤና ጣቢያዎች ሁለት ሆስፒታሎች፣ አንድ የቀይ መስቀል ፋርማሲ ፣ ሶስት የሕዝብ መድኃኒት ቤቶች መኖራቸውን የገለፁት አስተባባሪዋ፤ ከሌሎች ክልሎች በተለየ መልኩ ለጤና ጣቢያዎች የቅድመ ክፍያ አገልግሎት ስላለ የተሻለ የመድኃኒት አቅርቦት እንዲኖር አስችሏል ይላሉ፡፡

ከዚህ በፊት የነበረውን የመድኃኒት ቤቶቹን በየሶስት ወሩ መጠየቂያ እየላኩ መጠየቂያው ተተንትኖ አቅርቦቱ የመዘግየቱን ስራ እንዳስቀረም አስረድተዋል፡፡ ከዚያ ባሻገር አንዱ ጋር የሌለውን መድኃኒት ከአንዱ እንዲያገኙ የማድረግ ስራም እንደሚሰራ ጠቁመዋል፡፡ በዚህ ዓመትም አዲሱን የቁርጥ ክፍያ አከፋፈል ለመተግበር እየተወያዩ እንዳለ አብራርተዋል፡፡

# ሲዳማ ባንክ 71 ነጥብ 6 ሚሊዮን የተጣራ ትርፍ አስመዘገበ

**አበበች ማቴዎስ**

ሀዋሳ፡- ሲዳማ ባንክ ባለፈው የሂሳብ ዓመት 71 ነጥብ 6 ሚሊዮን የተጣራ ትርፍ ማስመዝገቡን ገለጸ፤

ባንኩ የባለ አክሲዮኖች 3ኛ መደበኛና 3ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በሀዋሳ ትናንት ተካሂዷል።

የባንኩ ዳይሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር አቶ አብርሃም ማርሻሎ የባንኩን ያለፈውን በጀት ዓመት አፈፃፀም ሪፖርት ሲያቀርቡ እንደገለጹት፤ ባንኩ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት 45 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር ትርፍ ለማግኘት አቅዶ 71 ነጥብ 6 ሚሊዮን ብር የተጣራ ትርፍ አስመዝግቧል። ይህም ከእቅዱ አንጻር 58 በመቶ ብልጫ አለው ብለዋል፡፡

ባንኩ በበጀት ዓመቱ ውስጣዊና ውጫዊ ጫናዎችን ተቋቁሞ በተቀማጭ ሀብት አሰባሰብ፣ አዳዲስ ደንበኞች ምልመላ፣ ኮርፖሬት ደንበኞች በማፍራት እና ከክልሉ መንግሥት ጋር ያለውን መልካም ግንኙነት በማጠናከር በሁሉም ዘርፍ ውጤታማ አፈፃፀም ማስመዝገቡንም ተናግረዋል።

የተመዘገበው ትርፍ ባንኩ አዲስ ከመሆኑና ብሔራዊ ባንክ ያስቀመጠውን የብድር ማስፋፊያ ጣሪያ ከነበሩት ፈታኝ ሁኔታዎች አኳያ ሲታይ አበረታች ሊባል የሚችል መሆኑንም ነው አቶ አብርሃም የገለፁት።

በሁሉም ቅርንጫፎች አማካይነት ተቀማጭ ገንዘብ ለማሰባሰብ የተደረገው ጥረት ፈታኝ የነበረ ቢሆንም የባንኩን አጠቃላይ ተቀማጭ ገንዘብ መጠን አንድ ነጥብ 22 ቢሊዮን




ማድረስ መቻሉን ጠቁመው፤የባንኩ አጠቃላይ ሀብትም ሁለት ነጥብ 62 ቢሊዮን ብር መድረሱን ተናግረዋል። ይህም ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር የ98 በመቶ ዕድገት ማሳየቱን አመልክተዋል።

ባንኩ በበጀት ዓመቱ 799 ነጥብ 29 ሚሊዮን ብር ብድር ለደንበኞቹ በመስጠት አጠቃላይ የብድር ክምችት መጠን ወደ አንድ ነጥብ 17 ቢሊዮን ብር ማሳደግ ተችሏል ነው ያሉት፡፡

በበጀት ዓመቱ በደንበኞቻችን ላይ የተከሰተው የንግድና ኢንቨስትመንት መቀዛቀዝ በተበዳሪ ደንበኞች የብድር አመላለስ እና በማሰባሰብ ሂደት ላይ ተፅዕኖ ቢፈጥርም የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድና የስራ አመራሮች በወሰዱት ስትራቴጂካዊ የስራ አመራር የባንኩ ጤናማ ያልሆኑ ብድሮች መጠን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ካስቀመጠው ጣሪያ በታች ሁለት ነጥብ 96 በመቶ እንዲሆን መደረጉንም አንስተዋል፡፡

የባንኩን ቅርንጫፎች አድማስ እና ተደራሽነትን ለማስፋትም በበጀት ዓመቱ 8 አዳዲስ ቅርንጫፎች መከፈት መቻሉን የተናገሩት ሊቀመንበሩ፤ አጠቃላይ የባንኩ ቅርንጫፎች ቁጥር ወደ 39 ከፍ ማለቱን ገልፀዋል።

የባንኩ ባለአክሲዮኖች በተጨማሪ አክሲዮን በመግዛት በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ወደ ተፈለገው የካፒታል መጠን መድረስ እንዲቻል የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉም የባንኩ ዳይሬክተሮች ቦርድ ሊቀ መንበር አቶ አብርሃም ማርሻሎ ጠይቀዋል።

በመደበኛ አስቸኳይ ጉባኤ ለቀጣይ ዓመታት የሚያገለግሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ በባለ አክሲዮኖች ተመርጠዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ምርጫው አትሌቲክሱን የሚታደግ ዕድል ሊሆን ይገባል!

ኢትዮጵያ በዓለም መድረክ ገናና ስም ያተረፈችበት የአትሌቲክስ ስፖርት ከታመመ መሰንበቱ የአደባባይ ሀቅ ነው። ኢትዮጵያ ከጀግናውና ዘመን የማይሽረው የማራቶን ንጉስ አበበ ቢቂላ አንስቶ ዛሬም ድረስ በታላላቅ መድረኮች በድል ያንፀባረቁ እልፍ ከዋክብት ማፍራት ብትችልም ስፖርቱ በብዙ ፈተናዎች ውስጥ እየተጓዘ እንደሚገኝ መደበቅ አይቻልም።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ በእነዚህ ፈተናዎች ውስጥም ሆኖ በራሳቸው ጥረት ውጤቶችን በሚያስመዘግቡ አትሌቶች ድል ተሸፋፍኖ ሕመሙ ችላ ሲባል ኖሯል። ባለፉት ጥቂት የማይባሉ ዓመታት ግን በአትሌቶች የግል ጥረትም የሚመዘገቡ ታላላቅ ውጤቶች እያሽቆለቆሉ መጥተዋል። ኢትዮጵያ ከሌሎች የተለየ አቅምና ችሎታ ያላቸው ብርቅዬ አትሌቶች ይዛ በዓለም መድረኮች ሕዝብ የለመደውን ድል በሚጠበቀው ደረጃ ማስመዝገብ ላለመቻሏ ዋነኛው ምክንያት አስተዳደራዊ ችግር መሆኑ የቅርብ ጊዜ ዓለም አቀፍ ውድድሮችን በማስታወስ ብቻ ማወቅ ይቻላል።

ስፖርት ወዳዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ አትሌቲክስ እንደ ዓይኑ የሚሳሳለት ስፖርት ነው፡፡ አትሌቲክስ የኢትዮጵያን መልካም ገጽታ በዓለም መድረኮች ከመገንባት ባለፈ ለሀገር ያለው ጥቅም ዘርፈ ብዙ ቢሆንም ስፖርቱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአስተዳደራዊ መሰናክሎች ውስጥ ለማለፍ ተገዷል፡፡

የተለመደ ውጤት ያልተመዘገበበትን የፓሪስ 2024 ኦሊምፒክን ጨምሮ በሌሎች ውድድሮች ለገጠሙት የውጤት ማሽቆልቆልና ይህንን ተከትሎ ለተነሳው ውዝግብ በርካታ ምክንያቶች ቢቀርቡም አስተዳደራዊ ጉዳዮች ይበልጥ ሚዛን ይደፋሉ፡፡ በአትሌቲክሱ አስተዳደራዊ ችግሮች የተነሳ እንደሀገር ውጤት ከማጣት አንስቶ በርካታ ብርቅዬ አትሌቶች በሚደርስባቸው በደል በአደባባይ ተከፍተዋል፤ አልቅሰዋል። ሕዝብም ተቆጥቷል፣ አትሌቲክሱ ላይ የሚታየው አስተዳደራዊ ችግር መፍትሄ እንዲበጅለትም ሲጠይቅ ቆይቷል። የሚስተዋለውን አስተዳደራዊ ችግር ለማስተካከል ስፖርቱን ከሚመሩ ሰዎች ጀምሮ ስር ነቀል መዋቅራዊ ለውጥ የግድ ይላል።

በፌዴሬሽን ውስጥ የሚታዩ አስተዳደራዊ እንከኖችን ፈር ለማስያዝ፣ ይህንንም በትክክለኛው መንገድ እንዲጓዝ የሚያደርግ ሁነኛ አመራር የግድ ይላል፡፡ ይህ አይነቱ የስፖርቱ አመራር ደግሞ ፌዴሬሽኑ በየአራት ዓመቱ በሚያደርገው የፕሬዚዳንትና ሥራ አስፈፃሚ አባላት ምርጫ ላይ የጠቅላላ ጉባዔ ድምፅ አግኝቶ ስልጣን እስኪይዝ መጠበቅ አሠራሩ ያስገድዳል፡፡

ይህን ለማድረግ ደግሞ ፌዴሬሽኑ በአራት ዓመት አንድ ጊዜ የሚያደርገውን ፕሬዚዳንታዊና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ምርጫ ሲጠበቅ ቆይቷል። ፌዴሬሽኑን ባለፉት ዓመታት ሲመሩ የቆዩ ሰዎች የአገልግሎት ዘመን መቋጨቱን ተከትሎ በቀጣይ ወር መጀመሪያ አዳዲስ አመራሮች የሚመጡበት ምርጫ ተቃርቧል።

የክልሎችና ከተማ አስተዳደር ፌዴሬሽኖችም ለፕሬዚዳንትነትና ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልነት እንዲወዳደሩ ይወክሉኛል ያሏቸውን እጩዎች አቅርበው ጨርሰዋል። ከቀረቡት እጩዎች ውስጥም በስፖርቱ ኢትዮጵያን በዓለም መድረክ ያኮሩ የቀድሞ አትሌቶችና በስፖርቱ አስተዳደር ውስጥ ቀደም ሲል ያገለገሉ የተለያዩ ግለሰቦች ተካተዋል።

አትሌቲክስ በዚህ ወቅት ትልቅ አቅምን ይጠይቃል፡፡ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ተወዳዳሪነቱ በዓለም ላይ ከሚገኙ ጥቂት ምርጥ ፌዴሬሽኖች(ተቋማት) ጋር ነው፡፡ መገንባት ያለበትም ከሌሎች ዓለም አቀፍ ፌዴሬሽኖች በእኩል መፎካከር የሚችል ሆኖ ነው። ለቀረቡት እጩዎች ድምፅ ከመስጠት በፊት ስፖርቱ በዚህ ዘመን የሚጠይቀውን እውቀትና ክህሎት ማሟላት የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው።

ይህ ምርጫ ስፖርቱን ከገባበት ችግር ለማውጣት የሚችሉ ሁነኛ የአትሌቲክሱ መሪዎች ወደ ኃላፊነት የሚመጡበት ትልቅ ዕድል ነውና ብዙዎች ተስፋ አድርገውበታል። ሕዝብም ምርጫው ከውዝግቦች የፀዳና ፍትሐዊ ሆኖ ተገቢውን ሰው ወደ ኃላፊነት የሚያመጣ እንዲሆን ይጠበቃል። ይህ የተሳካ እንዲሆን የጉባዔው አባላትና በምርጫው ድምጽ የሚሰጡ ሁሉ ትልቅ ኃላፊነትና የሕዝብ አደራ አለባቸው።

የጉባዔው አባላት አትሌቲክሱን የመታደግም ይሁን በቁልቁለት መንገድ እንዲጓዝ የማድረግ ቁልፉ በእጃቸው ላይ ይገኛል። ስፖርቱን ለማቅናት ዕውቀት፣ አቅምና ቅንነቱ ላለው ሰው ብቻ ድምጻቸውን በመስጠት ይህን አትሌቲክሱን የማዳን ትልቅ ዕድል በአግባቡ ሊጠቀሙበት ይገባል።

የሚመረጠው ፕሬዚዳንትም ይሁን የሥራ አስፈፃሚ አባላቶቹ ቀላል ሥራ እንደማይጠብቃቸው አውቀው ኃላፊነት የሚረከቡና የሚወጡ መሆን አለባቸው። አትሌቲክሱ ምን ይፈልጋል፣ አሁን የተሳሳተው ነገር ወይም ችግሩ ምንድነው? የሚለውን ጉዳይ አውቀውና ተረድተው የማስተካከል አቅም እንዲሁም የመምራት ችሎታ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል። በምርጫ ወቅት ድምፅ እንዲሰጡ ከክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮችና የተለያዩ ስፖርት ተቋማት የሚወከሉ ግለሰቦች ድምፅ የሚሰጡት ሰው ስፖርቱን ለማገልገል ተገቢ መሆኑን የማረጋገጥ አደራ እንዳለባቸው ማስታወስ ተገቢ ነው!

**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**

ወርቁ ማሩ

Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ
- አልማዝ አያሌው

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## አማራጭ የወደብ አገልግሎት ለጋራ ተጠቃሚነት

ኃይለማርያም ወንድሙ

ወደቦች ለዓለም አቀፍ ንግድ መስተጋብር ትልቅ አቅም ናቸው፡፡ የትራንስፖርት ድረ-ግብር (network) ወደቦች እንደ መስቀለኛ መንገድ የሚያገለግሉ ናቸው። የሚመሠረቱት ባሕር ዳርቻዎች አካባቢ ሆኖ ለማኅበረ ኢኮኖሚ መሳለጥ ሠፊ ሚና አላቸው ይላል፡፡ ለወደብ ቅርብ የሚሆኑ ከተሞች የማደግ ዕድላቸው ሠፊ ነው። ይህንንም የወደብ ንግድ መስመር የሌላቸው ከተሞችን ካላቸው ከተሞች ጋር በማነፃፀር መረዳት እንደሚቻል የተለያዩ ጥናታዊ ጽሑፎች ያሳያሉ፡፡

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ በይፋ ዕውቅና ያላቸው 44 የባሕር በር የሌላቸው ሀገሮች ይገኛሉ፡፡ ማለትም ነፃና ሉዓላዊ ሀገር ሆነው ድንበራቸው ከባሕር ወይም ከውቅያኖስ ጋር ያልተዋሰነ ማለት ነው፡፡ ከአፍሪካ ደግሞ 16 የባሕር በር የሌላቸው ሀገሮች አሉ፤ ይህም ከአህጉራቱ ሁሉ የአንበሳውን ድርሻ የያዘ ነው፡፡

የባሕር በር ከሌላቸው የአፍሪካ ሀገራት አንዷ ሀገራችን ኢትዮጵያ ነች። ሀገራችን በፍጥረቷ ወደብ አልባ ባትሆንም፤ ወደብ አልባ ከሆነች ግን ሦስት አስርት ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ደርግ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ከሕወሓትና ከሻዕቢያ ጋር ሲያካሂደው የነበረው ጦርነት በግንቦት 1983 ዓ.ም በሽንፈት ሲደመደም ሀገሪቱ የተለያዩ አማራጮች ቢኖሯትም በፈቃድዋ ወደብ አልባ የመሆን ጉዞዋን ጀምራለች፡፡

ኤርትራ ስትገነጠል የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን በዋና ጸሐፊነት የሚመሩት እና ቀደም ብሎ የግብጽ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ቡትሮስ ቡትሮስ ጋሊ ነበሩ፡፡ በወቅቱ ኤርትራ እንድትገነጠልና ኢትዮጵያም ወደብ አልባ ሆና በቀይ ባሕር ላይ ተሰሚነት እንዳይኖራት በማድረግ እግረ መንገዳቸውን ሀገራቸውን ረድተዋታል፡፡

ያው የግብጽ የዘወትር ሥጋትዋ ኢትዮጵያ ከበለፀገች ዓባይን ትገድብብኛለች፤ በምዕራባውያን ዘንድ ያለኝንም ተሰሚነት ትወስድብኛለች የሚል ነው፡፡ ቡትሮስ ጋሊ ኤርትራን አዋልደው ኢትዮጵያን ወደብ አልባ በማድረግ ሂደት የድርሻቸውን ተወጥተዋል፡፡

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያን ኤርትራ፣ ጅቡቲ፣ ሱዳን፣ ደቡብ ሱዳን፣ ሶማሌ ላንድ፣ ሶማሊያና ኬንያ ያዋስናሉ፡፡ ከነዚህ ጎረቤት ሀገሮች እንደ ኢትዮጵያ የባሕር በር የሌላት ደቡብ ሱዳን ናት፡፡ ኢትዮጵያን ስድስቱም የጎረቤት ሀገሮች ሕዝቦች ቢደመሩ ቁጥራቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ አይደርስም፡፡ ከምሥራቅ አፍሪካ ብሎም ከአፍሪካ በሕዝብ ብዛት ከቀዳሚዎቹ ተርታ የምትገኘው ኢትዮጵያ ወደብ አልባ የመሆኗ እውነታ ይዋል ይደር እንጂ የህልውና ጉዳይ ሆኖ መምጣቱ የማይቀር ነው ፡፡

በወቅቱ በዲፕሎማሲ መንገድ በተመድ እና በአህጉር አቀፍ ተቋማት በመከራከርና የወደብ ባለቤትነት መብቷን ማስከበር እንደምትችል ብዙዎች ይስማማሉ። ይህ ግን ሊሆን አልቻለም፤ ለዚህ ትውልድ ትልቁ የቤት ሥራ ሆኖ ተቀምጧል። አሁን ከወደብ ጋር በተያያዘ እንደ ሀገር እየሄድንበት ያለውም መንገድም የዚሁ እውነታ አካል ነው።

አሁንም ላይ የወደብን ጉዳይ ሰጥቶ በመቀበል በጋራ ተጠቃሚነት መርህ ለመፍታት እየሄድንበት ያለው መንገድ ሰላማዊ ብቻ ሳይሆን ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያለንን ግንኙነት በማጠናከር ቀጣናዊ የኢኮኖሚ አቅም ለመገንባት የሚያስችል እንደሚሆን ይታመናል።

ሀገራችን ለጐረቤት ሀገራት አማራጭ ወደቦችን ለመጠቀም ያቀረበችውም ጥያቄ ከዚሁ ጋር አብሮ የሚታይ ነው፡፡ የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ምጣኔ ሀብታዊና ማኅበራዊ ትስስራቸው የበለጠ እንዲጎለብት እንደሚረዳም ብዙዎች ይስማሙበታል፡፡

ይህንን ታሳቢ ባደረገ መንገድ፤ በቅርቡ የኢትዮጵያን የባሕር በር የማግኘት ፍላጎት ሊያሳካ የሚችል ስምምነት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድና የሶማሌ ላንድ ፕሬዚዳንት ሙሴ ቢሂ አብዲ በአዲስ አበባ የመግባቢያ ሰነድ መፈራረማቸው ይታወሳል፡፡ ይህም የኢትዮጵያን የባሕር በር አማራጮችን የሚያሰፋ መሆኑ እሙን ነው፡፡

በስምምነቱ መሠረት ኢትዮጵያ ከሶማሌ ላንድ በሊዝ የወደብ ባለቤት የምትሆንበት እድል ይፈጠራል፡፡ ይህም በአንድ ወደብ አገልግሎት መገደብን ያስቀራል፡፡ አማራጭ ወደቦችን የመጠቀም እድል በመፍጠር የሀገሪቱን የወጪ እና ገቢ ንግድ ማቀላጠፍ ያስችላል፡፡

ከዚህ ባለፈም የቀይ ባሕር ቀጣና የስዊዝ ቦይና የህንድ ውቅያኖስ መገናኛ ነው፡፡ የእስያንና የአፍሪካን ሀገራት ከአውሮፓ ጋር የሚያገናኝ የዓለማችን ትልቁ የንግድ መስመርም ነው፡፡ በየቀኑ ከ160 በላይ ግዙፍ የንግድ መርከቦች የሚቀዝፉበት፤ በብዙ ቢሊዮን ዶላር በላይ የዓለም ዓመታዊ ንግድ ልውውጥ የሚካሄድበት ነው።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ለቀይ ባሕር ቀጣና የቅርብ ሩቅ መሆንዋ ተገቢ አይደለም፡፡ ለቀይ ባሕር ባይተዋር መሆንዋ በአካባቢው ያላትን አቅም በመጠቀም ለአካባቢው ሰላም እና መረጋጋት ማበርከት የሚገባትን እንዳታበረክት ያደርጋታል፤ በብሔራዊ ጥቅሞቿ ላይም የሚያሳድረው ተጽእኖ ቀላል የሚባል አይሆንም፡፡

ኢትዮጵያ ከሶማሌላንድ በሊዝ ወደብ ማግኘቷ ስምምነት ዕውን ሲሆን የወደብ ንግዱን ከማሳለጥ ባለፈ፤ የቀይ ባሕር የባሕር ወንብድናን በመቆጣጠር የቀይ ባሕር እና የአካባቢውን ሰላም ማስከበር ትችላለች፡፡ ከዛም ባለፈ ስትራቴጂክ ብሔራዊ ጥቅሞቿን ማስጠበቅ ያስችላታል፡፡ ሀገሪቱ ወደ ቀይ ባሕር የመመለሷ እውነታ ለአካባቢው ስጋት የሆነውን የባሕር ውንብድናን (pric-ey) በመከላከል ሂደት የሚኖረውም ጠቀሜታ ከፍ ያለ ነው።

ጅቡቲ ለኢትዮጵያ የምትሰጠው የወደብ አገልግሎት በዓመት በአማካይ 1 ነጥብ 6 ቢሊዮን ዶላር እንደሚያወጣ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህ ትልቅ ገቢ ደግሞ ለልዕለ -ኃያላኑ ወታደራዊ ጦር ሰፈር ምሥረታ የባሕር በሯን ቸርችራ በማከራየት ከምታገኘው 500 ሚሊዮን ዶላር በላይ እንደሆነ አቶ ጌታቸው ወልዩ በአንድ ወቅት ባወጡት አንድ ጽሑፍ አስረድተዋል፡፡

በምስራቅ አፍሪካ ካለን 120 ሚሊዮን ሕዝብ ብዛትና ከቆዳ ስፋታችን እና እያደገ ከሚሄደው ኢኮኖሚያችን አኳያ በአንድ ወደብ ላይ መገደብ የለብንም፡፡ እያደረ የሚመጣውን የወደብ አገልግሎት የጅቡቲ ወደብ ብቻውን አይሸከመውም ፤ ይህንን መረዳት ደግሞ ብዙም አስቸጋሪ አይደለም፡፡

የጂቡቲ ወደብ የነዳጅ ማጠራቀሚያ ዴፖ የሚሰጠው አገልግሎት አቅም እየቀነሰ ነው፡፡ ይህም በኢትዮጵያ የነዳጅ አቅርቦት ላይ መስተጓጎል እየፈጠረ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በያዝነው ዓመት ከጂቡቲ በተጨማሪ በሶማሌ ላንድ በርበራ ወደብ በኩል ነዳጅ ለማስገባት ምክረ ሃሳብ ቀርቦ የመንግሥት ውሳኔ እየተጠበቀ እንደሆነ ከኢትዮጵያ ነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን የተገኘ መረጃ ያሳያል፡፡

በቅርቡ «ኢትዮጵያ በማንም ተሸንፋ እንደ ማታውቀው ሁሉ ማንንም ሀገር ወራም አታውቅም፤» በማለት የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ በወደብ ጉዳይ በወንድም የጎረቤት ሕዝቦች ላይ ቃታ እንደማትስብ ተናግረዋል፡፡ በሰላማዊ መንገድ ካልሆነ በስተቀር ኢትዮጵያ የባሕር በር የማግኘት ሌላ ፍላጎት እንደሌላትም አመልክተዋል፡፡

ከለውጥ ወዲህ አማራጭ ወደቦችን ለመጠቀም የሚያስችሉ ተስፋ አመንጪ ፋና ፈንጣቂ ጅምሮች ነበሩ። እነዚህ ቢተገበሩ አማራጭ ወደቦች እንዲኖረን ሁነኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ለኬንያ፣ ለሶማሊያ፣ ሶማሌ ላንድና እንዲሁም ለሱዳን ወደቦች ቅርብ የሆኑ የኢትዮጵያ አካባቢዎችና ከተሞች ነዋሪዎችም ተጠቃሚዎች ይሆናሉ፡፡

ወደብ አልባ መሆናችን በሀገር ውስጥ ከተሞች ደረቅ ወደብ እንድንመሠርት መሠረት ሆኗል፡፡ የወደብ ኪራይ እየተከፈለ ዕቃው በጅቡቲ ወደብ ማቆየቱ ሀገሪቱን ለወጪ የዳረገ ነው፡፡ ይህን ችግር ለመፍታት የሞጆ፣ የድሬዳዋ ደረቅ ወደቦችን ጨምሮ የኮምቦልቻ ደረቅ ወደብ እንዲመሠርት ተደርጎ አገልግሎት እየሰጠ ነው። ደረቅ ወደብ በሀገር ውስጥ ለማስፋፋት የተሰጠው ትኩረት ያህል ኢትዮጵያ የባሕር በር ኮሪደር ለማግኘት የምታደርገው ዲፕሎማሲያዊ ጥረት አሁንም ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፡፡

በኢትዮጵያ አዳዲስ የባሕር በር ኮሪደሮች እውን ቢሆኑ ለዜጎች አዳዲስ ሥራዎች ይፈጠራሉ፣ አዳዲስ ከተሞች ይዋለዳሉ፣ ያድጋሉ፣ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ይስፋፋሉ፡፡ ይህም ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለቀጣናው ሀገራት ሕዝቦች አዲስ የትብብር ምዕራፍ የሚከፍት ነው።

በቀጣይ አማራጭ የወደብ ስምምነቶቹ ከሶማሌ ላንድ በተጨማሪ ከኬንያ ከሱዳን ጋር ተግባራዊ ይሆናሉ የሚል እምነት አለ፡፡ የተጀመረው አማራጭ የወደብ አገልግሎት የማግኘት ጥረት አጠናክሮ መቀጠል ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርግ ከመሆኑ አኳያ ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባ የትውልዱ ትልቁ የቤት ሥራ ነው፡፡

## ከአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር በየ 15 ቀኑ የሚታተም

# ዩኒቨርሲቲው ያስተናገደው የኢትዮ-ሩሲያ ጉባዔ

**ዘላለም ተሾመ**

በኢ.ኤ.አ በ2030 ብሄራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ማዕከል ለመሆን ብሎም በአህጉር አቀፍ ደረጃ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሆኖ ለመውጣት ራዕይ በማስቀመጥ በመስራት ላይ የሚገኘው አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ከተለያዩ ዓለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ተቋማት ጋር አብሮ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

ከነዚህ የትብብር ሥራዎች መካከል ከተለያዩ ተቋማት ጋር በጋራ አውደ ጥናቶችን፣ የምርምር ጉባዔ እና የጋራ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት ተቋማት ያላቸውን እውቀት እና ልምድ አንዱ ለሌላው እንዲያካፍል ምቹ ሁኔታን መፍጠር አንዱ ነው። ለምሳሌ በኮሪያ፣ በጃፓን፣ በቻይና እንዲሁም በአውሮፓ ከሚገኙ ታዋቂ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የጋራ የመግባቢያ ስምምነት በመፈራረም በተማሪዎች እና መምህራን ልውውጥ፣ ሀገር አቀፍ ፋይዳቸው ከፍተኛ የሆኑ የጋራ ፕሮጀክቶችን በጋራ በመሥራት ዓለም አቀፋዊነቱን እያሳደገ ይገኛል፡፡

ሰሞኑንም የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ እና በሩሲያ የሚገኙ አራት የቴክኖሎጂ ተቋማትን ያሳተፈ ኢትዮ-ሩሲያ የትምህርትና ቴክኖሎጂ ጉባዔ በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ አስተናጋጅነት ተካሂዷል፡፡ የጉባዔው ዋና አላማ አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ እና በሩሲያ የሚገኙ እውቅ የቴክኖሎጂ ተቋማት በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ አብረው እንዲሠሩ ትስስር እና የእውቀት ሽግግር መፍጠር ነው፡፡

በጉባዔው ላይ ከሩሲያ ተቋማት የመጡ ታዋቂ ምሁራን እና ተመራማሪዎች ተገኝተዋል፡፡ በተጨማሪም የሩሲያ መንግሥት ኮርፖሬሽን "ROSATOM" አምኒስክ ቴክ የኒውክለር ኃይል ምህንድስና ተቋም፣ ሞስኮ የምህንድስና ፊዚክስ ተቋም እና ከቅዱስ ፒተርስበርግ ኤሌክትሮ ቴክኒካል ዩኒቨርሲቲ የመጡ ተወካዮች ተሳታፊዎች ነበሩ፡፡



መርሐ - ግብሩን በይፋ ያስጀመሩት የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር አብረሃም ደበበ ናቸው፡፡ ዶክተሩ በእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክታቸውም ጉባዔው ዩኒቨርሲቲው በትምህርት እና ቴክኖሎጂ ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ያለውን ትስስር እንዲያጠናክር እና የልምድ ልውውጥ እንዲያደርግ ምቹ አጋጣሚ በመፍጠር በቀጣይም የሁለቱን ሀገራት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ትስስር የሚያሳድግ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ዶ/ር አብረሃም አያይዘውም ዩኒቨርሲቲው ለኢንዱስትሪው የሚያደርገውን አስተዋጽኦ የሚደግፍ እና በተለይም በዩኒቨርሲቲው የሰው ኃይል ልማት፣ በኒውክለር ሪያክተር ቴክኖሎጂ የልህቀት ማዕከል ላይ የሚኖረው አወንታዊ አስተዋጽኦ ትልቅ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የኒውክለር ሪያክተር ቴክኖሎጂ የልህቀት ማዕከል አንዱ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራበት ማዕከል መሆኑን በመጠቆም ሩሲያ የቴክኖሎጂ ተቋማት ጋር በተለያዩ ፕሮጀክቶች፣ በምርምር፣ በስልጠና እና ትምህርት ላይ አብሮ መስራት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን መፍጠር እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡

ይህም ተቋማቱ በጋራ የምርምር ሥራዎች፣ የሰው ኃይል ሥልጠና፣ የእውቀት እና ልምድ ልውውጥ እንዲሁም በተማሪ መምህራን ልውውጥ ዘርፎች ላይ አጋርነታቸውን በማጠናከር አብረው ለመሥራት መልካም አጋጣሚ እንደሚፈጥር አብስረዋል፡፡

ከሩሲያ የቴክኖሎጂ ተቋማት የመጡ ተወካዮች በበኩላቸው፤ በአዳዲስ የቴክኖሎጂ እና ትምህርት ዘርፎች ላይ በተለይም በኑክሌር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ፣ በምርምር ፕሮጀክቶች እና በሙያዊ ሥልጠናዎች ላይ ሊኖሩ የሚችሉ የትብብር እድልን ገልጸዋል። ሁለቱ ሀገራት በቀጣይ ለሚሠሯቸው ሳይንስና ቴክኖሎጂ ተኮር ስራዎች ጉልበት የሚሆን እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡ በተለየ መልኩ በኑክሌር ቴክኖሎጂ ላይ የትብብር አስፈላጊነትን አጽንኦት ሰጥተው የገለጹት የተቋማት ተወካዮች በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የኒውክሌር ሬያክተር ቴክኖሎጂ የልህቀት ማዕከል የዩኒቨርሲቲው አንዱ የትኩረት ዘርፍ መሆኑ ለጋራ ተነሳሽነቶች የማዕዘን ድንጋይ ሆኖ ሊያገለግል እንደሚችልም አያይዘው ተናግረዋል፡፡

ድል በላብ ይገኛል እንዲሉ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ያለፉትን አመታት ራዕዩን እውን ለማድረግ በቁራጥነት በመሥራት ወደህልሙ በሚያስጠጋው የተስፋ ጎዳና ላይ መሆኑ እየሠራቸው ካሉ ሥራዎች መረዳት ይቻላል፡፡ ሰሞነኛው የሁለትዮሽ ጉባኤም የዚህ ትጋት አንዱ አካል በመሆን የሚገለጽ ነው፡፡ በጉባኤው ላይ ከሩሲያም ሆነ ከኢትዮጵያ ተወካዮች በኩል የተላለፉ መልዕክቶች ለጋራ ጥቅም በጋራ መሥራት ያለውን ሁለንተናዊ ፋይዳ በመደገፍ በቀጣይ የተሻሉ ሥራዎችን ለመሥራት ጥቁምታ የሚሰጡ ነበሩ፡፡

እንዲህ ያሉ ጥምረቶች ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሽግግር ባለፈ ለበጎ ሀገራዊ ገጽታው የሚውሉ ናቸው፡፡ ዘመናዊነት ቦታ በመቀየርና እንዲህ ባሉ የልምድ ልውውጦች በኩል የሚያጨነቁር መሆኑ እሙን ነው፡፡ በእድገትና ሥልጣኔ ስም የሚጠሩ ለሀገርና ሕዝብ ብሎም ለትውልድ ደጀን የሆኑ ሥራዎች ከአንዱ ወደአንዱ ቅብብሎሽ መሆናቸው እንዲሁ የአደባባይ ሀቅ ነው፡፡

የዓለም ስርአት የሰጥቶ መቀበል ስርአት ነው፡፡ ያለን ሰጥቶ የሌለን መቀበል ልክ ከእኛ ለሌላው ከሌላው ለእኛ አይነት መልዕክት ያለው ነው፡፡ የኢትዮ ሩሲያ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ወዳጅነትም በዚህ እከክልኝ ልከክልህ ስም የሚገለጽ ነው፡፡ እንዲህ ያሉ ከሌላው መጥተው ሌላውን የሚጠቅሙ እውቀትን፣ ተሞክሮን፣ መሰል መልካም ዕድሎችንም መሰረት ያደረጉ ቅብብሎሾች እንደሀገር ፋይዳቸው የትየሌለ ነው፡፡

በአጠቃላይ ፎረሙ ዓለም አቀፍ አጋርነቶችን በማጎልበት ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ያለው ሲሆን አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን እና በተቋማት መካከል የእውቀት ሽግግር እንዲኖር መልካም አጋጣሚ የፈጠረ እንደነበር ተገልጿል፡፡ የኢትዮ-ሩሲያ የትምህርት እና ቴክኖሎጂ ጉባዔ አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በቴክኖሎጂ ልማት እና ትምህርት እድገት ላይ ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ለመሥራት ያለውን ቁርጠኝነት የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በቀጣይም መሰል የትብብር ጉባኤዎችን በማዘጋጀትና በመሳተፍ በ2030 የተቀመጠውን እቅድ ከማሳካት ባለፈ እንደሀገር የምናተርፍበትም ጭምር ነው፡፡

# ከእናት ወደ ልጅ የሚተላለፉ በሽታዎች ትኩረት እንደሚሹ ተገለጸ

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

አዲስ አበባ፡- ከእናት ወደ ልጅ የሚተላለፉ ኤች አይ ቪ ኤድስ ፣ ቂጥኝ እና ሄፒታይተስ ቢ አሳሳቢ የጤና ስጋት እየሆኑ በመምጣታቸው ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራው ይበልጥ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት የጤና ሚኒስቴር ገለጸ፡፡ መገናኛ ብዙኃን ግንዛቤ የማስጨበጥ ኃላፊነታቸውን በትኩረት እንዲወጡ ጥሪ አቀረበ።

በጤና ሚኒስቴር የኤች አይ ቪ መከላከልና መቆጣጠር ክፍል ኤክስፐርት አቶ ሙለጎ ሻፊ እንደገለጹት፤ በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን ከእናት ወደልጅ የሚተላለፉና አሳሳቢ የጤና ችግሮች ተብለው በተለዩት በኤች አይ ቪ ኤድስ ፣ በቂጥኝ እና በሄፒታይተስ ቢ በሽታዎች ዙሪያ ሚዲያዎች ግንዛቤ የማስጨበጥ ሰፊ ስራ መስራት አለባቸው፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ጥናት እ.አ.አ በ2024 በሀገራችን 13 ሺ 312 ኤችአይቪ በደማቸው የሚገኝ ነፍሰጡር እናቶች መኖራቸውን ያመለከቱት አቶ ሙለጎ፤ ይህ አሀዝ ቀድሞ ከነበረው 16 ነጥብ 9 በመቶ ወደ 8 ነጥብ 64 በመቶ ቀንሷል፡፡ ይሁን እንጂ ቁጥሩ በተፈለገው ልክ የወረደ ባለመሆኑ ግንዛቤው ላይ ጠንክሮ መስራት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

እንደ ሀገር ከኤች አይ ቪ ኤድስ ነጻ የሆነ ትውልድን ለመፍጠር ከተቀመጠው ግብ አኳያ፤ የበሽታው ስርጭት እየጨመረ መ ምጣቱ ሀገር ተረካቢ ትውልድ በማፍራት ሂደት ውስጥ ስጋት መሆኑን አመልክተዋል፡፡

የቂጥኝ በሽታ በነፍሰ-ጡር እናቶች ላይ ሲከሰት 80 በመቶ ያህል በጽንሱ ጤና ላይ ከፍ ያለ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል የጠቆሙት አቶ ሙለጎ ፤ ጥናታዊ አሀዝ እንደሚያመለከተው የበሽታው ስርጭት በየጊዜው እየጨመረ እንደሚገኝና በአሁኑ ጊዜም ከዜሮ ነጥብ 6 በመቶ ወደ 5 ነጥብ 1 በመቶ ከፍ እንዳለ ገልጸዋል፡፡

የሄፒታይተስ ቢ በሽታም አሁን ላይ አሳሳቢ የሚባል የጤና ችግር ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ይህ በሽታ በሀገራችን 4 ነጥብ 8 በመቶ ያህል ሽፋን አለው፡፡ በሽታው በእናቶች ላይ በተከሰተ ጊዜ የሚያደርሰውን የከፋ ጉዳት በመገመትም ከፍ ያለ ክትትል እንደሚያስፈልግ አስታውቀዋል፡፡

ሂፒታይተስ ቢ በተለይ ኤችአይቪ ባለባቸው እናቶች ላይ ታክሎ ሲመጣ ልዩ ትኩረት እንደሚያስፈልግ አቶ ሙለጎ ገልጸው፤ ለዚህም የጤና ሚኒስቴር ዕቅድ ይዞ በትኩረት እየሰራ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

ከበርካታ ተላላፊ በሽታዎች በላይ ለሶስቱ የተለየ ትኩረት የተሰጠው የመተላለፊያ መንገዳቸው ተመሳሳይ በመሆኑ ነው ያሉት አቶ ሙለጎ ፤ ሁሉም በሽታዎች የሚተላለፉት በግብረ-ስጋ ግንኙነት ነው፡፡ እናቶች በነዚህ በሽታዎች ከተጠቁ በኋላ የሞትና ህመም ምጣኔያቸው ከፍ ያለ እንደሚሆን አስታውቀዋል።

ነፍሰ-ጡር እናቶች በጊዜና በወቅቱ ወደ ጤና ተቋማት በመሄድ በሽታዎቹ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፉ ማድረግ እንደሚቻል የገለጹት አቶ ሙለጎ፤ በሽታዎቹ ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት የእናቶችንና የህጻናትን ጤና በመጠበቅ ሂደት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብለዋል፡፡

በበሽታዎቹ ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠር ወሳኝ መሆኑን ያመለከቱት አቶ ሙለጎ፤ ለዚህ ደግሞ የሚዲያ ተቋማት ኃላፊነት ከፍያለ ነው ብለዋል። ለዚህ የሚሆን ዝግጁነት መፍጠር ከመገናኛ ብዙኃን ይጠበቃል ብለዋል፡፡

የህብረተሰቡን ጤና ለማሻሻል በሚደረገው ትግል ሚዲያዎች ተገቢውን መረጃ ለህብረተሰቡ የማድረስ ሚናቸውን ሊወጡ፤ በተለይ ከእናት ወደልጅ በመተላለፍ የጤና ችግሮች በሆኑት ሶስቱ በሽታዎች ላይ ግንዛቤ የማስጨበጥ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል።

# "ብልፅግና ፓርቲ በአምስት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ከብልፅግና የሚጎድል ኢትዮጵያዊ እንደማይኖር ገልጸው፤ በብዛት መንገዶች ቢገነቡ፣ ከተሞች ቢዘምኑ፣ የግብርናው ምርታማነት ቢጨምር፣ ኢንዱስትሪው ቢስፋፋና ሌሎች ዘርፎች ቢያድጉ ከብልፅግና የማይጠቀም ኢትዮጵያዊ እንደማይኖር ገልጸዋል፡፡

ባለፉት አምስት ዓመታት ጉዞ ፓርቲው እውቀት፣ ጥበብና እውነትን ባይሰንቅ ኖሮ በቀላሉ የማይታለፉ ችግሮች አጋጥመውት እንደነበር አውስተው፤ ብልፅግና ፓርቲ እነዚህን ችግሮች በጽናት በመቋቋም ጥበቡን ተጠቅሞ ወደ ዕድል እንደቀየራቸው አመልክተዋል፡፡

ብልፅግና ሙሉዕ ዕይታ ያለው ፓርቲ ነው። ቅድሚያ ግብርና፣ ቅድሚያ ከተማ፣ ቅድሚያ ኢንዱስትሪ አይልም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፤ፓርቲው በአንድ ጊዜ ግብርናን፣ ኢንዱስትሪን፣ ቴክኖሎጂ፣ ከተማን፣ ገጠርን፣ ዲፕሎማሲንና ሌሎች ዘርፎችን አስተሳስሮ መምራት የሚሻና የሚችል መሆኑን በተግባር አሳይቷል ብለዋል፡፡

የሌሎችን ሀገራት የፖለቲካ ሥርዓት ሙሉውን መቅዳት፣ ኃይልና ሃሳብን መቀላቀል፣ ዲሞክራሲያዊነት አለመኖር፣ የወዳጅና የጠላት ፖለቲካ ማራመድና አካታችነት ጉድለት ያለፉት 50 ዓመታት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲዎች ስብራቶች መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ብልፅግና ፓርቲ ከእነዚህ ስብራቶች ትምህርት በመውሰድ አዲስ ሀገራዊ የፖለቲካ እሳቤን ተግባራዊ ማድረጉን ነው የተናገሩት፡፡ በዚህም ብዙ ስኬቶች ማስመዝገብና ተግዳሮቶችን ማለፍና ወደ ድል መቀየር እንደቻለ አብራርተዋል፡፡

መዳረሻችን ሁለተኛዊ ብልፅግና፣ መንገዳችን መደመር፣ ገዥ ትርክታችን ህብረ ብሔራዊነት፣ ማሳለጫችን ምክክር፣ትብብር፣ ቅንጅት፣ አጋርነት፣ ወንድማማችነትና እህትማማችነት ነው ያሉት የብልፅግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ፤ ባለፉት አምስት ዓመታት በሁሉም ዘርፍ የታሪክ እጥፋት የተመዘገበበት መሆኑንም ነው ያመላከቱት፡፡

ፈተናን ወደ ድል መቀየር የብልፅግና ፓርቲ ተጨባጭ መገለጫዎች መሆናቸውን ገልጸው፤ፓርቲው በርካታ ፈተናዎች ቢያጋጥሙትም እነዚህን ፈተናዎች ወደ ድል በመቀየር አንጸባራቂ ውጤቶች ማስመዝገቡን ተናግረዋል።

የትግላችን መዳረሻ ጠንካራ ሀገረ መንግሥት መገንባት ነው ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ ቃልን በተግባር መፈጸም የብልፅግና ፓርቲ ተጨባጭ መለያዎች ናቸው ብለዋል።

በሁሉም ዘርፎች ከፍተኛ ውጤት መመዝገቡን ገልጸው፤ "በተገኙ ውጤቶች ሳንዘናጋ ውጤቶቻችንን አጠናክረን እንቀጥላለን" ብለዋል፡፡

የብልፅግና ፓርቲ አምስተኛ ዓመት የምስረታ በዓል "የሃሳብ ልዕልና ለሁለንተናዊ ብልጽግና" በሚል መሪ ሃሳብ በተለያዩ ሁነቶች ሲከበር መቆየቱ ይታወሳል።

# ማዕከሉ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ማዕከሉን እንደራሳቸው መጠቀም የሚችሉበት መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ወንጀልን በጋራ መከላከል ካልተቻለ ወንጀለኞች በሀገር አጥር የሚገደቡ አይደለም ያሉት ምክትል ኮሚሽነሩ፤ የማዕከሉ አደረጃጀት፣አሰራርና አቅም እየተገነባ ያለው ለሁሉም ማገልገል በሚያስችል መልኩ ነው ብለዋል፡፡

ፖሊስ ዩኒቨርሲቲው የፎረንሲክና የምርመራ ትምህርትና ሥልጠና ማዕከል ሆኖ በቀጣይነት ብቁ ባለሙያዎችን ለማፍራት በመደበኛ፣ ሥልጠናዎች፣ በአጫጭር ፕሮግራሞች እያሰለጠነ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ የማዕከሉን ባለሙያዎች የማሰልጠን ሥራ ተሠርቷል ብለዋል፡፡

በቀጣይ ሁልጊዜ እያደገ ከሚሄደው ቴክኖሎጂ ጋር አዳዲስ ግብዓቶችንና ቴክኖሎጂዎች እየተጨመሩለት እንደሚሄድ በመግለጽ፣ተጨማሪ ማሽኖችንና የሰው ኃይል በማስገባት አቅምን ማሳደግና በተለያዩ አካባቢዎች ላይ ቅርንጫፎችን የማስፋት ሥራ እንደሚሠራ ጠቁመዋል፡፡

የፌዴራል ፖሊስ የፎረንሲክ ምርመራና የምርምር ልህቀት ማዕከል በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)ህዳር 7 ቀን 2017 ዓ.ም መመረቁ ይታወሳል፡፡

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# ፈጠራንና እውቀትን አስኳሉ ያደረገ ስትራቴጂ

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂ ማዕቀፍ ግምገማን አስመልክተው ባስተላለፉት መልዕክት፤ በኢትዮጵያ የሀገር በቀል ለውጥ አጀንዳ፣ ብሔራዊ የ10 ዓመት ዕቅድ፣ የዘላቂ ልማት ግቦች ዕቅድ እና ከአፍሪካ ኅብረት አሕጉራዊ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂ ማዕቀፍ የመነጨው ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 በኢትዮጵያ ፈጠራ እና የእውቀት መሠረት ያለው ኢኮኖሚ ለማደራጀት ያለመ እንደሆነ ገልጸዋል። ፈጠራንና እውቀት ያዙልኝ፤

ዛሬ የዓለማችን ኢኮኖሚ እየተቃኘና እየተመራ ያለው ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት በፈጠራና በእውቀት ነው። በምድራችን በሀብትና በወረት ቀዳሚ የሆኑ 10 ኩባንያዎች የነዳጅ፣ የወርቅ፣ የአልማዝ፣ የሜርኩሪ፣ ወዘተረፈ ማዕድናትን የሚያለሙ አልያም የእነ ቶዮታ፣ ኒሳን፣ አይሱዙ፣ ፎርድ፣ ወዘተረፈ አምራች ኩባንያዎች አይደሉም። ወይም እነ ቦይንግና ኤርባስ አይደሉም። በዓለማችን ከአንድ እስከ አስር ያሉ ግዙፍና ቀዳሚ ኩባንያዎች በፈጠራ፣ በእውቀትና በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዙሪያ የተመሠረቱ ናቸው። ቴስላ፣ አፕል፣ ሜታቨርዝ፣ ማይክሮሶፍት፣ ጉግል፣ አማዞን፣ አሊባባ፣ ሳምሰንግ፣ ሁዋዌ፣ ወዘተረፈ ናቸው የዓለምን ኢኮኖሚ ከፊት ሆነው እየመሩ ያሉት።

የመጀመሪያው ባለ ትሪሊየን ዶላር ወረት ኩባንያ ሆኖ የተመዘገበው ኩባንያ የሳዑዲው ግዙፍ የነዳጅ ኩባንያ ራምኮ፣ ወይም የእንግሊዙ ብሪቲሽ ፔትሮሊየም፣ አልያም የአሜሪካው ኤክሶን፤ አልያም የጃፓኑ ቶዮታ ሳይሆን አፕል ነው። እሱን ተከትለው ዛሬ እነ ቴስላም ባለ ትሪሊየን ዶላር ኩባንያ ሆነዋል። አሜሪካም ዛሬ ልዕለ ኃያል ሀገር የሆነችው በሠራዊቷ ብዛት በአየር ኃይሏና በባሕር ኃይሏ ብቻ ሳይሆን ከፍ ብለው በተጠቀሱት በፈጠራና በእውቀት በተመሠረቱ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ኩባንያዎቿ ነው። በሰው ሠራሽ አስተውሎት እያስመዘገበችው ያለ ስኬት መሪነቷን አጠናክሮላታል።

ሀገራችንም ይሄን ሰልፍ በጊዜ ተቀላቅላ የትሩፋቱ ተጠቃሚ መሆን አለባት። ለኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት የተሰጠው ትኩረት ይበል የሚያሰኝ ቢሆንም አሁንም ሌት ተቀን መሥራትን፤ ከዓለም እኩል መሮጥን ይጠይቃል። ጎረቤት ሀገራት በዘርፉ እያስመዘገቡት ያለው እመርታ ሊያስቀናንና ሊያስቆጨን ይገባል። ሀገራችን የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂ ነድፋ ለተግባራዊነቱ እየሠራች መሆኗ ይበል የሚያሰኝ ቢሆንም ከዘርፉ ፈጣን ዕድገትና ተለዋዋጭነት አንጻር ራስን መልሶ መላልሶ መፈተሽ ያሻል።

ለአፍታ ለቅጽበት እንኳ ዓይንን ከዚህ ዘርፍ ማንሳት ኋላ ያስቀራልና። ከስር ከስር አፈጻጸሙን መከታተል፤ ስኬቱን ማስፋት፤ ክፍተቱን እየገመገሙ መሙላት ይጠይቃል። የስትራቴጂው አፈጻጸም ግምገማ የዚህ አካል ነው። በነገራችን ላይ የ "ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025" ስትራቴጂ በዋናነት የዲጂታል መሠረተ ልማት በመገንባት እና በማስፋት የአገሪቱን ምጣኔ ሀብታዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ እድገት ማፋጠንን ዓላማ ያደረገ ዘመኑንና ትውልዱን የዋጀ ስትራቴጂ ነው::

"የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025" ስትራቴጂ የመካከለኛ ዘመን የግምገማ መድረክ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን (ዶ/ር) ጨምሮ የፌዴራል እንዲሁም የክልል ከፍተኛ አመራሮች እና የዘርፉ ተዋናዮች በተገኙበት በዓድዋ መታሰቢያ ሙዚየም ነው የተካሄደው:: ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ለዕቅዱ መነሾ የሆኑ ሀገራዊ ተግዳሮቶችን አብራርተዋል። በኢትዮጵያ የሀገር በቀል ለውጥ አጀንዳ፣ ብሔራዊ የ10 ዓመት ዕቅድ፣ የዘላቂ ልማት ግቦች ዕቅድ፣ የአፍሪካ ኅብረት አሕጉራዊ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂ ማዕቀፍ ውስጥ የመነጨው ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 በኢትዮጵያ ፈጠራ እና የእውቀት መሠረት ያለው ኢኮኖሚ ለማደራጀት ያለመ እንደሆነ ገልጸዋል።

በግምገማ መድረኩ ላይ የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት አስተዳደር (ኢመደአ) ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ ትዕግስት ሃሚድ የ"ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025" ስትራቴጂን እውን ለማድረግ እንደ ተቋም የተሠሩ ዋና ዋና ሥራዎችና ስኬቶች ዙሪያ ገለጻ አድርገዋል:: ዋና ዳይሬክተሯ ባቀረቡት ማብራሪያ የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት አስተዳደር ለዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ መሠረት የሚሆኑ የዲጂታል ፕላትፎርሞችን (Digital Foundations) በማልማት እንዲሁም የሀገራችንን የሳይበር ደኅንነት በማረጋገጥ ረገድ የሠራቸው ሥራዎች እና የተገኙ ስኬቶች ምን እንደሚመስሉ በዝርዝር አቅርበዋል::

የ"ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025" ስትራቴጂን እውን ለማድረግ ዋና የጀርባ አጥንት የሆነው ቁልፍ የሕዝብ መሠረተ ልማት የመረጃ ቋት ግንባታ (Public Key Infrastructure Data Center) መሆኑን የገለጹት ዋና ዳይሬክተሯ ይህንን እውን ከማድረግ አኳያ ኢመደአ የዚህን የመረጃ ቋት ግንባታ የማጠናቀቅ ምዕራፍ ላይ እንደሚገኝ፤ ሌላው ለዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ መሠረት የሆነው "ፋይዳ" የተሰኘው ብሔራዊ መታወቂያ ሲሆን ይህንን ፕሮግራም ከመደገፍ አኳያ ኢመደአ የራሱን ሚና እየተጫወተ እንደሚገኝም፤ በሀገራችን የሚካሄደውን የዲጂታል ክፍያ ሥርዓት ከማዘመንና ደኅንነት ከማረጋገጥ አኳያ "ደራሽ" የተሰኘ ደኅንነቱ የተጠበቀ የክፍያ ፕላትፎርም በማልማት ተግባራዊ መደረጉን ወ/ሮ ትዕግስት ገልጸዋል::

በሌላም በኩል የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂን እውን ከማድረግ አኳያ የሀገራችንን የሳይበር ደኅንነት ማረጋገጥ ቁልፍ አጀንዳ እንደሆነ፤ ብሔራዊ የሳይበር ደኅንነትን እና ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የሕግ ማዕቀፎችን በማዘጋጀት በኩል ኢመደአ በርካታ የሕግ ማዕቀፎችን ማውጣቱን፤ ለአብነትም፡ ብሔራዊ የሳይበር ደኅንነት ፖሊሲ፣ የኤሌክትሮኒክ ፊርማ አዋጅ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርቶች ደህንነት ፍቃድና ቁጥጥር አዋጅ ወ.ዘ.ተ የሚጠቀሱ ናቸው::

በሀገራችን የሳይበር ሥነ ምሕዳር ላይ የሚቃጡ የሳይበር ጥቃቶችን አስቀድሞ ለመከላከል እና ከተከሰተም አፋጣኝ መፍትሔ ለመውሰድ የሚያስችል "ብሔራዊ የሳይበር አደጋ ዝግጁነትና ምላሽ መስጫ ማዕከል" በማቋቋም በርካታ የሳይበር ጥቃቶችን የመከላከል ሥራ መሠራቱን፤ ከዚህም ባሻገር የተቋማትን የሳይበር ደኅንነት ዝግጁነትና አቅም ለማጠናከር የሚያስችል የሳይበር ደኅንነት ፍተሻ በማድረግ ቀጣይነት ያለው የሳይበር ደኅንነትን የማረጋገጥ ሥራ እየተሠራ እንደሆነ እና የሳይበር ደኅንነትን ለማረጋገጥ ቁልፉ ሀገራዊ የቴክኖሎጂ ባለቤትነትን ማረጋገጥ እንደሆነ የገለጹት ወ/ሮ ትዕግስት፤ ከዚህ አኳያ ኢመደአ በራሱ አቅም በርካታ የሳይበር ደህንነት ቴክኖሎጂዎችን ማልማቱን፤ በኢመደአ የሚገኘው "የኢትዮ ሳይበር ታለንት ማዕከል" ለዲጂታል 2025 አቅም የሚሆኑ ታዳጊ ወጣቶችን እያፈራ እንደሆነም ገልጸዋል::

ዓለማችን ሦስተኛውን የኢንዱስትሪ አብዮት አገባዳ ወደ አራተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ማማተር ከጀመረች ሰነባበተች። ሦስተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ከ20ኛው መክዘ አጋማሽ ዛሬ ድረስ የቀጠለው ሲሆን፤ የዲጂታል ቴክኖሎጂ፣ በይነ መረብ ወይም ኢንተርኔት፣ አውቶሜሽን፣ ሮቦቲክስና ሌሎች ቴክኖሎጂዎች የተስፋፉበትና በስፋት ጥቅም ላይ የዋሉበት ነው። ብዙ ሊቃውንት አሁን የምንገኝበትን ጊዜ የአራተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት የተጀመረበት፤ የዲጂታል ቴክኖሎጂ የተቀናጀበት፣ የሰው ሠራሽ አስተውሎት ወደ ሥራ የገባበት፣ በይነ መረብ እያንዳንዱን የሕይወት ቅንጣትና የኢኮኖሚ ዘርፍ ማዳረስ የጀመረበት ከመሆኑ ባሻገር በአኗኗራችንና በግንኙነታችን ላይ ዕለት ዕለት እየተገለጠ ያለ ነው። እጃችን የገባን ቴክኖሎጂ ተለማምደነውና ተዋውቀነው ሳናበቃ እጃችን ላይ የሚያረጅበትና በፍጥነት የሚለዋወጥበት ዘመን ነው።

ዓለማችን እጃችን ላይ ዲጂታል እየሆነች ነው። በዲጂታል ቴክኖሎጂና በኮሙኒኬሽን ኔትወርክ እየተሳሰረች በአኗኗራችን፣ በሥራችንና በዕለት ተዕለት ግንኙነት ላይ ለውጥ እየመጣ ነው። ከዚህ ጋር የተያያዙ ዲጂታል መሣሪያዎች፣ የሶፍትዌር መተግበሪያዎች፣ እንደ ፌስቡክ ያሉ ማኅበራዊ መድረኮች፣ በመረጃ ወይም በዳታ ላይ የተመሠረቱ እንደ መረጃ የማፈላለግና ኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች እየተስፋፉ ነው። ፍጥነት፣ ተለዋዋጭነት፣ የማያቋርጥ መሻሻል፣ ወዘተረፈ የዲጂታል ዓለሙ መለያ ነው።

ለፈጠራና ለንግድ አዳዲስ ዕድሎችን ይዞ እንደመጣው ሁሉ የዜጎችን ግለ ሕይወት ወይም ፕራይቬሲ፣ ደኅንነትና ግንኙነት አደጋ ላይ እየጣለ ነው። የተሳሳተና ሆን ተብሎ የተዛባ መረጃ እንደ እንጉዳይ እየፈላ፤ በይነ መረብ፣ ማኅበራዊ ሚዲያ፣ የሞባይል ስልኮች፣ ክላውድ፣ ቢግ ዳታ አናሌቲክስ፣ ሰው ሠራሽ አስተውሎትና ብሎክቼይን የዲጂታል ዓለሙን ወደ አዲስ ምዕራፍ እያሸጋገሩት ይገኛል። እነዚህ የቴክኖሎጂ እምርታዎች መረጃን በቀላሉ እንድናጋራና እንድንለዋወጥ፣ ከሌሎች ጋር እንድንተባበር፣ ሂደቶችን አውቶሜት እንድናደርግ፣ የዲጂታል ምርቶችንና አገልግሎቶችን እንድናስፋፋ በመጋበዝ አኗኗራችንና አሠራራችን አቅልለውልናል።

ወደ አሕጉራችን አፍሪካ ስንመጣም በስፋት ጥቅም ላይ እየዋለ እናገኘዋለን። ዲጂታል ቴክኖሎጂዎችና ፈጠራዎች በፍጥነት እያደጉ ነው። የተንቀሳቃሽ ስልክና የበይነ መረብ ተጠቃሚዎች መበራከት ለአፍሪካ ዲጂታል ኢኮኖሚ ማበብ የማይተካ ሚና እየተጫወተ ይገኛል። ዲጂታል አፍሪካ ሰፋ ያለ የዲጂታል ቴክኖሎጂን ማለትም የሞባይል ስልኮችን፣ ማኅበራዊ ሚዲያን፣ ኢ-ኮሜርስን፣ የዲጂታል ክፍያን፣ ፊንቴክን፣ ኢ-ጤናን፣ ኢ-ትምህርትን እና ኢ-ግብርናን የሚያካትት ነው። በአሕጉሩ ለዲጂታል ፈጠራ መስፋፋትና መጎልበት የአንበሳውን ድርሻ እየተጫወተ ያለው ደግሞ የሞባይል ስልክ ሲሆን ለበይነመረብ ተደራሽነትና ለዲጂታል አገልግሎት መስፋፋትም የማይተካ ሚና እየተጫወተ ይገኛል። ሞባይል መኒ በአፍሪካ እያደገ ለመጣው የፋይናንስ አካታችነት እንዲሁ የላቀ አስተዋፅዖ እያበረከተ ነው።

በሚቀጥሉት ዓመታት የዲጂታል ኢኮኖሚ ተጽዕኖ በአፍሪካ አሁን ከሚገኝበት ይልቅ እያደገና እንደ ዋርካ እየሰፋ እንደሚሄድ ሀገራችን ጥሩ ማሳያ ናት። የዲጂታል መሠረተ ልማት መስፋፋት ለዲጂታል ኢኮኖሚው ጥሩ መደላድል እየፈጠረ ነው። ሆኖም ተግዳሮቶች የሉበትም ማለት አይደለም። የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተደራሽነት በእኩል ደረጃ አለመገኘት ወይም ዲጂታል ዲቫይድ ቀዳሚው ችግር ነው። ዜጋው ስማርት ስልኮችን፣ ታብሌቶችን፣ ላፕቶፖችንና በይነ መረብን በቀላሉ አለማግኘቱ የመረጃ ተደራሽነቱን ኢ-ፍትሐዊ አድርጎታል። የዲጂታል ክህሎት እጥረትና የዲጂታል ኢንቨስትመንቱ ውስን መሆን ሌላው የዘርፉ ማነቆ ነው። ለመሆኑ በሀገራችንስ ዲጂታል ኢኮኖሚው በምን ሁኔታ ነው የሚገኘው።

የመንግሥት ኤሌክትሮኒክስ ክፍያ ድርሻን ለማሳደግና ቀልጣፋ ለማድረግ እስካሁን ወደ 200 የሚጠጉ ባለ በጀት መሥሪያ ቤቶች የኤሌክትሮኒክስ ክፍያ ዘዴ እንዲተገብሩ መደረጉ፤ ለአብነትም የታክስ ክፍያ አሰባሰብ ሥርዓቱ በቴሌ ብር እንዲከፈል የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱ ይጠቀሳል። ኢትዮ ቴሌኮም የቴሌ ብር የሞባይል ገንዘብ ዝውውርን ይፋ ካደረገበት ግንቦት 3 ቀን 2013 ዓ.ም ጊዜ አንስቶ እስካሁን ከ51 ሚሊዮን በላይ ደንበኞችን አገልግሎት በመስጠት፤ ከ3 ነጥብ 2 ትሪሊየን ብር በላይ ግብይቶችና ዝውውሮች መፈጸማቸው ውጤታማነቱን ያሳያል። ወደ ዲጂታል ኢትዮጵያ ዘፍጥረት ስንመለስ።

ኢትዮጵያ የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂን ቀርፃ እና አፅድቃ ወደ ሥራ ከገባች ሦስተኛ ዓመቷን ተያይዛለች። ዲጂታል ኢትዮጵያ የዲጂታል ዕድሎችን በመጠቀም ፈጠራ የታከለበትና በእውቀት ላይ የተመሠረተ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያስችል በኢትዮጵያ መንግሥት የሚመራ ተነሳሽነት ነው። ከሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳ እና የ10 ዓመት የልማት ዕቅድን ከመሳሰሉ ቁልፍ ሀገራዊ ስትራቴጂዎች ጋር እንዲሁም እንደ አፍሪካ ኅብረት አሕጉራዊ ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂ ካሉ ዓለም አቀፍ ስትራቴጂዎች ጋር የተሳሰረ ነው ።

ዲጂታል ኢትዮጵያ የመንግሥትን፣ የግሉን ዘርፍና የልማት ኤጀንሲ ተዋንያንን በአንድ ላይ በማሰባሰብ፣ መሠረታዊ የዘርፍ ተነሳሽነትን በመለየት የሀገሪቱን ዲጂታል ኢኮኖሚ ጉዞን ለማሳለጥ እንዲሁም የኢትዮጵያ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽንን በግንባር ቀደምትነት ለመምራት የሚችሉና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ሊጠቀሙ የሚችሉ አራት ስትራቴጂያዊ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ዘርፎችን ለይቷል። ግብርና፣ የማምረቻ ዘርፍ፣ የመረጃ ቴክኖሎጂና ቱሪዝም ቅድሚያ የተሰጣቸው ዘርፎች ናቸው።

**ለመሆኑ ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ምንድነው?**

ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን፥ በአካል ከሚደረጉ ግንኙነቶች ወጥቶ የዲጂታል አሠራሮችን በመተግበር ወደ ዲጂታል ኢኮኖሚ ለመድረስ ባለ ሂደት ውስጥ ያለ "ጉዞ" ነው። የዲጂታል የሽግግር ጉዞ በመንግሥት፣ በንግድ ድርጅቶች እና በማኅበረሰቡ መካከል ግንኙነት በአካል ይካሄድ ከነበረበት አናሎግ ኅብረተሰብ ወጥቶ ግንኙነትና ልውውጦች በበይነ መረብ በጣም ፈጣን፣ ርካሽ፣ እና ደኅንነቱ አስተማማኝ የሆነን ቴክኖሎጂን በመጠቀም ወደሚካሄዱበት የተቀናጀና አካታች ዲጂታል ኢኮኖሚ የሚደረግ ጉዞ ነው።

ዲጂታል ኢኮኖሚ የሚያመለክተው የተሻሻለ የኔትወርክ ግንኙነቶችን እና እርስበርስ ተያያዥነት ያላቸውን የዲጂታል መድረኮችን በመጠቀም የሚደረግ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን ነው። የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ጉዞ ከአናሎግ ኢኮኖሚ ይጀምራል። በአናሎግ ኢኮኖሚ ውስጥ በዜጎች በመንግሥትና በንግድ ድርጅቶች መካከል ያለው ግንኙነት የዲጂታል ቴክኖሎጂን የማይጠቀም እና በአካል የሚደረግ ነው። ከአናሎግ ኢኮኖሚ ቀጥሎ የሚገኘው ደግሞ ዝቅተኛ የዲጂታል ተደራሽነት ነው። በዚህ ውስጥ ውስን የዲጂታል መሠረተ ልማት ይኖራል፤ የተወሰኑ የዲጂታል ማሳያዎች ብቅ ብቅ ማለት ይጀምራሉ።

የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ጉዞው ይቀጥልና አናሎግ ግን የዲጂታል አሠራር እያደገ ይሄዳል። በዚህ ውስጥ አብዛኞቹ አገልግሎቶች አናሎግ የሆኑበት፣ ግልፅ የሆነ የዲጂታል ራዕይ ካልተቀናጁ አገልግሎቶች ጋር ያሉበት እና የሚተገበርበት ነው። ይህ አናሎግ እና ያልተቀናጀ የዲጂታል አገልግሎት ደግሞ የተቀናጀ የዲጂታል ሥርዓትን ይወልዳል።

በዚህ ውስጥ የላቀ፣ የተቀናጀ የዲጂታላይዜሽን አገልግሎትና ጠንካራ አስቻይ ሥነ ምሕዳሮች ይኖራሉ። የዲጂታል ኢኮኖሚም ይገነባል። የዲጂታል ኢኮኖሚ የተሟላ የዲጂታል ኢኮኖሚ የተተገበረበት፣ ከመንግሥትና የንግድ ተቋማት ጋር ለመገናኘት የዲጂታል አገልግሎትን የሚጠቀም ነው። የንግድ ተቋማት ፈጠራ የታከለበት አገልግሎት ያቀርባሉ። የመንግሥት ሥራዎችና አገልግሎቶች ዲጂታል ይሆናሉ። አብዛኞቹ የንግድ መነሻዎች ዲጂታል ይሆናሉ ።

**ሻሎም! አሜን።**

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# ልበ ቀናው የልብ ሕሙማን ሕፃናት ደራሽ

ዳግም ከበደ

በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1989 ዓም የሕፃናት ልብ ሕሙማንን የሚደግፍ መርጃ ማዕከል ያቋቋሙ ናቸው። አንድ ብር ለአንድ ልብ በሚል ሀገራዊ ንቅናቄ በመፍጠር ወገን ለወገኑ እንዲደርስ ምክንያት ሆነዋል። የልብ ታማሚዎችን እርዳታ በማስተባበር ወደ ውጪ መላክ የመጨረሻ ግብ አለመሆኑንም ተረድተው የሕክምና ተቋማት እዚሁ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲገነባ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርገዋል።

እኚህ ባለራዕይ የብዙ ሺህ ሕፃናት ነፍስን ከስቃይ ያዳኑ፤ የልብ ሕመም (በተለይ የሕፃናት) ልዩ ትኩረት እንዲሰጠው አምባሳደር የሆኑ ናቸው። እኚህ ሰው የሕፃናት ልብ ሐኪምና በኢትዮጵያ የልብ ሕሙማን ሕፃናት መርጃ ማዕከል መሥራች ዶክተር በላይ አበጋዝ ናቸው። የዝግጅት ክፍላችን የእኚህን የኢትዮጵያውያን ባለውለታ የሕይወት ገፅታ እንደሚከተለው ይቃኛል።



ዶክተር በላይ አበጋዝ፤

### ትውልድና እድገት

ዶክተር በላይ አበጋዝ በ1937 ኅዳር 12 በደሴ ከተማ ነው የተወለዱት። እድገታቸው ደግሞ በደቡብ ወሎ ዞን በምትገኘው ኩታ በር ነው። ፍቅር፣ ብዝኃ ባሕልና ሃይማኖት አሰባጥራ የያዘችው ወሎ እኚህን ታላቅ ሰው ብታፈራም ዛሬን አሻግራ ተመልክታ የኢትዮጵያ ባለውለታ እንደሚሆኑ ገና አልተገለጠላትም ነበር። ነገር ግን አንድ እውነታን መካድ አይቻልም፤ የሰሜኑ ክፍል የአብሮነትና የመቻቻል ምሳሌ ወሎ ‹‹የሀገር ኩራት የሕዝብ አለኝታ›› ባለውለታዎችን ማፍራት ሁሌም አይነጥፍባትምና አንጋፋውን የጤና ዘርፍ ጀግና ሳትሰስት ጀባ አለችን።

የያኔው ብላቴና የዛሬው የልብ ሕሙማን አለኝታ ዶክተር በላይ በኩታበር የሕይወትን መንገድ አሐዱ ብለዋል። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በዚያው በኩታበር ነበር የጀመሩት። በቀለም ትምህርት አንቱ የተባሉና ብሩህ አዕምሮ ከታደላቸው ታዳጊዎች ውስጥ አንዱ ነበሩ። አባታቸው አቶ አበጋዝ በኩታ በር የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህርና ዳይሬክተር ነበሩ። ይህ አጋጣሚ ደግሞ እርሳቸውም በተፈጥሮ የታደሉት ፀጋ ጋር ተደምሮ ስኬታማ የትምህርት ግዜን እንዲያሳልፉ ምክንያት ሆኗቸዋል።

ወሎ ከጉያዋ ለሚወጡ ልጆቿ የቀለም ትምህርት ብቻ አትለግስም። ይልቁኑ አብሮ የመኖር ብልሀትን፣ የሃይማኖት መቻቻልን፣ ለሀገር እና ለሕዝብ የመኖር ጥበብን ጨምራ ታሳድጋለች። ዶክተር በላይ ይህን ጥበብ ከትምህርታቸው ጎን ለጎን ተምረው አድገዋል። መክሊታቸውን ያወቁበትን መዳረሻ ራዕያቸውን የቀረፁበትን ትምህርት ከኩታ በር ባሻገር ከታዋቂውና በደሴ ከተማ ከሚገኘው ወይዘሮ ስህን ትምህርት ትምህርት ቤት ቀስመዋል። ይህ ትምህርት ቤት አንጋፋና ለሀገር ባለውለታ የሆኑ በርካታ ግለሰቦች የወጡበት ታዋቂ የአስኳላ መንደር ነው።

ዶክተር በላይ አበጋዝ እርሳቸውን ጨምሮ ከ12 እህትና ወንድሞቻቸው ጋር ነው ያደጉት፤ ለእናትና አባታቸው ሦስተኛ ልጅ ናቸው። ከቀለም ትምህርት ባሻገር የአደን ዝንባሌም ነበራቸው። ያደጉበት አካባቢ ገጠራማ የኢትዮጵያ ክፍል መሆኑ ለዚህ ዝንባሌያቸው ልዩ አስተዋፅዖ ነበረው። የልጅነት ጊዜያቸውን ከትምህርት ባሻገር ለምግብነት የሚውሉ እንደ ቆቅ፣ ጅግራና ሌሎች የዱር እንስሳትን በማደን ያሳልፉ ነበር።

ይህ ልምዳቸው ከተፈጥሮና መልክዓ ምድር ጋራ ያላቸውን ግንኙነት ይበልጥ ያስተሳሰረ ነበር። ያደጉበት ባሕልና እሴት ደግሞ ከሰዎች ጋር ጥብቅ ግንኙነት እንዲያዳብሩ፣ ሩህሩህ ማንነት እንዲገነቡና ለማኅበራዊ እሴቶች ትልቅ ስፍራ እንዲኖራቸው አድርጓቸዋል። ለዚህ ነው ሁለንተናዊ ስብዕናን የገነቡ መነሻቸውንም ሆነ መድረሻቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁ ትጉህ ሰው ለመሆን የበቁት።

### ከፍተኛ ትምህርት

ዶክተር በላይ አበጋዝ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በከፍተኛ ውጤት ካጠናቀቁት መካከል ናቸው። ይህንን አቅማቸውን የተገነዘበው በሐረር የሚገኘው የያኔው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የጦር አካዳሚ ለውትድርና ትምህርት ከመረጣቸው ባለ ብሩህ አዕምሮ መካከል አንዱ ነበሩ። በጊዜው የትምህርት ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች በአካዳሚው እየተመረጡ የውትድርና ሳይንስን በማጥናት በከፍተኛ

**የልብ ሕክምና አሁንም ድረስ እጅግ ውድና ውስብስብ ሁኔታዎችን መጋፈጥ የሚጠይቅ ነው። በአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ዘንድ ይህንን ሕክምና በቀላሉ ለማግኘት የሚታሰብ አይደለም። በዚህ ምክንያት ብዙዎች ሕይወታቸውን ያጡ ዘንድ ተገድደዋል**

የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ይመደቡ ነበር። እርሳቸውም ይህ ዕጣ ደርሷቸው በእጩ መኮንንነት ወታደራዊ ሳይንስ ተምረው እስከ ሌተናል ኮለኔልነት ማዕረግ ደርሰዋል። በጊዜው ከትምህርቱና ወታደራዊ ማዕረጉ ባሻገር በአካዳሚው ለሁለት ዓመታት መምህር ሆነው አገልግለዋል። በጊዜው የነበራቸው ንቁ ተሳትፎና በውትድርና ሙያቸው ባሳዩት የላቀ አፈጻጸምም በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አራት ጊዜ ተሸልመዋል።

ዶክተር በላይ አበጋዝ፤ በልጅነታቸው የሕክምና ባለሙያ (ዶክተር) የመሆን ልዩ ፍላጎት ነበራቸው። ይህ ሕልማቸው እውን ይሆን ዘንድ የላቀ የትምህርት ውጤት እንደሚያስፈልግ በማወቃቸው ጠንክረው ለመማራቸው ምክንያት ነበር። ወደ ሐረር አካዳሚ ሲገቡም የልጅነት ሕልማቸውን ታሳቢ አድርገው ነበር። የውትድርና ሳይንስ መማራቸው ደግሞ ይበልጥ ወደ ሙያው እንዲሳቡና ሙሉ ለሙሉ ወደ ሕክምናው እንዲገቡ ገፊ ምክንያት ሆኗቸዋል።

በአካዳሚው ለሁለት ዓመታት ካስተማሩና ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ለአራት ጊዜያት በላቀ አፈፃፀም ከተሸለሙ በኋላ ቀጣይ ጉዞ ያደረጉት የልጅነት ሕልማቸውን ከዳር ወደሚያደርሱበት ዩኒቨርስቲ ነው። የሐረር ቆይታቸው አብቅቶ የሕክምና ትምህርት ለማጥናት ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለመግባትና ውጤታማ ለመሆን ጊዜ አልፈጀባቸውም። በ1961 ዓም የዩኒቨርስቲውን የሕክምና ኮሌጅ ተቀላቅለው በትምህርት ቆይታቸው በነበራቸው ውጤታማነት ተሸላሚ ሆነው አጠናቀቁ። የዶክተር በላይ የሕይወት ጉዞ አቅጣጫውን በመቀየር ለማነንነታቸው መሠረት የሆነውን ማኅበረሰብ በጤናው ዘርፍ ለማገልገል መንገዳቸውን ጀመሩ።

### እውቀትን ወደ ተግባር

ዶክተር በላይ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የጦር አካዳሚ ብሔራዊ አገልግሎት በውጤታነት አጠናቀው ወደ ሕክምና ትምህርት ገብተዋል። ትምህርታቸውንም በሚገባ ጨርሰው ዳግም ብሔራዊ አገልግሎት ትርጉም ወዳሳያቸው ውትድርና በሕክምና የሙያ መስክ ተመለሱ። በአዲስ አበባ ጦር ኃይሎች ሆስፒታል በመግባት ለዳር ድንበሩ የሚዋደቅ ወታደር እና ውትድርናን ዳግም ማገልገል ጀመሩ። ይህ ጊዜ በቅርብ ላጠናቀቁት የሕክምና ትምህርት ይበልጥ እንዲቀርቡና ሙያቸውን ተግባር ላይ አውለው ሀገራቸውን እንዲያገለግሉ ምክንያት የሆናቸው ነበር።

እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1977 ወደ አሜሪካ ተጉዘው ዳግም የሕክምና ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት በጦር ኃይሎች ሆስፒታል ሲያገለግሉ ቆዩ። ይህ ቆይታቸው ሙያውን የበለጠ እንዲያከብሩት ኢትዮጵያም በዘርፉ አንድ ተጨማሪ ጉምቱ ባለሙያ የምታፈራበት አጋጣሚን እንዲፈጠር አስቻለ። ይህን ጊዜ ነበር ለተጨማሪ ትምህርት ሀገራቸውን መልቀቅ የግድ የሆነባቸው።

ዶክተር በላይ ከጠቅላላ ዶክተርነት ወደ ስፔሻላይዝድ ያደረገ ሕክምና ባለሙያ ያሸጋገራቸውን ትምህርት በሀገረ አሜሪካ ነበር የተማሩት። በቆይታቸው ዛሬም ድረስ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ስማቸው ገንኖ እንዲጠራ ምክንያት የሆናቸውን የሕፃናት ሕክምና ዶክተር እንዲሁም የሕፃናት ልዩ የልብ ሐኪም የሚያደርጋቸውን ትምህርታቸውን በብሩክሊን ሜዲካል ኮሌጅና በኒውዮርክ ዩኒቨርሲቲ በስኬት አጠናቀቁ። በጥቅሉ በአሜሪካን ሀገር ለ6 ዓመታት ቆይተው ዳግም ሊያገለግሏት ቃላቸውን ወደሰጧት ሀገራቸው ኢትዮጵያ ተመለሱ።

### ቁጭት የወለደው ራዕይ

ዶክተር በላይ አበጋዝ ያስተማረ ወገናቸውን አልዘነጉም። ይህንን ማድረግ የሚያስችል ስሪትም አልነበራቸውም። ይልቁኑ በሠለጠነ ሀገር ላይ ምንም ሳይጎልባቸው መማራቸው ሀገራቸውን ይበልጥ እንዲወዱ፣ መልካሙን ሁሉ ለኢትዮጵያ እንዲመኙ ነበር ያደረጋቸው። የሕፃናት የልብና ጠቅላላ ሕክምና ስፔሻላይዝ ማድረጋቸው ደግሞ በኢትዮጵያ ለመታከም አቅም የሌላቸው ዜጎች ዕድል ፈንታ እንዲያሳስባቸው ያደረገ ነበር።

የልብ ሕክምና አሁንም ድረስ እጅግ ውድና ውስብስብ ሁኔታዎችን መጋፈጥ የሚጠይቅ ነው። በአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ዘንድ ይህንን ሕክምና በቀላሉ ለማግኘት የሚታሰብ አይደለም። በዚህ ምክንያት ብዙዎች ሕይወታቸውን ያጡ ዘንድ ተገድደዋል። ይህንን እውነት መቀልበስ ደግሞ የዶክተር በላይ የዘወትር ሕልም ነበር።

ለስድስት ዓመት በትምህርት በቆዩባት አሜሪካ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## ልበ ቀናው የልብ...

ከገጽ 6 የዞረ

ውስጥ ነበር የሕፃናት የልብ ሕክምና በነፃ ለወገናቸው መስጠት የሚያስችል ድርጅት ለማቋቋም ማሰብ የጀመሩት። የመጀመሪያው ውጥናቸው የቻሉትን ያህል ሕፃናት ሕክምናው ወደሚገኝበት ሀገር በመላክ ማሳከም ሲሆን፤ ቀስ በቀስ ደግሞ የልብ ሕሙማን ሐኪም ቤት በሀገራቸው በመክፈት፣ ባለሙያ በማፍራትና በቂ ዘመናዊ መሣሪያዎችን በማሟላት ሕፃናት ታማሚዎችን የመርዳት ግዙፍ እሳቤ ነበራቸው።

ዶክተር በላይ ከአሜሪካ መልስ ሆስፒታሉን መገንባት፣ የሕክምና መሣሪያውን ማሟላት፣ የሰው ኃይል ማግኘትና ዘላቂነቱን ማረጋገጥ የሚሉ አራት የራዕያቸውን ምሰሶዎች በአዕምሯቸው ጠንስሰው መምጣታቸውን በተደጋጋሚ ሲናገሩ ይደመጣል። በተለይ ‹‹መጀመር ሳይሆን ቁምነገሩ ዘላቂነቱን ማረጋገጥ ነው›› በሚለው ሀሳባቸው ይታወቃሉ።

እርሳቸው ስለዚህ ውጥን ሲገልፁ “በኢትዮጵያ የልብ ሕክምና ማዕከል የማቋቋም ሀሳብ የተጠነሰሰው በ1970 ዓ.ም በአሜሪካ ነው፤ በልብ ሕክምና ሙያ ለመሠልጠን (ስፔሻላይዝድ ለማድረግ) በዶክትሬት ዲግሪ የተመረቅኩበትን የትምህርት ማስረጃ እና የወደፊት ፍላጎቴንየሚገልጽ ሀሳብ ለኒውዮርክ ዩኒቨርሲቲ አቀረብኩ፤ ቃለ መጠይቅ ያደረገችልኝ ፕሮፌሰር ኢጂኒ ዶይል፤ ‘የምንቀበለው 10 ሰዎችን ነው፤ አንተ የተቀመጥኸው 10ኛ ላይ ነው፤ ባቀረብከው ማመልከቻ ውስጥ ጥሩ እና ደስ የሚሉ ነገሮች አይቻለሁ፤ ስላቀድካቸው ነገሮች ከአንደበትህ መስማት እፈልጋለሁ፤ እውነት ትምህርትህን ስትጨርስ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰህ በልብ ሕክምና ትሠራለህ?’ በማለት ስትጠይቀኝ። እኔም “አዎ!” በማለት በእርግጠኝነት መለስኩላት” ይላሉ።

ከስድስት ዓመታት በኋላ የኢትዮጵያን አፈር ከረገጡ ጀምሮ ለውጥናቸው መሳካት ከላይ እታች ይሉ ጀመር። የሚያውቋቸውን ሰዎች የሕፃናት ልብ ሕሙማን መርጃ ማዕከል የማቋቋም ሕልማቸውን በማጋራት ድጋፍ ማሰባሰብ ጀመሩ። ይህንን ተግባራቸውን የሚያከናውኑት ጎን ለጎን በተማሩት የሕክምና ዘርፍ ወገኖቻቸውን እየረዱ በተጨማሪነት ነበር።

በዶክተሩ መዝገበ ቃል ውስጥ ‹‹አይቻልም›› የሚል ቃልም ትርጉምም የለውም። ያሰቡትን ለማሳካት ዓመታትን ፈጅተዋል። መርጃ ማዕከሉ ሕጋዊ ሰውነት ይዞ መቋቋም እንዲችል ብዙ ውጣ ውረድን ያልፉ ዘንድ የግድ ብሏቸዋል። ከዚህ ውስጥ የመንግስት ቢሮክራሲ ቀዳሚው ነው። ሕጋዊ ሰውነት አግኝቶ በተራድዖ ድርጅትነት እንዲመሠረት ፈቃድ የሚሰጥ አካል ተባባሪነት መጥፋቱ ግን ከእቅዳቸው አላሰናከላቸውም።

ኋላ ላይ በብዙ ጥረት ፈቃዱን በማግኘታቸው በ1989 ዓም በይፋ የልብ ሕሙማን ሕፃናት መርጃ ማዕከልን አቋቋሙ። የመጀመሪያው እቅዳቸው ግቡን መታ። ሕጋዊ የተራድዖ ድርጅት ፍቃድ ከማግኘታቸው በፊት ለ108 የሚደርሱ ሕፃናትን በግላቸው ከውጪ ሕክምና ተቋማት ጋር ግንኙነት እየፈጠሩ በነፃ ሕክምና እንዲያገኙ አድርገው ነበር። በወቅቱ የአንድን ህፃን ሕክምና ለማሳካት በትንሹ እስከ 7 ሺህ ዶላር ይጠይቅ ነበር።

### የማዕከሉ እውን መሆን

ዶክተር በላይ የልብ ሕክምና የሚሹ ሕፃናትን እርዳታ በማስተባበር እና ልዩ ልዩ ድጋፎችን በማፈላለግ ማሳከሙን ቀጠሉበት። ሂደቱ በእጅጉ አድካሚና ከፍተኛ ጥረትን የሚሻ ነበር። በጊዜው ግለሰቦች ድርጅቶች (አየር መንገድን ጨምሮ) ያስተባብሩ ነበር። ሆኖም ሕፃናቱን ከነቤተሰቦቻቸው ለመላክ አስቸጋሪ በመሆኑ ሌላ ፈተና ይደቅንባቸው ጀመር። ባዕድ ሀገር አንድን ሕፃን ያለቤተሰቡ መላክ ከሚያገኘው ሕክምና ባሻገር ያልተጠበቀ ድብርት ውስጥ የሚከት ነበር።

እርሳቸውም በልጅነት አዕምሯቸው ታካሚዎቹ የሚፈጠርባቸውን የሥነ ልቦና ጫና ለመቀነስ መላ ይፈይዱ ጀመር። ይህ መፍትሔ ዘላቂ መሆን አለበት፤ የችግሩ ሁሉ መፍቻ ሊሆንም የግድ ይላል። እስከዚያው ግን ሕፃናቱን ወደ ውጪ በመላክ ማሳከማቸውን አላቆሙም ነበር። በዚህም እስከ 2001 ዓም ድረስ 2ሺህ 600 ሕፃናት ወደተለያዩ ሀገራት ተጉዘው ሕክምናውን እንዲያገኙ አድርገዋል።



ከዚህ በኋላ ነበር ከፍተኛ ወጪና ውስብስብ ቴክኖሎጂ የሚጠይቀውን የልብ ሕክምና በዚሁ በሀገር ውስጥ እውን ማድረግ ጊዜው መሆኑን ያመኑበት። ለእቅዱ መሳካት ደግሞ እውቀት፣ ገንዘብ እና ሁሉን አቀፍ ቅንጅት ይጠይቃል። በዚህ ወቅት ነበር ‹‹አንድ ብር ለአንድ ልብ›› የሚል ንቅናቄ በዶክተር በላይ አበጋዝ ሀሳብ ጠንሳሽነት በመላው ኢትዮጵያ የተጀመረው።

ይህ ገንዘብ ማሰባሰቢያ ሥርዓት ሆስፒታሉን ለመገንባት እንዲውል ታስቦ የተጀመረ ነበር። ሂደቱ ከፍተኛ መነሳሳትን ፈጠረ። በውጤቱ በነበረው መንግሥት እውቅናን ተቸረው። ባለሀብቶችም እጃቸውን ዘረጉ። የዶክተር በላይ ለበርካታ አስርተ ዓመታት ሲለፉበት የነበረው ሕልማቸውን እውን የሚያደርጉበት ጊዜ ደረሰ። እዚህ ጋር ነበር የሼህ መሐመድ አላሙዲን ታላቅ ውለታ የሚነሳው።

ሼህ መሐሙድ አላሙዲን በጊዜው የዶክተር በላይ አበጋዝ ራዕይ ገዛቸው። ለዓላማቸው እውን መሆን የድርሻቸውን ሊወጡ ወሰኑ። በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ውስጥ ለማዕከሉ በመንግሥት በተሰጠው ቦታ ላይ 100 ሚሊዮን ብር በሚፈጅ ወጪ ለልብ ታማሚ ሕፃናት በነፃ ሕክምና የሚሰጥ ማዕከል ተገነባ። ዘላቂነቱ እንዲቀጥል ደግሞ በብሥራተ ገብርኤል አካባቢ ማዕከሉ የሚያስተዳድራቸው ሕንፃዎች ተገነቡ ።

‹‹ኢትዮጵያ ተመልሰህ የልብ ሆስፒታል በሌለበት፣ መሣሪያ በሌለበት፣ ባለሙያ በሌለበት፣ እንዴት ነው የልብ ሕክምና እሠራለሁ የምትለው?›› የሚለው የዶክተር በላይ መምህር ጥያቄ መልስ አገኘ። ባለራዕይው የሀሳባቸው ተገዢ መሆናቸውን አስመሰከሩ። እቅዳቸውን ለማሳካት ዓመታት ቢፈጅባቸውም ተስፋ ሳይቆርጡ በኢትዮጵያውያን ቀናነትና በባለሀብቱ ሼህ መሐሙድ አላሙዲን ከፍተኛ አስተዋፅዖ ሆስፒታሉን ገነቡት።

ዘመናዊ የልብ ቀዶ ሕክምና መሣሪያዎች “ቼይን ኦፍ ሆፕ ዩኬ” በሚባል ድርጅት ተሟላላቸው። የልብ ቀዶ ሐኪሞች (ካርዲዮሎጂስቶች) ደግሞ የሚኒያፖሊስ የልብ ቀዶ ሐኪም በሆኑት በዶክር ቪ.ብ ክሸንት እና ታዋቂ በሆነው የሕንድ ናርያና ሆስፒታል ሠልጥነው ዝግጁ ሆኑ። ዶክተር በላይ እውቀት፣ ሀብት እና አንድነትን አስተባብረው በሺዎች ለሚቆጠሩ ሕፃናት ደረሱ።

የልብ ሕሙማን ሕፃናት መርጃ ማዕከሉ በ2001 ዓ.ም ምረቃው ተደርጎ በይፋ በአገር ውስጥ የልብ ሕክምና አገልግሎት መስጠት ጀመረ። ዶክተር በላይ ውለታ አይረሱምና የታላቁ ባለሀብት ሼህ አሕሙድ አላሙዲን ከፍ ያለ አስተዋፅዖ የሚዘክር ማስታወሻ አኑረውላቸዋል። ማዕከሉ በአንድ ሰው ራዕይ እዚህ ይድረስ እንጂ ለተግባራዊነቱ በርካቶች የድርሻቸውን ጡብ ማስፈራቸውን ይናገራሉ።

ለዚህም ነው ምስጋና ከአፋቸው የማይጠፋው። በተለይ ዶክተር በላይ ማዕከሉ ተቋማዊ መልክ እንዲይዝ የቦርድ አባላትንና ሥራ አስፈፃሚ በማዋቀር ለ16 ዓመታት እንዲመራ ዘላቂ የገቢ ምንጭ እንዲኖረው ተግተው ሠርተዋል። በሂደቱም በርካቶች ለዚህ በጎ ዓላማ ተሰልፈዋል። አሁንም ድረስ አርቲስት መሠረት መብራቱን ጨምሮ በርካታ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች የዚህ ራዕይ ተጋሪ ሆነው ይገኛሉ።

### በጎነት በዚህ ልክ ለምን?

በዶክተር በላይ የማዕከሉ ጽሕፈት ቤት ውስጥ ‹‹ጨለማን ከመርገም አንድም ሻማ ቢሆን መለኮስ ይሻላል›› የሚል አባባል ተሰቅሎ ይገኛል። አሁን እርሳቸው በጡረታ ጊዜ ላይ ቢሆኑም ይህ ጥቅስ ግን ከግድግዳው ላይ አልተነሳም። ማዕከሉን ተረክቦ የሚያስተዳድረው አዲሱ ትውልድ ተቋሙን ለማስቀጠል በሚያስችሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሲወያይ በዚህ ቢሮ ይሰበሰባል። ይህ አጋጣሚ የእርሳቸው ራዕይ ከተቻለ በተሻለ መልኩ ለማስቀጠል አሊያም ባለበት ሳይንገዳገድ እንዲቆይ ብርታትን ለአመራሮቹ የሚሰጥ ነው። እርሳቸውም ቢሆን ይህንን ምክር ለግሰው ነው በጡረታ ከማዕከሉ በክብር የተሰናበቱት።

‹‹በእውነት ሰው የምንሆነው ለሌሎች ማሰብ የጀመርን ቀን ነው›› የሚል አባባል አላቸው የእርሳቸው የመኖር ፍልስፍና በዚህ ጥብቅ የበጎነት እሳቤ ላይ የተመሠረተ ነው። ራዕያቸው ከራሳቸው አልፎ በሌሎች ላይ የመጋባት ኃይል አለው። ኢትዮጵያዊ ፍቅር፣ ሩህሩህነት ያላብሳል። በእርሳቸው እሳቤ ሰው ሆኖ አንድም የማይጠቅም የለም። ተፅዕኗችን ምንም ያህል ጥቂት ቢመስለንም ለውጥ በበጎነት ላይ ከተሳተፍን ለውጥ ማምጣት እንደምንችል በተደጋጋሚ ሲመክሩ ተደምጠዋል።

እሳቸው ከ1970 ዓ.ም ጀምሮ ተግተው መሬት እንዲነካና ወጤታማ እንዲሆን ያደረጉት የሕፃናት የልብ ሕሙማን መርጃ ማዕከል አሁንም የዚህኛውን ትውልድ ጥብቅ ክትትልና ድጋፍ ይሻል። ማዕከሉ ተገንብቶ፣ መሣሪያዎች ተሟልተውለት ሥራ ቢጀምርም አሁንም ድረስ በአላቂ ዕቃዎች ምክንያት በሙሉ አቅም የሚፈለገውን ግልጋሎት አለመስጠቱ እንደ ምክንያትነት ይነሳል። ዛሬም በጎ ልብ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ለማዕከሉ እርዳታ በማሰባሰብ አምባሳደር በመሆን እየተጉ ቢገኙም በቂ ግን አይደለም። በኢትዮጵያ የልብ ሕክምና የማግኘት አጋጣሚው ፍፁም ቀላል እስኪሆን ድረስ መሥራትን ይጠየቃል። ዶክተር በላይም ራዕዩን ሁሉም ይጋራው ሲሉ በተደጋጋሚ ጥሪ አቅርበዋል።

ዶክተር በላይ በኢትዮጵያ ሕክምና ዘርፍ ላይ የገዘፈ አሻራን ማኖር ችለዋል። እርሳቸው ግን ከዚህም ያለፈ ራዕይ አላቸው። የልብ ሕሙማን ሕፃናት መርጃ ማዕከሉን ከመመስረታቸው ባሻገር እውቀትና ጉልበታቸውን ለልዩ ልዩ ትርጉም ያላቸው ተቋማት ሳይሰስቱ ሰጥተዋል። የሕጻናት ሕክምናን በማስተማር፣ ስለ ሙያውም ልዩ ልዩ ጥናታዊ ጽሑፎችን በማሳተምም ይታወቃሉ።

በዚህ ሳያበቁ ከ1981 ዓ.ም ጀምሮ የአሜሪካ ፔዲያትሪክስ አካዳሚ፣ የኢንተርናሽናል ሶሳይቲ ኦፍ ሃይፐርቴንሽን ኢን ብላክስ፣ ፓን አፍሪካን ሶሳይቶ ኦፍ ካርዲዮሎጂ እና የ ዘ ናሽናል ድራግ አድቫይዘሪ ቦርድ ኦፍ ኢትዮጵያ አባል ሆነው አገልግለዋል። የኢትዮያን ሜዲካል ጆርናል በአባልነት፣ በረዳት ዋና ጸሐፊነት እና በሊቀ መንበርነት አገልግለዋል።

በሀገር በቤተሰብ ጠንካራ እምነት ያላቸው እኚህ ታላቅ የኢትዮጵያውያን ባለውለታ ከባለቤታቸው ሲስተር ሐና በላይ 1965 ትዳር መሥርተው ሁለት ወንድ ልጆችን አፍርተዋል። ልጆቻቸው የእርሳቸውንና የባለቤታቸውን የሙያ ፈለግ የተከተሉ ናቸው።

### የሕይወት ዘመን አበርክቶ

የዶክተር በላይ የሕይወት ዘመን ስኬቶች እንዲሁ በአጭር ጽሑፍ ተዘርዝሮ የሚያበቃ አይደለም። ይሁን እንጂ ተፅዕኗቸው በእያንዳንዱ ኢትዮጵያውያን ደጃፍ የደረሰ ነበር። ለዚህ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ደጋግመው አመስግነዋቸዋል። ለበርካታ አስርተ ዓመታት ሀገራቸውን ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ለሠሩት ሥራ በ2008 ዓ.ም በልብ ሕክምና ዘርፍ ባደረጉት በጎ አስተዋፅዖ ከወሎ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬት ማዕረግ ተቀብለዋል።

በ2006 ዓ.ም የበጎ ሰው ሽልማት ተሸላሚ ነበሩ፤ የልብ ሕሙማን ሕክምና መርጃ ማኅበር ምስረታ 30ኛ ዓመት ሲከበርም ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እጅ የሕይወት ዘመን አገልግሎት ዕውቅና የሜዳሊያ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል። ዶክተር በላይ ከዚህም ያለፈ ለትውልዱ ማስተማሪያ የሚሆን ማስታወሻዎች ሊኖራቸው እንደሚገባ የዝግጅት ክፍላችን ያምናል።

የእርሳቸው የሕይወት ዘመን ሥራዎች በሙዚየም ውስጥ ሊቀመጡ ይገባል። ይህ መሆኑ በጎነት በመጪው ኢትዮጵያውያን ዘንድ ጉልህ ስፍራ እንዲኖረው ያስችላል። በዘመናቸው ታላላቅ ውለታዎችን ለሀገራቸው ሠርተው ያለፉ ኢትዮጵያውያን የሚዘክርና ሥራዎቻቸውን በመሰነድ በሙዚየምነት የሚያስቀምጥ ተቋምም ያስፈልጋል።

### ማዕከሉ ዛሬ

የዶክተር በላይ ራዕይ የወለደው የልብ ሕሙማን ሕፃናት መርጃ ማዕከል ዛሬ 10 ሺህ ለሚደርሱ ሕፃናት እፎይታን ሰጥቷል። ዛሬም ድረስ በማዕከሉ ወረፋ የያዙ ሕክምናን የሚሹ ሕፃናት ይገኛሉ። በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ 7 ሺህ የሚደርሱ ሕፃናት ይገኛሉ። የማዕከሉ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዶክተር ኅሩይ ዓሊ ማዕከሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ የልብ ሕሙማን በአቅም ውስንነት መድረስ አይችልም ይላሉ። ሁሉም ኢትዮጵያውያን ከተረባረቡ ግን የመሥራቹን ራዕይ እውን ማድረግ ይቻላል ይላሉ።

ማዕከሉ የዶክተር በላይ አበጋዝ ራዕይ የወለደውን ተቋም ለማስቀጠል የተለያዩ ስልቶችን ነድፎ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ከዚህ ውስጥ አንዱ የገቢ ማሰባሰቢያ ንቅናቄዎችን ማካሄድ ነው። በዚህ በያዝነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የገና ፆም ወቅት እስከ በዓሉ ድረስ የሚቆይ የርዳታ ማሰባሰቢያ መርሐ ግብር ይፋ አድርጓል። የተለያዩ ዘላቂ የገቢ ማሰባሰቢያዎችም መንገዶችንም ለመፍጠር እየሠራ ነው። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ኢትዮ ቴሌኮም ይህንን ንቅናቄ የተቀላቀሉ ኢትዮጵያዊ ታላላቅ ተቋማት መካከል ቀዳሚዎቹ ናቸው።

# የሀዋሳ ከተማን የቱሪስት ፍሰት በእጥፍ መጨመር የሚያስችሉ ፕሮጀክቶች

ኃይሉ ሣህለድንግል

የከተማዋ ትልቁና የቱሪስቶቿ አይኖች ማረፊያ ሐይቋ ነው። ስያሜዋን ያገኘችውም ከዚሁ ከሐይቋ ሲሆን፣ በሐይቁ ዳርቻዎች የሚገኙና የሚከናወኑ የተለያዩ ተግባሮችም ሌሎች መገለጫዎቿ ናቸው።

አዎን ሀዋሳ ከተማን አለ ሀዋሳ ሐይቅ ማንሳት አይቻልም፤ የዓሣ ገበያዋ፣ የጉዱማሌ ፓርክ፣ የፍቅር ሐይቅ፣ ታቦርና አላሙራ ተራሮች ሁሉም የከተማዋ ስም ሲነሳ አብረው የሚነሱ ናቸው። አረንጓዴ ስፍራዎቿ፣ ሰፋፊ ውብ መንገዶቿ፣ ሞቃታማ አየሯ የሀዋሳ ከተማ ስም ሲነሳ አብረው ይነሳሉ።

ከተማዋ ለነዋሪዎቿ፣ ለጎብኚዎቿና እንግዶቿ ተመራጭ ስለመሆኗ ሁሉም የሚመሰክረው ሐቅ ነው። ቱሪስቶች ለሁለት ለሦስት ቀናት መጥተውባት ሳምንት የሚቆዩባት ሲሉ የሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ባሕል ቱሪዝምና ስፖርት መምሪያ ኃላፊ ወይዘሮ መቅደስ ሁሪሶ ተናግረዋል።

ከተማዋ በርካታ በቱሪስቶች ሊጎበኙ የሚችሉ የቱሪዝም ሀብቶች እንዳሏት መምሪያ ኃላፊዋም ጠቅሰው፣ ሐይቁ ብቻ ሳይሆን የሐይቁ ዳር የዓሣ ገበያ በቱሪስት የሚመረጥ ውብ መስሕብ መሆኑን አመልክተዋል፤ ስፍራው በሀገር ውስጥም በውጭ ቱሪስቶችም በእጅጉ እንደሚወደድ፣ ይህን ገበያ ሳይጎበኝ ወደመጣበት የሚመለስ ጎብኚ እንደሌለም ይገልጻሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ሌላው የከተማዋ ውበት በዚሁ ገበያ አካባቢ የሚገኘው የጉዱማሌ ፓርክ ነው። ይህ በሲዳማ ልማት ማኅበር የሚተዳደርና የሲዳማ ብሔረሰብ በየዓመቱ የሚያከብረው የዘመን መለወጫ የፍቼ ጨምበላላ በዓል የሚከበርበት ስፍራ፣ ቀድሞ አሞራ ገደል በመባል ይታወቅ ነበር፤ በማኅበሩ አማካይነት ከቀድሞው በተሻለ መልኩ አዳዲስ ነገሮች ተካተውበት እየተሠራ ይገኛል፤ በዚህም የቱሪስቶችን ቀልብ ይበልጥ እየሳበ ያለ ስፍራ መሆን እየቻለ ነው። እነዚህ በሙሉ የሀዋሳ ስም ሲነሳ አብረው የሚነሱ የከተማዋ የቱሪስት መስሕቦች ናቸው።

የታቦር ተራራ ሌላው የከተማዋ ውበት ስለመሆኑ የማያውቅ የለም። ተራራ መውጣት ለሚፈልጉ ቱሪስቶች ምቹ ስፍራ ነው የሚሉት ወይዘሮ መቅደስ ፤ይህም ተራራ በኢኮ ቱሪዝምነት እየለማ መሆኑን ጠቅሰው፣ የኢኮ ቱሪዝም ግንባታው ከተጀመረ ቆየት ያለና ሊጠናቀቅ ጥቂት ሥራዎች ብቻ የቀሩት መሆኑን ይገልጻሉ። ግንባታው ተጠናቆ ወደ ሥራ ሲገባ ወደ ከተማዋ የሚመጣውን የቱሪስት ፍሰት ይበልጥ እንደሚጨምረው ይጠበቃል ሲሉም ተናግረዋል።

አላሙራ ተራራም ሌላው የከተማዋ የቱሪስት መስሕብ ነው። በዚህ ተራራ ላይ እስከ አሁን የተለየ ነገር ባይሠራም ወደፊት እንዲለማ በማድረግ ከታቦር ተራራ ጋር በድልድይ የማስተሳሰር ሀሳብ እንዳለም ወይዘሮ መቅደስ ጠቁመዋል።

የአፄ ኃይለሥላሴ የቀድሞ ቤተመንግሥት፣ ጣሊያን በአምስት ዓመቱ ቆይታው ሲጠቅመበት የነበረና ጥሎት የሄደው መድፍ ያለበት ስፍራ፣ ቡርቂቶ ፍል ውሃ፣ የሀዋሳ ሐይቅ መነሻ ተደርጎ የሚታየውና በተለይ በበጋ ወቅት የከብቶች መዋያ በመሆን የሚታወቀው ጨለለቃ ረግረጉ ስፍራ /ሆንሴ/ ሌላው የቱሪስት መስሕብ መሆኑንም ጠቁመዋል። በዚህ ስፍራ ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች ከብቶቻቸውን እንደሚለቁ አስታውቀዋል።

"የሀዋሳ ከተማ ሌላው ትልቁ መስሕብ ነው ብለን የምናስበው የከተማዋ ፀጥታና ደኅንነት ነው" ሲሉ የሚገልጹት የመምሪያ ኃላፊዋ፣ የከተማዋ ሕዝብ "ከፖሊስ ይልቅ የከተማዋ ሠላምና ፀጥታ ጠባቂ፣ በእንግዳ ተቀባይነቱ በእጅጉ የሚታወቅ፣ ዳኤቡሹ ብሎ እንግዶቹን የሚቀበል» ሲሉም ገልጸውታል።

ከተማዋ ከውጭም ይሁን ከሀገር ውስጥ ወደ ከተማዋ የሚመጡ ጎብኚዎችን የሚቀበሉ ትላልቅ ሆቴሎችና ሪዞርቶች በብዛት ያሉባት መሆኗን የማይመሰክር የለም። ከባቡር ትራንስፖርት በስተቀር በሁሉም የትራንስፖርት አማራጮች ወደ ከተማ መምጣትም ሆነ ከከተማዋ መውጣትም ይቻላል። ለአዲስ አበባና ለተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ያላት ቅርበት የቱሪስቶች ምርጫ ካደረጓት መካከል ይጠቀሳሉ።

ይህች ውብ ከተማ አሁን ደግሞ ለነዋሪዎቿ፣ ለቱሪስቶቿና ለእንግዶቿ ይበልጥ ምቹ በሚያደርጋት የኮሪደር ልማት ላይ ትገኛለች። የኮሪደር ልማቱ ዘመኑን የምትመጥን ከተማ እንድትሆን የሚያስችሏትን ሌሎች ትሩፋቶችን ይዞላት እንደመጣም ወይዘሮ መቅደስ አስታውቀዋል።

በከተማዋ እየተካሄደ የሚገኘው የኮሪደር ልማት ከተማዋን የበለጠ ውብ እንድትሆን የሚያደርግ ስለመሆኑ ገና ከአሁኑ በስፋት እንደሚታይ የመምሪያ ኃላፊዋ ጠቁመዋል። በሀዋሳ ሐይቅ ላይ ቀደም ሲል የሚከናወኑ ሥራዎች እንዳሉ ሆነው በኮሪደር ልማቱ ሌሎች አዳዲስ ሰፋፊ ሀሳቦች ተይዘው ወደ ትግበራ ተገብቷል። በዚህም ሐይቁ በራሱ የቱሪስት መስሕብ መሆኑ እንዳለ ሆኖ የበለጠ ቱሪስቶችን እንዲስብ ለማድረግ እየተሠራ ይገኛል ሲሉም አብራርተዋል።

በኮሪደር ልማቱ ከሚካሄዱት ግንባታዎች መካከል አንዱ መነሻውን ከአዲስ አበባ ሀዋሳ መግቢያ በር ወይም ሀዋሳ ጌት ከሚለው ጥቁር ውሃ አካባቢ አንስቶ ወደ መሐል ሀዋሳ የሚወስደውን ነባር መንገድ አድርጎ ፍቅር ሐይቅ አካባቢ ወይም ሻፌታ ታወር /ሀዋሳ ማዘጋጃ ቤት አደባባይ በሚል ይጠራ የነበረው አደባባይ/ የሚዘልቀው ነው። ይህን በጣሊያን ጊዜ እንደተሠራ የሚነገርለትን ጠባብ መንገድ በኮሪደር ልማቱ የማስፋትና የማዘመን ሥራ መጀመሩን ተናግረዋል።

ወይዘሮ መቅደስ እንዳብራሩት፤ ግንባታውን ለማከናወን የሚያስፈልገው የወሰን ማስከበር ሥራ በዚህ ሳምንት ተጠናቆ፣ ግንባታውን ከሚያካሂደው ተቋራጭ ጋር ሰሞኑን ውል ተፈርሞ ሥራው ተጀምሯል፤ ለግንባታው ሁለት ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር የተመደበለት ሲሆን፣ በአምስት ወራት ውስጥ ግንባታውን ለማጠናቀቅ ታቅዷል።

በዚህ ግንባታም የተለያዩ ፕሮጀክቶች ተካተውበታል። በአንድ ጊዜ ስምንት መኪናዎችን የሚያስተላልፍ ተደርጎ የሚገነባ ሲሆን፣ በሁለቱም አቅጣጫዎች አምስት አምስት ሜትር ስፋት ያላቸው የእግር መንገዶች፣ በየመሐሉ የስፖርት ማዘወተሪያዎች፣ የሕጻናት መጫወቻ ስፍራዎች፣ አረንጓዴ ስፍራዎች፣ ወዘተ እንዲኖሩት ተደርጎ ይገነባል።

ሁለተኛው የኮሪደር ልማት የሚካሄድበት ስፍራ ፍቅር ሐይቅ አካባቢ መሆኑን የመምሪያ ኃላፊዋ ጠቅሰው፣ ለዚህም ሐይቁን በሚጠብቅ መልኩ ትልቅ ፕሮጀክት ተዘጋጅቷል፤ የሳይክል መንገድና ሌሎች ቱሪዝሙን ሊያሳድጉ የሚችሉ መሠረተ ልማቶች ለመገንባት ታስቧል ብለዋል።

ከሀዋሳ በር እስከ ፍቅር ሐይቅ ያለው ፕሮጀክት ከተጠናቀቀ በኋላ ወደ ሌሎች ግንባታዎች እንደሚገባ ጠቅሰው፣ አሁን የተያዘው አቅጣጫ ፕሮጀክት መጀመር ብቻ ሳይሆን ጨርሶ ማሳየት እንደመሆኑ የተያዘውን በማጠናቀቅ ወደ ቀጣዩ ምዕራፍ ይገባል ሲሉ አብራርተዋል። ሁሉም ግን እንዲያያዙ እንደሚደረግ ገልጸዋል።

ሌላው የኮሪደር ልማቱ ሲካሄድበት የቆየው አካባቢ ከሜምቦ አደባባይ እስከ ሪፈራል ሆስፒታል ያለው መንገድ ነው፤ የዚህ ግንባታ እየተጠናቀቀ መሆኑንና አካባቢውን ይበልጥ ውብ ማድረግ ማስቻሉን ገልጸዋል።

ወይዘሮ መቅደስ ወደፊት የኮሪደር ልማት የሚካሄድበትን የከተማዋን መሐል አካባቢም ጠቁመዋል። ይህ ሚሊኒየም አደባባይ አካባቢ /ገብርኤል ቤተክርስቲያን አካባቢ/ የሚገኙ ነባር ግንባታዎችን በሙሉ በማንሳት የሚካሄድ ፕሮጀክት ሲሆን፣ ለከተማዋ ሕዝብ መተንፈሻ የሚሆኑ አረንጓዴ ስፍራዎች፣ ቤተመጽሐፍት፣ የሕጻናት መጫወቻዎች፣ የአረጋውያን ማረፊያዎች፣ ወተር ፓርኮች ለመገንባት መታሰቡን አመልክተዋል።

በኮሪደር ልማቱ የሚገነቡት መሠረተ ልማቶች ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ሀብታሙም ዝቅተኛ ገቢ ያለውም ሊገለገልባቸው በሚችል መልኩ የሚሠሩ ይሆናሉ። በልማቱ በሚሠሩትና በተሠሩት የውሃ ፓርኮች፣ በሳይክል መንገዶች፣ በሕጻናት መጫወቻዎች ወዘተ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ያለምንም ክፍያ ሊዝናና እንደሚችልም ጠቁመዋል።

የከተማዋ የቱሪስት ፍሰት ከዓመት ዓመት እየጨመረ እንደሚገኝ ወይዘሮ መቅደስ ጠቅሰው፣ በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት 106 ሺ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች እንዲሁም 12 ሺ 250 የውጭ ቱሪስቶች ከተማዋን መጎብኘታቸውንም ተናግረዋል። የሦስት ወሩ እቅድ የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች 102 ሺ እንደነበረ ጠቅሰው፣ አፈጻጸሙ ከእቅድ በላይ መሆኑን አመልክተዋል። የውጭ ቱሪስቶች እቅድ 15ሺ እንደነበርም አስታውሰዋል። እነዚህ የኮሪደር ሥራዎች ተጠናቀው የከተማዋ ውበት ሲጨምር ደግሞ የቱሪስት ፍሰቱ ከዚህ በእጥፍ ሊጨምር እንደሚችል እርግጠኛ ሆኜ እናገራለሁ ሲሉ ተናግረዋል።



**የሦስት ወሩ እቅድ የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች 102 ሺ እንደነበረ ጠቅሰው፤ አፈጻጸሙ ከእቅድ በላይ መሆኑን አመልክተዋል**

የታቦር ተራራ ፕሮጀክት ከተጀመረ ስለመቆየቱና ስለመዘግየቱ፣ ሐይቅ ላይ ሊሠሩ ስለታሰቡ ነገሮች የተጠየቁት የመምሪያ ኃላፊዋ፣ ፕሮጀክቱ መዘግየቱን እሳቸውም አረጋግጠዋል። ምክንያቱ ከኮንትራት እንዲሁም ከዲዛይን ችግር ጋር የተያያዘ መሆኑን ጠቅሰው፣ ለዚህም ማስተካከያ ተደርጎ ከኮሪደር ልማቱ ጋር ተያያዞ እየተሠራ መሆኑን ሊጠናቀቅ የቀረው ሥራ ጥቂት ሥራ ብቻ መሆኑን ገልጸዋል። ግንባታውን ፈጥኖ ለማጠናቀቅ እንደ ከተማ አስተዳደርም እንደ ክልልም ቁርጠኝነቱ እንዳለም አስታውቀዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የሐይቅ ላይ የትራንስፖርቱ አገልግሎቱ በዘመናዊ ጀልባዎች ጭምር እየተካሄደ ነው፤ ከ100 ሰው በላይ የሚጭኑ ባለወለል ጀልባዎች አሉ። ይህ አገልግሎት ብዙዎችን የሚያዝናና እና ሌላ ቦታ የሌለ የሚባል ነው። ሐይቁ የካፌ አገልግሎት በተንሳፋፊ ቤቶች እየተሰጠበት የሚገኝም ነው።

በኮሪደር ልማቱ ደግሞ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች ይሠራሉ ተብሎ ታስቧል። ፕሮጀክቶቹ ወደፊት ይፋ የሚደረጉ ሲሆኑ የሳይክል መንገድ፣ የንባብ ቤቶች፣ ቢች በአሸዋ ላይ የሚሠራ ፕሮጀክትም ይኖራል፤ እንዲኖር ይደረጋል።

የሀዋሳ ከተማ ወደ ሐይቁ ማዶ እየተስፋፋ መሆኑንም ወይዘሮ መቅደስ ጠቅሰው፣ ሪዞርቶች፣ ሎጆችና ሆቴሎች ተገንብተው ወደ ሥራ መግባታቸውን ተናግረዋል። እሳቸው እንደተናገሩት፤ ጎብኚዎች ሀዋሳ ማደር ካልፈለጉ 100 ብር ብቻ ከፍለው በጀልባ ወደ እነዚህ አካባቢዎች ተሻግረው ማደር ይችላሉ፤ በዚያው ልክም ማዶ ውለው ለአዳር ተመልሰው መምጣት ይችላሉ።

ከተማዋ ወደፊት የምታድገው በሐይቅ ማዶ አካባቢ እንደመሆኑ ለኢንቨስትመንት የሚያስፈልጉ ቦታዎች እየተሰጡ ናቸው። ሁለቱን የከተማዋን አካባቢዎች ማገናኘት የግድ ነው፤ ይህን የሚያተሳስር የትራንስፖርት አገልግሎት ወደፊት ይኖራል ተብሎ ታስቧል፤ ፕሮጀክቱን ጊዜው ሲደርስ ብናነሳው ይሻላል ሲሉም ወይዘሮ መቅደስ ጠቁመዋል።

በሐይቁ አካባቢም እንዲሁ በቀጣይ የሚካሄዱና ጊዜው ሲደርስ ይፋ የሚደረጉ ፕሮጀክቶች እንዳሉ ጠቅሰው፣ በሐይቁ፣ ጉዱማሌ ፓርክ፣ የዓሣ ገበያ፣ ፍቅር ሐይቅ የቱሪስት አገልግሎቶች እየተሰጡ መሆናቸውን ጠቁመዋል። ዓሣውና ሾርባው፣ የጀልባው መዝናኛው ሀዋሳን ይበልጥ ያስተዋውቃታል፤ ሁሉንም ይበልጥ ለማዘመን በቀጣይ የሚሠራ ይሆናል ሲሉ አመልክተዋል።

ከሁለት ዓመት በፊት የሐይቁን አካባቢ ለመጠበቅ ሲባል ማናቸውም ግንባታዎችና ሥራዎች ከሐይቁ ከአንድ መቶ ሜትር ርቀት ላይ ብቻ መካሄድ እንዳለባቸው የተላለፈውን ውሳኔ ተከትሎ ለቱሪስቶች አገልግሎት ይሰጡ የነበሩ ማኅበራት ከአካባቢው እንዲነሱ ተደርጎ እንደነበር አስታውሰው፣ የሚፈለገው ፕሮጀክት ወደ ሥራ እስኪገባ ድረስ አገልግሎቶቹ እንዲቀጥሉ የሚል ውሳኔ መተላለፉንና ማኅበራት እንደገና ገብተው መሥራት እንዲጀምሩ መደረጉን አስታውቀዋል።

ከተማዋ በብስክሌት ትራንስፖርትና ስፖርት ትታወቃለች፤ ይህን መጠበቅ የሚያስችሉ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን የመምሪያ ኃላፊዋ ጠቁመዋል። ሁሉም የኮሪደር ልማት ሥራዎች ሁሉም የከተማዋ መንገዶች ብስክሌትን ያካተቱ ተደርገው እንደሚገነቡ ጠቅሰው፣ የሜምቦ ሪፈራል እንዲሁም የሀዋሳ ጌት ሻፌታ ታወር የኮሪደር ልማት ፕሮጀክቶች ለብስክሌት መንገድ ትኩረት መስጠታቸውን አስታውቀዋል። የኮሪደር ልማቱ የብስክሌት ስፖርቱ ከፍ እንዲል ያደርጋል ሲሉም ገልጸዋል።

በኮሪደር ልማቱ የተጀመሩ ሥራዎች በጣም አመርቂ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ትላልቅ ፕሮጀክቶች በሦስትና በአራት ወራት እያለቁ ናቸው፤ አራት ዓመት አምስት ዓመት የሚፈጁ ፕሮጀክቶች ነበሩ፣ ተጀምረው የማይጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ነበሩ፤ በአሁኑ ወቅት ግን በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅጣጫ መሠረት ሁሉም ክልሎችና ከተሞች ፕሮጀክቶችን እየጀመሩ እየጨረሱ ናቸው፤ የኛም ከተማ በሦስት ወር ውስጥ አንድ ፕሮጀክት ያስመርቃል፤ ቀጣዩ ደግሞ ተጀምሯል፤ ያ ሲጠናቀቅ ሌላው ይጀመራል ሲሉ አስታውቀዋል። በዚህ አይነት ሁኔታ የከተማዋን የቱሪስት መስሕቦችና መዳረሻዎች እንዲያያዙ ለማድረግ ይሠራል ብለዋል።

በሀዋሳ መግቢያ በር ጥቁር ውሃ አካባቢ የከተማዋ የቱሪስት መረጃ ማዕከል መከፈቱን መምሪያ ኃላፊዋ ጠቁመው፣ በቅርቡ ሥራ እንደሚጀምርም አስታውቀዋል። በዚህም በዌብ ሳይትና በሌሎች ዘመኑን በዋጁ ቴክኖሎጂዎች መስሕቦቻችን እያስተዋወቅን ከሄድን የተሻለ የቱሪስት ፍሰት ይኖራል ብዬ አምናለሁ ሲሉም አስታውቀዋል።

# ሳምንቱን በታሪክ

## ፋሽስቱ የወጣበት የመጨረሻው ውጊያ

**ዋስልኝ አየለ**

ኢትዮጵያ ነፃነትን ለዓለም በማስተማር ደማቅ ታሪክ አላት:: ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ አሸናፊ የሆኑት የዓለም ልዕለ ኃያል የተባሉት አራቱ ሀገራት (አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ እና ሶቪየት ኅብረት) የጣሊያን ቅኝ ግዛት የነበሩት ሀገራት እንዴት ይሁኑ? በሚለው ጉዳይ ላይ ከ10 ዓመታት በላይ ተከራክረዋል:: በእነዚህ ክርክሮችና ውይይቶች ውስጥ፤ ቅኝ ያልተገዛችው ኢትዮጵያ ከኃያላኑ ሀገራት ጋር በአንድ አዳራሽ ተቀምጣ መክራለች:: ሙሉ ታሪኩን «የኤርትራ ጉዳይ» ከሚለው የአምባሳደር ዘውዴ ረታ መጽሐፍ ላይ ማግኘት ይቻላል::

ኢትዮጵያ ለዚህ ክብር የበቃችበት ምክንያት ቅኝ ያልተገዛች ሀገር መሆኗ ነው:: ቅኝ የተገዙ ሀገራትን ልክ እንደ ሕጻን ልጅ ሞግዚት እናድርግላቸው ወይስ ራሳቸውን ችለው መኖር ይችሉ ይሆን? እየተባለ ሲመከር ኢትዮጵያ ግን የይገባኛል ጥያቄ ይዛ (ኤርትራንና ሱማሌን) ከኃያላኑ ጋር አብራ መካሪ ነበረች:: በጀግኖች ልጆቿ ሉዓላዊነቷን ባታስከብር ኖሮ በዚያ ውይይት ላይ መካሪ ሳይሆን «ማንን ሞግዚት እናድርግላት?» እየተባለ የሚመከርባት ትሆን ነበር::

በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን 83 ዓመታት ወደኋላ መለስ ብለን በዚህ ሳምንት ኅዳር 19 ቀን 1934 ዓ.ም ወራሪው የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ኢትዮጵያ ውስጥ የመጨረሻውን ውጊያ አድርጎ የተሸነፈበትን እና የኢትዮጵያ ሙሉ ነፃነትና ሉዓላዊነት መከበሩ የተረጋገጠበትን የታሪክ ክስተቶች እናስታውሳለን:: ከዚያ በፊት እንደተለመደው ሌሎች የዚህ ሳምንት ክስተቶችን በአጭር በአጭሩ እናስታውሳለን::

ከ172 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ኅዳር 19 ቀን 1845 ዓ.ም ደጃዝማች ካሣ ኃይሉ «ዳግማዊ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ» ተብለው ከመንገሣቸው በፊት ከግዛት ባላባቶች ጋር ካደረጓቸው ታላላቅ ጦርነቶች መካከል አንዱ የነበረውን የጉር አምባ ጦርነት ከደጃዝማች ጎሹ ዘውዴ ጋር አደረጉ:: ይህ ጦርነት ለአፄ ቴዎድሮስ ወደ ንጉሠ ነገሥትነት መምጣት እና ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ ወሳኙ ጦርነት ነበር:: በዚህ ጦርነት ላይ የደጃች ጎሹ ጦር ለማሸነፍ ተቃርቦ ነበርና አንድ አዝማሪ ለደጃች ጎሹ አድሮ እንዲህ አለ::

**ያንዣብባል እንጂ መች ይዋጋል ካሣ**
**ወርደህ ጥመድበት ከሸንብራው ማሳ**

ወዲያውኑ የደጃች ካሣ (አፄ ቴዎድሮስ) ጦር አሸነፈ:: ያ አድርባይ አዝማሪ አቋሙን ቀይሮ እንዲህ አለ::

**አወይ የአምላክ ቁጣ**
**አወይ የእግዜር ቁጣ**
**አፍ ወዳጁን ያማል የሚሠራው ሲያጣ**
**ዱሳ ይገባዋል የአዝማሪ ቀልማጣ**

ይህ አዝማሪ አፄ ቴዎድሮስን ለማስደሰት ብሎ አቋሙን ቀይሮ ንጉሡን ቢያወድስም፤ አፄ ቴዎድሮስ ግን «እንዲህ አይነት አድር ባይ ሰው አልወድም» ብለው እንዳስገደሉት በታሪክ ተጽፏል::

ከ50 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ኅዳር 19 ቀን 1967 ዓ.ም ብርጋዴር ጄኔራል ተፈሪ ባንቲ የደርግ ሊቀመንበር ሆነው ተመረጡ::

ከ164 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ኅዳር 21 ቀን 1853 ዓ.ም የታሪክ ጸሐፊ፣ ተርጓሚ፣ ደራሲ፣ የቅኔ ሊቅ፣ የሃይማኖት መምህር የነበሩት እና በኢትዮጵያ የሥነ ጽሑፍ ታሪክ ውስጥ ስማቸው ጎላ ብሎ የሚጠቀሱት አለቃ ታዬ ገብረማርያም ተወለዱ::

ከ114 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ኅዳር 22 ቀን 1903 ዓ.ም በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ዘመናዊ መድኃኒት ቤት (ፋርማሲ) ተቋቋመ::

ከ30 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ልክ በዛሬዋ ቀን ኅዳር 22 ቀን 1987 ዓ.ም ደራሲ፣ የሥነ ጽሑፍ መምህር፣ ገጣሚ እና የተውኔት ጠቢብ የነበረው ዳኛቸው ወርቁ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ:: በተለይም «አደፍርስ» በሚለው መጽሐፉ በብዙዎች ዘንድ የሚታወቀው ዳኛቸው ወርቁ፤ የመጽሐፉ የቋንቋ ረቂቅነት፣ የሀሳብ ጥልቀት እና የሥነ ጽሑፍ ቅርጽ የሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎችን ሲያነጋግር ቆይቷል:: አደፍርስ በሥነ ጽሑፍ ቅርጽ የቃለ ትውኔት ቅርጽ እንዳለውም ይነገራል:: ደራሲ ዳኛቸው ወርቁን «የሥነ ጽሑፍ አብዮተኛው» በሚል ርዕስ ከዚህ በፊት ሳምንቱን በታሪክ በዝርዝር መሥራታችን ይታወሳል::



**በዝርዝር ወደምናየው ሳምንቱን በታሪክ እንሂድ::**

ወራሪው የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ኢትዮጵያ ውስጥ የመጨረሻውን ውጊያ አድርጎ የተሸነፈውና ኢትዮጵያ ሙሉ ነፃነትና ሉዓላዊነቷን ያረጋገጠችው ከ83 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ኅዳር 19 ቀን 1934 ዓ.ም ነበር:: ይህ ወቅት ጣሊያን በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከጀርመን ጋር ተባብራ ባደረገችው ውጊያም የተሸነፈችበት ነበር::

ወደ ኢትዮጵያ ታሪክ ስንመጣ፤ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም አዲስ አበባ ገብተው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ቢውለበለብና የፋሺስት ጦር መሸነፉ ይፋ ቢሆንም፤ ጦሩ ከአንዳንድ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ጨርሶ አልወጣም ነበር:: በዚሁ ሳምንት ኅዳር 18 ቀን 1934 ዓ.ም የፋሺስቱ ጦር የመጨረሻ ይዞታው የነበረችውን ጎንደርን ለማስለቀቅ ኢትዮጵያውያን አርበኞች ከእንግሊዝ ጦር ጋር በጋራ በመሆን ውጊያ ከፈቱ:: በዕለቱ የአካባቢው የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር መሪ የነበረው ጀኔራል ናዚ የኢትዮጵያውያን አርበኞችና የእንግሊዝ ወታደሮች የጋራ ጥቃት ጥንካሬው ተስፋ ስላስቆረጠው ከአደባባይ ኢየሱስ ወደ መድኃኔዓለም ሄዶ ነጭ ጨርቅ አውለበለበ:: ምርኮ የመረከብ ሥራ ተጀምሮ ነበርና፤ አርበኛውም ሁሉ ጉራያ ማስጫ ከሚባለው ቦታ ከግንቡ ስር አደረ::

በምሥራቅ በኩል የተሰለፈው የኢትዮጵያ ጦር ግን ወደ ጎንደር ለመግባት ሲሞክር ተቀብሮ የነበረው የፋሺስት ጣሊያን ጦር ቦምብ ፈንድቶ ጉዳት አደረሰበት፤ እርምጃውንም አዘገየበት:: በማግስቱ ኅዳር 19 ቀን 1934 ዓ.ም ራስ ብሩ ወልደገብርኤል ከእንግሊዛዊው ሜጀር ጄኔራል ፎክስ ጋር ወደ ጎንደር ገቡ:: «ባለህበት እርጋ» ተባለና ሁሉም ተረጋጋ:: ጄኔራል ናዚ ያለድርድር እጁን ሰጠ:: የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በፋሲለደስ ግንብ ላይ ተውለበለበ።

በማግሥቱ ኅዳር 20 ቀን 1934 ዓ.ም ልዑል አልጋወራሽ አስፋወሰን ኃይለሥላሴ ጎንደር ገቡ:: የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር በኢትዮጵያ የነበረው ቆይታም በዚሁ ተደመደመ:: በጎንደሩ ውጊያ የጣሊያን ሽንፈት የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር በአፍሪካ ምድር ያካሄደው የመጨረሻው ውጊያና የተከናነበው የመጨረሻው ሽንፈት ሆኖም ተመዘገበ::

አራት ኪሎ የሚገኘው የአርበኞች ድል መታሰቢያ (የድል ሐውልት) አፄ ኃይለሥላሴ ከእንግሊዝ ተመልሰው አዲስ አበባ የገቡበት ቀን ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ነው ተብሎ በታሪክ መዝገብ ላይ ቢሰፍርም፤ ኢትዮጵያ ከፋሺስቶች ሙሉ በሙሉ የተላቀቀችበት ቀን ኅዳር 19 ቀን 1934 ዓ.ም ነው፤ በዚሁ ዕለት ጄኔራል ናሲ የተባለው የፋሺስት ጦር መሪ ከነሠራዊቱ እጁን ሰጥቶ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በፋሲለደስ ግንብ ላይ ተውለበለበ። በነገራችን ላይ በደርግ ዘመነ መንግሥት ጊዜ የአርበኞች ቀን የሚከበረው ሚያዚያ 27 ቀን አልነበረም:: ደርግ የንጉሡ ነገሥቱን ታሪክ መቀየር እንደሚፈልግ ግልጽ ቢሆንም ሚያዝያ 27ም ቢሆን ግን ታሪካዊ ቀን ነው::

በወቅቱ ይታተም የነበረ «ባንዲራችን» የተሰኘ ጋዜጣ በ1ኛ ዓመት ቁጥር 39 የካቲት 18 ቀን 1934 ዓ.ም ዕትሙ፤ ከፋሽስት ጣሊያን ጋር ለመጨረሻ ጊዜ ስለተደረገው የጎንደሩ ጦርነት የሚከተለውን መረጃ አትሟል::

ብዙ ሽንፈት የተከናነበው ሞሶሎኒ የጠቅላይ ጦር አዛዥነቱን ሥልጣን ለጀኔራል ናዚ ሰጠው። ናዚ የቀረውን አርባ ሺህ የሚሆነውን የጣሊያን ጦር አሰባስቦ የመጨረሻውን ፍልሚያ ለማድረግ ጎንደር ላይ መሽጎ መጭውን ጊዜ በጭንቀት ይጠባበቃል።

በደጃዝማች ሀብተሥላሴ በላይነህ የሚመራው አምስት ዓመት ሙሉ ጠላትን መግቢያ መውጫ ያሳጣው የሸዋ አርበኛ አምባላጌ ላይ ዱከ ዳውስታን ማርኮ በየቦታው የመሸገውን የጠላት ጦር እየደመሰሰ በተለይም ጠላት መቼም አይደፈሩም ብሎ የመሸገባቸውን ወልከፊት፣ ፍርቃ በር እና ቁልቋል በር የተባሉትን የጠላት ምሽጎች ሰባብሮ ጎንደር ደርሶ ለመጨረሻ ጊዜ ፋሽስቱን የጣሊያን ጦር ለመቅበር ዝግጅቱን ጨርሷል። በጄኔራል ፎክስ የሚታዘዘው የእንግሊዝ ጦርም በአየር፣ በመካናይዝድ እና በእግረኛ ጦር ተዘጋጅቶ የመጨረሻውን ትዕዛዝ ይጠባበቃል:: በመጨረሻም የጎንደር ከተማ በየአቅጣጫው ተከበበች::

የጎንደር ከተማ ከተከበበች በኋላ ኅዳር 18 ቀን 1934 ዓ.ም ከጠዋቱ 12፡00 ሰዓት ጦርነቱ ተጀመረ:: የእንግሊዝ እና የጠላት መድፎች ሰማይና ምድሩን ያናውጡት ጀመር:: የእንግሊዝ የጦር አውሮፕላኖችም ከዳባት በመነሳት የናዚን የጦር ሰፈር በቦንብ ይቀጠቅጡት ጀመር።

በደጃዝማች ሀብተሥላሴ የሚመራው በደቡብ ጎንደር ሰፍሮ የነበረው አርበኛ ሌሊቱን ተጉዞ አድሮ ወደ ምሽጉ ተጠግቶ ስለነበር በፈንጂ ላይ እየተረማመደ የጣሊያኑን የጄኔራል ማርቲንን ሠራዊት ሰብሮ ቀድሞ ጎንደር ገብቶ የጠላትን ጦር ያርበደብደው ጀመር:: በጄኔራል ፎክስ የሚታዘዘው የእንግሊዝ መካናይዝድ ጦር የአዘዞን ግንባር ጥሶ ገባ:: በምሥራቅ በኩል የነበሩት አርበኞችና የእንግሊዝ ወገን የሆኑት የኬንያ ወታደሮች ደፈጫ የነበረውን የጠላት ጦር በጥንካሬ ወግተው አስለቅቀው ወደ ጎንደር ለመግባት ሲሞክሩ በተጠመደ ፈንጂ ከባድ ጉዳት ደረሰባቸው።

የእንግሊዝ ጦርም ከሰዓት በኋላ ወደ ስምንት ሰዓት ተኩል ሲሆን ወደ ፋሲል ግንብ ተጠጋ:: በዚህ ጊዜም ጀኔራል ናዚ በተጠባባቂነት ያስቀመጠውን የመጨረሻውን ጦር ቢልክም ውጤት ሳያመጣለት ቀረ። ከትንሽ ጊዜም በኋላ ጄኔራል ናዚ ከተደበቀበት «ካዲ ኢጣሊያ» ከሚባለው ቤት አስተርጓሚ ሆነው ሲያገለግሉት ከነበሩት ከፊታውራሪ አስፍሓ ወልሚካኤል ጋር በመሆን እጁን ሰጠ።

ከዚህ በኋላ ሠራዊቱ እንዲረጋጋ የተማረኩና የተበተኑት የጠላት ወታደሮችም እንዲሰበሰቡ በተማረኩ የጠላት ወታድሮች ላይም አርበኞች ምንም ጉዳት እንዳያደርሱ የማረኳቸውን እንዲያስረክቡ የሚል ትዕዛዝ በመተላለፉ አርበኞች የማርኳቸውን የጠላት ወታደሮች እያመጡ ያስረክቡ ጀመር።

በዚህ ጦርነት አራት ሺህ የጣሊያን ወታደሮች ሲገደሉ፣ ስምንት ሺህ አራት መቶ የቆሰሉ ሲሆን፤ ሃያ ሰባት ሺህ ተማርከዋል:: ጄኔራል ናዚም የጦር ወንጀለኛ ሆኖ በእስር ወደ ኬንያ ተላከ።

በዚህ ጦርነት ከጠላት የተማረከውን ከባድና ቀላል የጦር መሣሪያ መድፍ፣ ታንክ፣ እና ከባድ የጦር ተሽከርካሪ አንድም ሳያስቀሩ እንግሊዞች በሱዳንና በኤርትራ በኩል አግዘው ወስደዋቸዋል።

ከድሉ በኋላ ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ የሚከተለውን የደስታ መግለጫ መልዕክት ጎንደር ለሚገኙት አርበኞች አስተላለፉ::

«በዚህ በታላቅ ደስታ ምልክት በሚታይበት ቀን በሰንደቅ ዓላማችን ዙሪያ ተሰብስባችሁ በአየር ሲውለበለብ የምትመለከቱት አርበኞች ዓይኖቻችሁ ከኢትዮጵያ አየር ተለይቶ በማያውቀው ቀለም የተጌጠውን የነፃነት ምልክት ለማየት ሲወረወሩ ልባችሁ የሚሰማውን የደስታ ወለልታ መላ በጌምድር እንደሚሰማው ለኛም ይሰማናል። በዚህች ሰዓት በተወደደ ልጃችን አማካኝነት ስንናገራችሁ በመካከላችሁ እንዳለን ቁጠሩት። በአለፉት ዓመቶች የደረሰውን ፈተና ድል አድራጊ ለመሆንና በጎንደር ከተማ በዛሬው ቀን ይህን ለማየት ስትችሉ መሪር መንገድ አልፋችሁ ወደዚህ ቦታ ለመድረስ የበቃችሁ አርበኞቻችን በጦር ሜዳ የተመሰገኑ ጀግኖቻችንን እሬሳና አፅም ተራምዳችሁ ነው። ይህም ዛሬ የምታዩት ሰንደቅ ዓላማ በነዚያ ደምና በእናንተ ገበሬነት በለሰለሰ መሬት ላይ በቅሎና ለምልሞ ያደገ የነፃነት ሕይወት ዛፍ ነው። የአለፉት መታሰቢያና የኛና በሕይወት የተረፋችሁት ድካም አልጠፋምና እኛን ደስ እንዳለን እናንተም ደስ ይበላችሁ:: ይህ በወገኖቻችን ደም የበቀለው የሰንደቅ ዓላማ ዛፍ የዘለዓለም የሕይወት ዛፍ እንዲሆን ያለፉት በመስዋዕትነት የደከሙትን ያህል በሕይወት የቀረነው ወደፊትም የሚመጣው ትውልድ በአስፈለገ ጊዜ በመስዋዕት የሚሰጥበት የቃል ኪዳን ምልክት ነው»

ከዚህ በኋላ ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋወሰን ጎንደር መጥተው ስለነበር፤ እርሳቸውን ተቀብለው ከእርሳቸው ጋር ሀገር ሲያረጋጉ ከቆዩ በኋላ ደጃዝማች ኃብተሥላሴ ከነሠራዊታቸው ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው የካቲት 16 ቀን 1934 ዓ.ም በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከፍተኛ የጦር ሰልፍና ሥነ ሥርዓት አቀባበል ተደርጎላቸዋል:: በጊዜው በቦታው ተገኝቶ የነበረው «ባንዲራችን» የተባለው ጋዜጣ ሥነ ሥርዓቱን በምልከታ ሐተታ ዘግቦታል::

በአጠቃላይ፤ ኢትዮጵያ በዓድዋ ጦርነት ያሳየችውን የጀግንነት ድል በድጋሚ አስመስክራለች:: ከ40 ዓመታት ዝግጅት በኋላ ቂሙን ለመወጣት የመጣው የጣሊያን ወራሪ በድጋሚ ሽንፈት ተከናንቦ ተመልሷል:: ኢትዮጵያም ሉዓላዊነቷን በማስከበሯ በዓለም አቀፍ መድረኮችና ማኅበራት ላይ ከአድራጊ ፈጣሪዎች ጋር ተሳታፊ ለመሆን በቅታለች:: ክብር ለጀግኖች አርበኞቻችን!

# የዝነኞች ገጽ

## ቀለም ኮርኳሪዋ ልዕልት



**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ስለዚህች እንስት ብዙ አድንቄ ጥቂት እንድጽፍላት ሆንኩ። ብዙዎቹ ተግተልትለው ከሀሳቤ ድቅን ቢሉ ጊዜ ተራ በተራ እያመላለስኩ ደጋግሜ አሰብኩ። ግን ያለ ተራዋ ሁሉ ብቅ ጥልቅ እያለች ምናቤን መኮርኮሯን የተያያዘችውን አንዷቷን ጥበባዊት ለመገላገል ግን አልሆንልህ አለኝ። ግራም የለሹ የሀሳብ ሚዛን እየሄደ ከሷው ምስል ጋር ቢላተምብኝ ከሁሉም መርጬ በታሪኳ ሰገነት ላይ ላኖራት ወደድኩ። እርሷን አሳዶ ስለሌላው መጻፍም ነውር ሆኖ ታየኝ።

ከኔ ቃላት በላይ የእርሷ ቀለማት ትንትን አድርገው ይናገሩላታል። በዚህች የጥበብ ልዕልት በውበቷ ቀለማቱ ራሳቸው የሚደመሙ ይመስለኛል። አፈጣጠሯና ፈጠራዋ ሁሉ ልዩ ነው። ቀለማቱን በብሩሽ እየኮረኮረች አንዴ ፈገግ፣ ሌላ ጊዜም ጭፍግግ፣ ደግሞ ወገግ ስታደርጋቸው ያሰበችውን ቀርቶ የሚያስቡትንም ቁልጭ አድርገው ይናገሩታል። ቀለማቱን እየኮረኮሩ ማናገር፣ አናግሮም ጥበብና ውበትን ማዋሓድ ሥራዋ ነው።

በጥበቧ የፈጠረቻቸውን ስዕሎች እየተመለከቱ መደመምና መደሰት፣ በትዝታ መውረድና በሀሳብ መውጣት የኛ ሥራ ነው። ይህች የምትሾር የጥበብ እንዝርት ለዚህ ሁሉ የምታበቃን ኀበዝ ሰዓሊ በመሆኗ ብቻ አይደለም። ከዘመን ቀድማ ለስዕል የደረሰች ሊቅ በመሆኗም ጭምር ነው። ታዲያ ቀለሟ መልኳ የሆነላትን፣ ስዕልን ሳናውቅ ሰዓሊ የነበረችን፣ ይህቺን ሴት ከማርታ ነሲቡ ወዲያ ማንስ ሊሆን...

እሳት እሳትን ወለደ። ጅምር ፍጻሜዋን የተመለከተ ሁሉ "ደጃች ነሲቡ እንዴት ያለችውን የሴት እንዝርት ወለዱ!" ማለቱ አይቀርም። ገና ከመነሻዋ የሰው ቁንጮ አድርጎ ፈጠራት። አንዱንም ሳያጎድል ሁሉንም አደላት። ፀባየ ሠናይ ናት። ከውበት ውበት ከጥበብም ጥበብን ሰጣት። ተወልዳ ያደገችው ለኛ የጨለማ ከሚመስለው ዘመን ላይ ቢሆንም ጭለማው ግን አልደረሰባትም። አንድም ያጨለመው ነገር ሴትነት ነበር። በዚያ ዘመን ሴት መሆን ፍርጃው ብዙ ነው።

ማጀት እንጂ ትምህርት አልተፈቀደላትም። በሙያዋ እናቷን የምታኮራ ባልቴት እንጂ ከጥበብ ጋር በፍቅር የምትወድቅ ሴት መሆን ያስነውራታል። ድንገት ብትስት ግን ለቤተዘመዱና ቤተሰቡ ሁሉ ማፈሪያ ተደርጋ መቆጠር ዕጣ ፈንታዋ ነው። ድንገት ጊዜና ቦታውን ብታገኝ እንኳን፤ እርሷም ሀሳቡ አፍታ ውልብ አይልባትም። በጥበብ ፍቅር ምን ዛሩ ቢያንዘረዝራት፣ ምን ጨርቋን አስጥሎ ቢያስመንናት ካልጠፉ ምኞት ሁሉ ሰዓሊነትን የምትናፍቅ አይመስልም። በሸለብታ ሕልሟ በጨረፍታም አይታያት። ቢታያት እንኳን ቅዠት ነው ብላ ቸል ብትለው ነው። አድርጋው ብቅ ብትልም ዳገቱ ላይ የቆመው ኮርኳሚ ብዙ ነው።

ከአንድ ታላቅ ሰው ቤት ግን ያ ሁሉ ሳይሆን ቀረ። ሴት ልጅ ተኩኖ እጇ ማማሰያ እንጂ የስዕል ብሩሽ ለመጨበጥ ባልታደለበት በዚያን ጊዜ ብሩሽ ጨብጣ ቀለማትን የምትኮረኩር ልጅ ተወለደች። ሕልሙ ሁሉ እንደ ራዕይ፣ ጥበብ ሁሉ እንደ ስዕል ሆኖ የተገለጠላት ዘመናይ ጦቢያ ናት። አባት ነሲቡ የወለዱት እሷን ነው። ማርታ ነሲቡ ተብላ ስም ብታስጠራም፤ ያስጠራቻቸውም ስመጥር ነበሩ። ግዳችን ከእሷ ቢሆንም ከስሟ ቀጥሎ ያለውን ስም እንዲሁ በፊደላት ለውሰን በመጠሪያነት ብቻ ብናስመልጠው አጥንታቸው እሾህ ይሆንብናል።

ከቡርነታቸው ከንቲባ ነበሩ። ደጃዝማችነት ተጎናጽፈው ኋላም "ራስ" ተብለዋል። መታወቂያቸው ግን በደጃዝማችነቱ ነውና ከንቲባ ነሲቡ ዘ አማኑኤል በሹመት ወንበር ላይ ሳይሟሟቁ ሀገሬን ብለው ወደ ጦር ግንባርም ገስግሰው እንደ ጆፌ አሞራ ወርደዋል ከማለታችን ምን አሉ እንበልና የታሪክ ሊቁ ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ በመጽሐፋቸው "ከኢትዮጵያ ቀዳሚ ምሑራን መካከል አንዱ ናቸው" ይሉና የሞትን ጥቁር ዝናብ አውርዶ የአዲስ አበባን ምድር አኬልዳማ ካደረገው የሰላቶው ሩዶልፍ ግራዚያኒ ጦር ጋር በደገሐቡር፣ በኦጋዴንና በጅግጅጋ በሐረር የጦር አውድማ ላይ የተዋደቁ ስለመሆናቸው ይናገራሉ። ኋላም ጃንሆይ ወደ እንግሊዝ ምድር ሲያቀኑ አብረዋቸው ተጉዘዋል። መጓዝ ብቻም ሳይሆን ለሊግ ኦፍ ኔሽን እዝጎ! ለማለት ከተሰናዱ ሰነዶች መካከል ሁለቱን ያረቀቁትም እኚሁ ደጃዝማች ነሲቡ ዘ አማኑኤል ናቸው። ዳሩ ምን ያደርጋል ፋሽስቱ በእልክ ጥርሱን ነክሶ ባርከፈከፈው የጋዝ መርዝ ሳቢያ ጎኔን ለአልጋ አልሰጥም ብለው ከሕመማቸው ጋር ሲታገሉም በ1936 ዓ.ም በሕመሙ ተሸነፉና በዓመቱ ሞት ነጠቃቸው።



ሰዓሊ ማርታ ነሲቡ

የአባት ታሪክና ገድል ቢያፍሱት የማይጎድል ነውና ስለወለዳት ጀግና ልጁ እናውጋ። እሳት አመድ እንዳይሆን እሳት እሳቷን ወለደ። በ1923 ዓ.ም ማርታ ነሲቡ ተወለደች። ገና ከልጅነቷ አንስቶ ልዕልት ነበረች። እጅግ ውብና ፅዓዳ አድርጎ ፈጣሪ ባለው ሁሉ የተጠበባት የምታስብል ሰንፔር መሳይ ነች። የትልቅ ሰው ልጅ እንደመሆኗ በጊዜ ወደ አስኳላው ስለመግባቷ አይጠየቅም። አስኳላውንም መሰሎቿና ሌላውም የነበረበት በመሆኑ በዚያ የሚለያት የለም። ነገር ግን ማርታ ነሲቡ ገና የ14 ዓመት ታዳጊ ሆና የስዕል ሥራዎቿን ለማስመለከት የቻለች ናት። እዚህ ጋር መደነቅም መጠየቅም። ግን ይደነቁ ይሆናል እንጂ ቢጠይቁ ምላሹ ከብዙዎች የተሰወረ ሆኗል።

ማርታ ከዚያ ዕድሜዋ በፊት ከሀገር አልወጣችም። ስለ ስዕልም ገና ለማንም በሰፊው በጉልህ ያልተገለጠበት ጊዜ ነው። ጥቂቶች በግል ጥረትና በጣት የሚቆጠሩት ደግሞ ከውጭ ተምረው መጥተው የሚፍጨረጨሩበት ቢሆንም በሀገራችን ውስጥ ስለ ስዕል የሚያስተምር አልነበረም። ይህቺ አስማተኛ ታዳጊ ግን ስዕልን አውቃና ችላው ቁጭ ብላ ነበር። ታዲያ ይህን ጥበብ ከየትስ አምጥታ? ከማንስ ተማረችው?

በታዳጊነቷ ገና ከእቃ እቃ ጨዋታ ሳትሸኛኝ ከስዕል ጋር በፍቅር እፍ ብላ ነበር። በዚያው ሰሞን ግን የእርሷንና ቤተሰቧን ብቻም ሳይሆን የመላው ኢትዮጵያን ጀንበር የበጠበጠ ነገር ተከስቷል። ፋሽስቱ የኢጣሊያ ወታደር የጦር መንጋውን በትኖ ሀገር ቀውጢ ላይ ነበረች። ለመጀመሪያው ሽንፈቱ ማስተዛዘኛ እንዲሆነው በበቀል እሳት ነዶ ሰውነቱን ሁሉ አስረስቶት ነበርና ከኢትዮጵያ ሰማይ ላይ የመርዝ ጋዙን ማርከፍከፍ ተያያዘው። ሁሉም ነገር ከአቅም በላይ እየሆነ ለአርበኛው ከፋና ፋሽስቱ ሾልኮ የሚፈልጋቸውን ሁሉ እያደነ ገሚሱን በምርኮ ወደ ሀገሩ መስደድ ጀመረ። ታዲያ ቤተ መንግሥቱ አካባቢ የነበሩት ዋነኛው ዒላማዎቹ ነበሩና ከተጋዙት የደጃዝማች ነሲቡ ዘ አማኑኤል ቤተሰብ ጋር በምርኮ ተወሰደች።

ፈቃድ አልባ በሆነ ስደት ላይ ግዞት ታክሎበት እጅግ የከፋው ነገር ነው። ማርታ ኢጣሊያ ከደረሰች በኋላ የጠበቃት አበባ ሳይሆን እስር ነበር። ለዓመታትም ከእስር ቤት ውስጥ ከርማለች። ኋላ ከጃንሆይ የእንግሊዝ ምልሰትና የሀገር ነፃነት በኋላ ለእርሷም ከእስራት ነፃ መውጣት ነበር። ወደ እናት ሀገሯ እቅፍ መመለሷ አልቀረም።

ከዚህ ቀጥሎ በነበራት የሀገር ውስጥ ቆይታዋም ተሰጥዖዋን በማበርታት ነበር። ስዕል መሳል፣ ግጥሞችና የተለያዩ ጽሑፎችን መጻፍ ገሚስ የሕይወቷ ክፍል ነበር። ከእነዚህ እንቅስቃሴዎቿ ሌላ በርካታ ጉዳዮችንም ትከውናለች። በአንድ ወቅትም ማርታ በትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ ትሠራ ነበር። በጊዜው ስለ ሀገራችን የትምህርት ሁኔታና ከፊደል ጀርባ የቆሙ እልፍ ሕጻናት ጉዳይ ሳያሳስባት አይቀርም። ምናልባትም ከዚህ በመነሳት ይሆናል ለልጆች መማሪያነት የሚያገለግል አንድ መጽሐፍ ጽፋ ነበር። ከዚያው ሳለችም ልዩ ሽልማት ተበርክቶላታል።

የማርታና የምትወዳት እናት ሀገሯ የአብሮነት ቆይታ ያከተመው በ1956 ዓ.ም ገደማ ነበር። ከዚያ በኋላ ያለው ኑሮዋ በውጭ ሀገራት ውስጥ ሆኗል። ባሕርማዶ ከተሻገረች ወዲያ ጥቂት የማይባሉ ሀገራትን ረግጣለች። በዋናነት ኑሮዋን መሥርታ የኖረችው በደቡብ ፈረንሳይ ነው። ከእናት ሀገሯ እቅፍ ብትወጣም ሙቀትና ግለቷ ግን ከዚያም ሆና ይሰማት ነበር። በስንብቱ ዕለት ዓይኖቿ እንባ አዝለው በይ ደህና ሁኚ ሀገሬ ስትል፤ ሀገሯ እንባዋን ጠርጋ በስጦታ የሰጠቻት ያን ከልጅነቷ ጀምሮ የወደደችውን ጥበብ ነበር። ለመንገዷም ሆነ ለሕይወት ዘመኗ ከጥበብ በላይ የሆነ ሌላ ስጦታ አልነበራትም።

ማርታ ነሲቡ በባዕድ ሀገር ሆና የምታስበው ይህንኑ ነበር። የእናት ስጦታዋን ከፍታ በሙሉ ልቧ ለስዕል ጥበብ መኖር ጀመረች። ዕውቀትና ክህሎቷን ለማዳበር ስትል ጎን ለጎን ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ሥልጠናዎችን መውሰዷም አልቀረም። በጄኔቫ፣ በፓሪስ እና በኒውዮርክ በተለያዩ ጊዜያት ለመማር ችላለች። በዘመናዊ የአሳሳል ጥበብ ረቃ ስዕሎቿም በረቂቅ ንድፍ የሚመደቡ ናቸው።

በመማር ሳትገታ፣ በማወቅ ሳትኮፈስ የነበራትን የጥበብ ፍሬ ቆፍራና ዘርታ ያማረ አደረገችው። እየዞረች እንደተማረችው ሁሉ እየዞረች የስዕል ሥራዎቿን ማቅረብም ጀመረች። በዓለም አቀፉ የጥበብና የባሕል ዓውደ ርዕይ ባገኘችው መልካም አጋጣሚ አንድ ጊዜ በሮም በሌላ ጊዜ ደግሞ በቫቲካን ውስጥ የስዕል ሥራዎቿን አቅርባለች። በእስር በተኮራመተችበት ሮም ቀርባ ነፃና ታላቋ የሀገሯ ልጅ መሆንዋን ባይን በግንባራቸው እንዲመለከቱት አድርጋለች። ለፋሽስቱ አድርሺልኝ ብላ የሰጠቻትን የሀገሯን መልዕክት በስዕል አድርሳላታለች። በዚያው ፊታቸው ቆማ "የአፍሪካ የሥነ ጥበብ ክብር"ን ተጎናጽፋለች። ለፋሽስቱ ርዝራዥ የነበራት መልዕክት ይሄ ብቻ አልነበረም።

ማርታ በራሳቸው የኢጣሊያ ቋንቋ መጽሐፍ ጻፈች። ሲተረጎም "የኢትዮጵያዊቷ ልዕልት ትውስታዎች" የሚል ነው። ኢትዮጵያዊ የጻፈው ነገር ለኛ መራራ ለእነርሱ መረቅ ነውና በኩባያ ማንኪያው ሁሉ ጠጡላት። ብዙ ተነበበላትና ተወዳጅነትና ዝነኝነትም አተረፈላት። ስለ ደጃዝማች ነሲቡ ዘ አማኑኤል ልጅ የምናውቀው ብዙ ስለሌ እነርሱ ቢነግሩን መልካም ነበር።

ሰዓሊና ጸሐፊ ማርታ ነሲቡ ከታላላቆቹ የሀገራችን የስዕል ጠበብት መካከል የቱ ጋር ነበረች? በታሪክ ቋት ውስጥ ማርታን ካፈላለግናት፣ እንደ ሀገር ከእንስት ሰዓሊያን በሁለተኛው ቁጥር ላይ ትሰፍራለች። ታላቋን ሴት ቀድመው ታላቅ ሰዓሊ የሆኑ ሌላ አንዲት ሴት ነበሩና። እኚህ ሰዓሊም ነብሳቸውን ለእግዜር አስጨብጠው፣ ሥጋቸውን ለጥበብ ማደሪያ ያደረጉት ወለተ እሥራኤል ስዩም መንገሻ ናቸው። እንደ አጋጣሚው ይሁን እንደ መርጦ ሹዋሚው እኚህ ሴትም ግንዳቸው ዙፋኑ ስር ነው። የአፄ ዮሐንስ የልጅ ልጅና የራስ መንገሻ ሥዩም ልጅ ናቸው። ባሕር ማዶ ተሻግረው፣ ዘመናዊውን ሥነ ስዕል ከፈረንጅ ቀስመው፣ የመጀመሪያዋ ዘመናዊት ሰዓሊም እሳቸው ነበሩ። ሁለተኛዋ ሴት ዘመናይ ደግሞ ማርታ ነሲቡ ነች።

ወንዶቹን አምጥተን ብንቀላቅላቸው፤ ከወለተ እሥራኤል ፊት አፈወርቅ ገብረየሱስ፣ ከማርታ ነሲቡ ፊት ደግሞ አገኘሁ እንግዳ ይቆማሉ። እስክንድር ቦጎሲያን እንዳለም አይዘነጋም። የስዕል ሥራን ቀድሞ ለእይታ በማብቃት ደረጃ ማርታ ነሲቡ ሜትር አርቲስት ሎሬት አፈወርቅ ተክሌንም ትቀድማለች።

አድራሻቸው ማዶ ለማዶ ሆኖ የታላቅነታቸውን የጋራ ማዕድ እንዳሻቸው ለመቁረስ ባይችሉም ሁለቱን ያገናኙ አጋጣሚዎች ግን አልጠፉም። በጊዜው ሎሬቱ ደርበብ ያለ ወጣት ነበር። እሷ ደግሞ ስክትክት ያለች መልከ መልካም ኮረዳ። ሁለቱም በአለባበሳቸው በነጭ የሀገር ባሕል አልባሳት መሽቀርቀርን የሚወዱ ነበሩ። ታዲያ ከዕለታት በአንዱ ቀን ማርታ ዓይን ከማያስነቅለው ውበቷ ጋር እንደልማዷ አምራና አጊጣ ሎሬቱ ፊት ተቀምጣለች። እርሱ ደግሞ ከተወጠረው ሸራ ፊት ቀለሙን ከቀለም እየቀየጠ ፈጣሪ በተጠበበባት ማርታ ላይ በተራው ሊጠበብባት ተሰናዳ። ቀለሙን በብሩሹ እየነከረ ቀና ብሎ በአትኩሮት ያያታል። በቀለም የተነከረውን ብሩሹን ወስዶ ከተወጠረው ሸራ ንድፍ ላይ ያሳርፈዋል። ቆንጆ ልዕልት የመሰለችው ማርታ በሎሬቱ ጥበብ ውስጥ ውበቷ ይበልጥ ፈንጥቆ ወጣ። የእርሱ የውበት ልክ ሆነችና ሰዓሊዋን ሳላት።

ዘመን የቀደመች ዘምናኒት፣ ስለ ጥበብ ሳታውቅ ጥበብ አውቃ የጠራቻት የስዕል ልዕልት ሥራዎቿ የዓለም ቅርስና ውበት ናቸው። ብዕሯን ወደውላታል። የስዕል ብሩሽዋን አድንቀውላታል። በሁለት እግር ቆመው አጨብጭበውላታል። እኛ ዛሬ የምንሰማው የዚህን ጭብጨባ ድምፅ ነው። እሷ ኩሩ ኢትዮጵያዊት ናት። በጥቁር ደሟ ቀለም ምርጡን ስዕል ስላ ለሁሉም አበርክታለች። ዛሬ ላይ የእርሷ ሥራዎች በየሀገራቱ የቅርስ መቅረዝ ላይ ተቀምጠዋል። ኢጣሊያ የማርታ ነሲቡን የጥበብ ጉንጉኖች በመሰብሰብ አንደኛዋ ናት። ለረዥም ጊዜ በኖረችባት ፈረንሳይ ሀገር ውስጥ በክብር ተቀምጠዋል። ሦስተኛዋ ሀገር አሜሪካም የዚህ በረከት ተቋዳሽ ናት። በእናት ሀገሯስ? የለም ቢሉ በጣም አስደንጋጭና አስነዋሪ ይሆን ነበር፤ ግን በብሔራዊ ሙዚየም ውስጥ ይገኛልና ደስ ቢያሰኘን ነው።

ይህቺ የማትደርቅ የቀለም ጠብታ በጋርዮሽ ዘመን ተወልዳና አድጋ በቴክኖሎጂ ከዘመንበት የማኀበራዊ ሚዲያ ጀንበሮቻችን ላይም ደርሳ ተመልክታዋለች። አንዲት ደብዳቤ ልካ ለምላሹ አንድ ወር እንዳልጠበቀች ሁሉ ከእጅ ስልኳ የቴሌ መልዕክት አልፋ በፌስቡክ ለመጻጻፍ በቅታለች። ይህንን ማኀበራዊ ሚዲያ ስትጠቀም የነበረው ትዝታዎቿን ለማጋራት ነበር። በተለያዩ ጊዜያት የሳለቻቸውን ስዕሎች፣ ከልጅነት አንስቶ የነበሯትን ፎቶዎቿን ጨምሮ ሀሳቧንም ታጋራ ነበር። ስሟ በሀገሯ ልጆች ዘንድ መጠራቱና መታወቋም ከዚህ በኋላ ነበር። እርሷም በስተእርጅና ማምሺያው እንኳ አልተገታችም። በውጭ ሀገራት ውስጥ የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት በዋናነትም ሀገርና ባሕሏን የማስተዋወቅ ሥራ ስትሠራ ነበር። በግል ሕይወቷ ከአንጋፋው እንደራሴ እምሩ ዘለቀ ጋር በትዳር ተጣምረው ሦስት ልጆችንም አፍርተዋል።

ታላቋ ሰዓሊ፣ የቀለም እናት ማርታ ነሲቡ ሰው ነችና የሕይወት ጀንበሯ ማቆልቆሉ አልቀረም። ቢሆንም ግን ከጥበብ ጥበብን፣ ከእድሜም እድሜን ጠግባለች። በረዥም የውጭ ሀገር ቆይታዋ ወዲህ ሳትመለስም የ89 ዓመት አዛውንት ሆና 2012 ዓ.ም'ን ደረሰች። ከዚያ ለማለፍ ግን አልቻለችም። በወርሐ መጋቢት ላይ የመጨረሻው የዓለም ስንብቷ ሆነ። ከዚያ የመጀመሪያው ስንብቷ ኋላም ዳግም እናት ሀገሯን አልተገናኘቻትም። ገላዋም ለፈረንሳይ አፈር ሆነ። እሷ ግን ኢትዮጵያዊት ናት። የአባቷ ልጅ፣ የሀገሯ አጫዋች መጅ፣ ጥበቧ በእጅ ነበር።

# ዓለም አቀፍ

## ኤች አይቪ በግብፅ እና በሳዑዲ አረቢያ እየተስፋፋ ነው

በዓለም አቀፍ ደረጃ እያሽቆለቆለ ያለው ኤች አይቪ /ኤድስ በሽታ በአፍጋኒስታን፣ ግብፅ፣ በፊጂ፣ በፊሊፒንስ፣ በፓፕዋ ኒው ጊኒ እና በሳዑዲ አረቢያ በአውሮፓውያኑ 2010 እስከ 2023 ባለው ጊዜ በቫይረሱ የሚያዙ ሰዎች ቁጥር ከ100 ፐርሰንት በላይ ጭማሪ እንዳሳየ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኤች አይቪ/ኤድስ ፕሮግራም (ዩኤንኤድስ) ገልጿል ።

ከአጠቃላይ ሕዝባቸው ጋር ሲነጻጸር እንደ አፍጋኒስታን፣ ግብፅ እና ሳዑዲ አረቢያ ባሉ ሀገራት በኤች አይ የተያዙ ሰዎች በአንጻራዊነት ዝቅተኛ ነው። ግን አሁንም ትኩረት የሚሻ ጉዳይ መሆኑን አሳስቧል፡፡

የሀገራት መሪዎች በተቻለ መጠን የመከላከል አማራጮችን በማስፋት እና ሰዎች የጤና አገልግሎቶችን እንዳያገኙ የሚያደርጉ እንቅፋቶችን የማስወገድ ተግባራት ላይ ማተኮር እንዳለባቸው ተገልጿል፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ በኤች አይቪ የሚያዙ እንዲሁም እያስከተለ ያለው ሞት በከፍተኛ ደረጃ ቢቀንስም የሕዝብ ስጋትነቱን ለማስቆም ዓለም በመንገድ ላይ እንዳልሆነች የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኤች አይቪ/ኤድስ ፕሮግራም (ዩኤንኤድስ) አስጠነቀቀ።

ኢትዮጵያ በኤችአይቪ/ኤድስ የሚያዙ ሰዎችን ቁጥር በመቀነስ ረገድ ባለፉት አስራ አራት ዓመታት ጥሩ እመርታ ካሳዩ የአፍሪካ ሀገራት መካከል የተጠቀሰች ሲሆን፣ ይህም 60 በመቶ መሆኑ



ተገልጿል።

እንደ ዩኤንኤድስ ከሆነ በዓለማችን ላይ 39 ነጥብ 9 ሚሊዮን ሰዎች ኤድስ በደማቸው ያለባቸው ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ ግማሾቹ በደቡብ እና ምሥራቃዊ አፍሪካ ይገኛሉ።

በዓለማችን ላይ በኤችአይቪ የሚያዙ ሰዎች ቁጥር ከአውሮፓውያኑ 2010 ጀምሮ በ39 በመቶ የቀነሰ ሲሆን፣ በኤድስ የሚሞቱትም እንዲሁ በግማሽ ቀንሷል።

ኬንያ፣ ማላዊ፣ ዚምባብዌ እና ኔፓል ኤችአይቪ/ኤድስን ከአውሮፓውያኑ 2010 ጀምሮ በተሳካ ሁኔታ በ75 በመቶ መቀነስ የቻሉ ሀገራት ናቸው።

እስካሁን ባለው መረጃ መሠረት ኤድስን በመዋጋት ረገድ አፍሪካ እንደ አህጉር ቀዳሚውን ቦታ ይዛለች።

ሌሎች 18 ሀገራት ደግሞ ከአውሮፓውያኑ 2010 ጀምሮ በየዓመቱ በኤችአይቪ የሚያዙ ሰዎችን ቁጥር 60 በመቶ መቀነስ ችለዋል።

አብዛኞቹ ከሰሃራ በታች ያሉ ሀገራት ሲሆኑ፤ እነሱም ሌሶቶ፣ ኢስዋቲኒ፣ ቤኒን፣ ኢትዮጵያ፣ ሩዋንዳ፣ ቦትስዋና፣ ኤርትራ፣ ላይቤሪያ፣ ቡርኪናፋሶ፣ ቶጎ፣ ዛምቢያ፣ ቡሩንዲ፣ ጊኒ ቢሳው እንዲሁም ካዛኪስታን፣ ፖርቹጋል፣ ቤላሩስ እና ጣሊያን ናቸው።

ኤች አይቪ በደማቸው ውስጥ ካሉ የዓለማችን ሕዝቦች መካከል 77 በመቶ የፀረ- ኤችአይቪ መድኃኒቶችን ይወስዳሉ። ከሰሃራ በታች ወዳሉ ሀገራት ስንመጣ ደግሞ 82 በመቶ የፀረ ኤችአይቪ መድኃኒቶች እንደሚወስዱ መረጃዎች ያሳያሉ።

የኤችአይቪ ቀውስን ለመግታት በተደረገው ትግል ምክንያት የሰው ልጅ አማካይ ዕድሜን ማሳደግ ተችሏል። በአውሮፓውያኑ 2010 የሰው ልጅ አማካይ እድሜ 56 የነበረ ሲሆን፤ በአውሮፓውያኑ 2013 ወደ 61 አድጓል።

"ዓለም ኤድስን እንደ የሕዝብ ጤና ስጋት የማስወገድ ጎዳና ላይ አይደለም ምክንያቱም በአገልግሎት ተደራሽነት ላይ በተለይም የተገለሉ ማኅበረሰቦችን በማካተት ደረጃ ሰፊ ክፍተቶች ይታያሉ። ኤች አይቪን በመከላከል ረገድ ያለው ቀውስ አሁንም ቀጥሏል" ብለዋል።

በአፍሪካ ያለው የህክምና መስፋፋት በኤች አይቪ የተያዙ ሰዎች ቁጥር በደማቸው ያለው የቫይረስ ጫና መጠን እንዳይጨምር እንዲሁም የመተላለፍ አደጋን እንዲቀንስ ማስቻሉን ዩኤንኤድስ ገልጿል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

## ትክክለኛውን የአትሌቲክስ መሪ ለማግኘት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በዓለም መድረኮች ከመገንባት ባለፈ ለሀገር ያለው ጥቅም ዘርፈ ብዙ ቢሆንም ስፖርቱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተደራራቢ መሰናክሎች ውስጥ ለማለፍ ተገዷል፡፡

የተለመደ ውጤት ያልተመዘገበበትን የፓሪስ እኤአ 2024 ኦሊምፒክን ጨምሮ በሌሎች ውድድሮች ለገጠሙት የውጤት ማሽቆልቆልና ይህንን ተከትሎ ለተነሳው ውዝግብ በርካታ ምክንያቶች ቢቀርቡም አስተዳደራዊ ጉዳዮች ግን ይበልጥ ሚዛን የሚደፉ ይመስላሉ፡፡

ይህንን በፌዴሬሽን ውስጥ የሚታይ አስተዳደራዊ እንከን ፈር በማስያዝ አትሌቲክሱ በትክክለኛው መንገድ እንዲጓዝ የሚያደርግ ሁነኛ አመራር የግድ ይላል፡፡

ይህ አይነቱ የስፖርቱ አመራር ደግሞ ፌዴሬሽኑ በየአራት ዓመቱ በሚያደርገው የፕሬዚዳንትና ስራ አስፈፃሚ አባላት ምርጫ ላይ የጠቅላላ ጉባዔ ድምፅ አግኝቶ ስልጣን መያዝ ይኖርበታል፡፡

እንደሚታወቀው በርካታ ቅሬታዎች እየተነሱበት የስራ ዘመኑን ያገባደደው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ከሳምንታት በኋላ በሚካሄደው 28ኛ መደበኛ ጉባኤው ላይ በአዲስ ይተካል፡፡ ይህም ስፖርቱን ከገባበት የቁልቁለት ጉዞ መንጭቆ የሚያወጣው አዲስ አመራር የሚመጣበት ትክክለኛው ጊዜ ላይ እንደሚገኝ ብዙዎች ተስፋ አድርገውበታል፡፡

አትሌቲክሱን ለመምራት ወደ ኃላፊነት የሚመጣው አዲስ አመራር እንዳለፈው ጊዜ የስፖርት ቤተሰቡን ላለማሳዘን፣ የአትሌቶችን ጥያቄ ለመመለስ እንዲሁም የኢትዮጵያን አትሌቲክስ ወደ ቀደመ ክብሩ ለመመለስ ምን ዓይነት ስትራቴጂ እቅዶችን ይዞ ሊቀርብ ይገባል? ለስፖርቱ ሁነኛ ሰው በመምረጥ ረገድ ትልቅ ዋጋ ያለው ድምፅና ኃላፊነት የተሸከሙት የጉባኤ አባላትስ ምን ይጠበቅባቸዋል? የሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ከወዲሁ አነጋጋሪ ሆነዋል፡፡

የቀድሞው የኢትዮጵያ አትሌቶች ማህበር ፕሬዚዳንት አትሌት ኮሚሽነር ማርቆስ ገነቴ፤ ለኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በስራ አስፈጻሚነት የሚቀርቡ ሰዎች በደንቡ የተቀመጠውን መስፈርት ማሟላታቸው ቀዳሚው ነገር መሆኑን ይናገራል፡፡

ከመስፈርት ባለፈ ግን በፌዴሬሽኑ ውስጥ ያሉና የሚያጋጥሙ ውጣ ውረዶችን ማለፍ የሚችሉ፣ የተጀመሩ ስራዎችን ማስቀጠልና ያልተነኩትን(የአትሌቶች ልማት፣ የህጻናት አትሌቲክስን መሰል ጉዳዮች) ማስጀመርን የመሳሰሉ ብቃቶች ሊኖሯቸው ይገባል ባይ ነው፡፡

ለስራ አስፈጻሚነት የቀረቡት እጩዎች ስፖርቱ በዚህ ዘመን የሚጠይቀውን እውቀትና ክህሎት ማሟላት የሚችሉ መሆን እንዳለባቸው የሚጠቁሙት ደግሞ የስፖርቱ ምሁርና የአትሌቲክስ አሰልጣኙ ብዙአየሁ ታረቀኝ(ዶ/ር) ናቸው፡፡ በአትሌቲክስ ዓለም አቀፍ ስልጠና እስከ ሦስተኛ ደረጃ የደረሱትና የጥሩነሽ ዲባባ የስልጠና ማዕከልን ጨምሮ በበርካታ ክለቦች በአሰልጣኝነት የሰሩት ብዙአየሁ ታረቀኝ(ዶ/ር)፣ አትሌቲክስን መምራት በዚህ ወቅት ትልቅ አቅምን ይጠይቃል ይላሉ፡፡

‹‹የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ተወዳዳሪነቱ በዓለም ላይ ከሚገኙ ጥቂት ምርጥ ፌዴሬሽኖች(ተቋማት) ጋር ነው፡፡ መገንባት ያለበት በእኩል መፎካከር የሚችል ፌዴሬሽን እንደመሆኑ በምርጫው የቀረቡት እጩዎች በዚህ ደረጃ ላይ መገኘት የሚችሉ ናቸው የሚለውን መመዘን አስፈላጊ ነው›› ሲሉም ያስረዳሉ፡፡

እንደ አሰልጣኝ ብዙአየሁ ገለፃ፣ ቀድሞ እንደነበረው ጥቂት ልምድ ብቻውን የስፖርቱ መሪ ሊያደርግ አይችልም፡፡ ይልቁንም አትሌቲክስ እውቀት የሚጠይቅ ሆኗል፡፡ ስለዚህም ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በእኩል መነጋገር የሚችል ባለሙያና ስትራቴጂካዊ እይታ ያለው ሰው የግድ ነው፡፡

ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን የሚቀላቀሉ ሰዎች በቅንነት ከባለሙያዎች ጋር በቅርበት በመስራትና በትምህርት እንዲሁም በልምድ የካበተ እውቀት ያላቸው ባለሙያዎችን ያካተተ ጠንካራ ቴክኒካል ኮሚቴ በማዋቀር የሚፈለገውን ነገር ማሟላት ይችላሉ፡፡ ይህ ካልሆነ ግን በሚቀጥሉት ዓመታትም የአትሌቲክሱ ውጤት ይበልጥ እያሽቆለቆለ የስፖርት ቤተሰቡም እያዘነ መቀጠሉ አይቀርም ብለዋል፡፡

ከፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንትነት በተጨማሪ በስፖርቱ ዕድገትም ይሁን ውድቀት ትልቅ ሚና ያላቸው የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ‹‹ስፖርቱን መምራት ይችላሉ›› ተብለው ለምርጫ ወደ እጩነት የሚያቀርቡት በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ወካይነት ነው፡፡ ስለዚህ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ተገቢውን ሰው በመወከል ረገድ ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ በተመሳሳይ በምርጫው ድምጽ የሚሰጡ የጠቅላላ ጉባኤ አባላትም ለስፖርቱ ለሚበጀው ትክክለኛ ሰው ብቻ ድምፅ የመስጠት ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

ኮሚሽነር ማርቆስ እጩዎችን ከመላክ አስቀድሞ ክልሎች እነማንን መወከል እንዳለባቸው በተገቢ ሁኔታ ማጤን እንዳለባቸው ያስረዳል፡፡ ለስፖርቱ እድገት እነማን በተሻለ ሁኔታ ይሰራሉ የሚለውን መዝነው ካሳወቁ በኋላም ድምጽ የመስጠት ሂደቱ በጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል ይላል፡፡

ስፖርቱን በትክክልና በሃቀኝነት ሊያገለግል የሚችለውን እጩ መለየት የግድ መሆኑንም ያብራራል፡፡ በቅርቡ በኦሊምፒክ የታየው መጥፎ ሁኔታ በአትሌቲክሱ እንዳይደገምም መራጮች የስፖርትን መርህ በመከተል ለአትሌቲክስ እድገት ለሚበጀው አካል ድምጽ መስጠት እንዳለባቸው አሳስቧል፡፡

አሰልጣኝ ብዙአየሁ በበኩላቸው፣ የክልሎች ቀዳሚ ስራ ያቀረቧቸው እጩዎች እነማን ናቸው? የሚለው መሆን አለበት ይላሉ፡፡ አክለውም፣ ለስፖርቱ የሚጠቅም ሃሳብና ራዕይ ያለው እንዲሁም ስፖርቱን ከወደቀበት በማንሳት ከፍ ወዳለ ደረጃ ማድረስ የሚችልን እጩ ስለማቅረብ አስቀድመው መስራት ይገባቸዋል ሲሉ አፅንኦት ሰጥተዋል፡፡ በምርጫው ድምጽ ከመስጠቱ አስቀድሞ ጠቅላላ ጉባኤው የእጩዎችን ሃሳብና ዕቅድ እንዲሰማ ቢደረግ መልካም ይሆናል ብለዋል፡፡

አሰልጣኝ ብዙአየሁ ከሕግ አንጻር ሲታይ በድምጽ አሰጣጡ ላይ መስተካከል የሚገባቸው ጉዳዮች አሉ ብለው ያምናሉ፡፡ በተለይ የጉዳዩ ዋነኛ ተዋናይ የሆኑት አትሌቶችና አሰልጣኞች የሚመራቸውን አካል መምረጥ የሚያስችላቸው የድምጽ ብዛት ሊታሰብበት ይገባ ነበር ይላሉ፡፡ ያም ሆኖ ስፖርቱ ‹‹ባለህበት እርገጥ›› እንዳይሆን በቀጣዩ ምርጫም ቢሆን ተሳታፊ የሚሆኑ አካላት ሊሰራ የሚችለውን እጩ በትኩረት በመለየት ድምጽ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

እጩዎችም ቦታውን ለመያዝ ብቻ ሳይሆን አትሌቲክሱን ለማሳደግ በተቆርቋሪነት ሊሰሩ እንደሚገባ አስቀምጠዋል፡፡

የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር በሀገር አቀፍ የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ለመወሰን ተሻሽሎ የቀረበው መመሪያ፣ ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተመራጭ የሚሆኑ አካላትን መስፈርት ይዘረዝራል፡፡ በዚህም መሰረት ተመራጮች የስፖርት ፍቅር ያላቸው፣ ለሀገርና ለሕዝብ ጥቅም ቅድሚያ የሚሰጡና በጽናት የሚቆሙ፣ ከሙስና የጸዱ እና በስፖርቱ ማህበረሰብ ተቀባይነት ያላቸው ሊሆኑ እንደሚገባ ያመላክታል። ይህም ብቻ ሳይሆን ስፖርቱን በሀብቱ፣ በእውቀቱና በሙያው መደገፍ የሚችሉ እንዲሆኑም ያሳስባል፡፡

# ስፖርት

## አዲሱ ሥራ አስፈፃሚ የአትሌቶችን መብት ለማስከበር ቃል ገባ

ብርሃን ፈይሳ

ስመጥርና ውጤታማ የሆኑ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች የዓለም አቀፍ ውድድሮችን መካሄድ ጨምሮ በተለያዩ ሁኔታዎች የአስቸጋሪ አሠራር ሰለባ በመሆን ቅሬታ ሲያቀርቡ ይስተዋላል። በቅርቡ የተካሄዱ የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮናዎችና ኦሊምፒክ መድረኮች የተፈጠሩ አነጋጋሪ ክስተቶችና ውዝግቦች ለዚህ ምስክር ናቸው፡፡ አትሌቶች ይህን መሰል ሁኔታዎች ሲገጥማቸው ችግሮች እንዲስተካከሉና መፍትሔ እንዲያገኙ የአትሌቶችን መብት ማስከበር እንዲችል የኢትዮጵያ አትሌቶች ማኅበር ቢኖርም ጥርስ የሌለው አንበሳ ሆኖ ይታያል፡፡

ማኅበሩ ለአትሌቶች ችግር መፍትሔ ማምጣት እንዳልቻለ የጠቆመ ሲሆን፣ ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አሠራር እንዲሁም ለዓለም አቀፍ ውድድሮች በብሔራዊ ቡድን አባልነት የሚደረግ ምርጫ ተከትሎ በተደጋጋሚ የአትሌቶች የበደል ድምፅ ሲሰማ ቢቆይም መፍትሔ ማምጣት እንዳልተቻለው የማኅበሩ አባላት ገልፀዋል፡፡

ለአትሌቶች መብት የቆመው ማኅበር ባለፉት ዓመታት የመፍትሔ አካል እንዳልነበር ማኅበሩ 5ኛ ጠቅላላ ጉባኤውን ባካሄደበት ወቅት ተገልጿል፡፡ የማኅበሩ አባላት በተለይም እአአ በ2023ቱ የቡዳፔስት ዓለም ሻምፒዮና እንዲሁም 2024ቱ የፓሪስ ኦሊምፒክ ላይ አትሌቶች ብሶትና በደላቸው እንዲማ ድምፃቸውን ቢያሰሙም በማኅበሩ በኩል የአትሌቶችን መብት ለማስከበር የተደረገ ጥረት እንዳልነበር ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የብሔራዊ ቡድን አትሌቶች መምረጫ መስፈርት ቋሚ እንዲሆን አለመሠራቱ፣ አሠልጣኞች በአትሌቶች ላይ አድሏዊ ተግባራትን ሲፈጽሙ አለመጠየቅ እንዲሁም ከተበዳይ አትሌቶች ጎን በመሆን አቋሙን እንዳላሳየም በተደጋጋሚ ተነስቷል፡፡

በሌላ በኩል አትሌቶች ከፓስፖርት ጋር የተያያዙ እንግልቶችን ለመፍታት ጥረት አለመደረጉ፣ ማኅበሩ ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጋር ተናቦ ከመሥራት አንጻር፣ ከዓለም አቀፍ አቻ ተቋማት ጋር ያለው ግንኙነት፣ የማዘውተሪያ ስፍራዎችና የስፖርት ቁሳቁስ እንዲሟሉ የሚደረገው ጥረት አናሳ መሆናቸውም በጉባኤው አባላት ተጠቁመዋል፡፡



አዲሱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ከቀድሞ አመራር አደራውን ተቀብሉ ሥራውን በኃላፊነት ለመወጣት ቃል ገብቷል፤

የጉባኤተኞችን ጥያቄ ተከትሎ ባለፉት አራት ዓመታት ማኅበሩን በፕሬዚዳንትነት የመራው አትሌት ኮሚሽነር ማርቆስ ገነቴ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ከዓለም አቀፍ ውድድሮች ጋር ተያይዞ አትሌቶች ያቀረቧቸውን ቅሬታዎች ማኅበሩ ለሚመለከታቸው አካላት በቃል፣ በጽሑፍ እንዲሁም በመገናኛ ብዙኃን በኩል ፍትሕ እንዲያገኙ ጥረት ሲያደርግ ነበር፡፡ በአንዳንድ አትሌቶች የቀረቡ ቅሬታዎች ደግሞ በሕግና ደንብ መሠረት አግባብነት የሌላቸው ነበሩ፡፡ ከዚህ ባለፈ የአትሌቶች የውጪ ጉዞን በሚመለከት በርካታ ሥራዎች መከናወናቸውን፣ ማኅበሩን ለማስተዋወቅ የ10 ኪሎ ሜትር የሩጫ ውድድር ማካሄድን ጨምሮ በርካታ ሥራ ሠርቷል፡፡ በማኅበሩ አባላት የተነሱ ሃሳቦች አብዛኞዎች ግብዓት ሲሆኑ ማኅበሩ ባለፉት ዓመታት በዕድሜ ተገቢነት፣ በስፖርት አበረታች ንጥረነገሮች ተጠቃሚነትን በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ አለመሥራቱን አልሸሸገም፡፡

ጠቅላላ ጉባኤው ምርጫ ያካሄደ ሲሆን፤ የሥራ ዘመኑን ባጠናቀቀው የማኅበሩ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴን በአዲስ ተክቷል፡፡ በተካሄደው ምርጫ መሠረትም የትግራይ ክልልን በመወከል በፕሬዚዳንትነት የታጨው አትሌት የማነ ፀጋይ ሊመረጥ ችሏል፡፡ በዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና በተደጋጋሚ ኢትዮጵያን የወከለውና በታላላቅ የማራቶን ውድድሮች ውጤታማ መሆን የቻለው አትሌት የማነ 9 ድምፅ በማግኘትም ነው በከፍተኛ ልዩነት ፕሬዚዳንትነቱን ያረጋገጠው፡፡ አትሌቱ በበርሊን፣ ሞስኮ እና ቤጂንግ ዓለም ሻምፒዮናዎች የብር ሜዳሊያ እንዲሁም ዲፕሎማ ማስገኘት ችሏል፡፡ ለረጅም ጊዜ ስኬታማነት ያሳለፈው በማራቶን ሲሆን፤ በኦቶዋ፣ ጉዋንዡ፣ ሮተርዳም፣ ዴጉ፣ ፎኮካ፣... ማራቶኖች አሸናፊ ነበር። የአትሌቶች ማኅበር ፕሬዚዳንት ሆኖ መመረጡን ተከትሎም የአትሌቶችን መብትና ግዴታ ለማስከበር ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን እንዲሁም ከነባሩ ሥራ አስፈጻሚ ጋር በጋራ ለመሥራት መዘጋጀቱን ገልጿል፡፡

የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ምርጫን ተከትሎም አትሌት ተመስገን ወርቁ፣ አትሌት ባንቺአየሁ ተሰማ፣ አትሌት መርሲት ገብረእግዚአብሄር፣ አትሌት በላይነሽ ኦሊጂራ፣ አትሌት ግርማ ጥላሁን፣ አትሌት በሻንቂ እሙሼ እና ኮከብ ተስፋዬ ተመርጠዋል፡፡


# ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ

## የግልጽ ጨረታ ቁጥር 04/2017

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ የጥሩነሽ ቤጂንግ አጠቃላይ ሆስፒታል በ2017 በጀት ዓመት በተያዘለት የመንግሥት በጀት ለሆስፒታሉ መገልገያ የሚሆኑ የላብራቶሪ የሪኤጀንት ዕቃዎች ግዥ፣ የተሽከርካሪ መለዋወጫ ግዥ፣ የላውንደሪ ማሽን ጥገና ኩሬቲቭ እና ፕሪቬንቲቭ ሜንቴናስ ግዥ ዓመታዊ ውል የሰው መድኃኒትና የህክምና መርጃ መሣሪያ ግዥ የህትመት ሥራዎች ግዥ፣ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሙላት ግዥ ዓመታዊ ውል እና የኬሚካል ርጭት በየ3 ወሩ ግዥ ዓመታዊ ውል በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

**በመሆኑም በጨረታው መሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች፡-**

1. የዘመኑን ግብር ከፍለው በመስኩ የታደሰ ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ መሆናቸውና የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ያላቸው የዋና ምዝገባ ሰርተፍኬት እንዲሁም በአቅራቢነት ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡ ስለመሆናቸው የሚገልጽ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
2. ተጫራቾች ከላይ የተዘረዘሩ የእቃ ወይም አገልግሎት አይነቶች በሙሉ ወይም በከፊል መጫረት የሚችሉ ሲሆን ለእያንዳንዱ ሎት (የጨረታ ሰነድ) የማይመለስ ብር 300.00 (ሦስት መቶ ብር) በመክፈል ጨረታው በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ በሆስፒታሉ ፋይናንንስ ዳይሬክቶሬት ቢሮ ድረስ በአካል በመቅረብ መውሰድ ይችላሉ፡፡
3. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ

3.1 የላብራቶሪ የሬጀንት ዕቃዎች ግዥ ብር 50,000.00 /ሃምሳ ሺህ ብር/

3.2 የተሽከርካሪ መለዋወጫ ግዥ ብር 50,000.00 /ሃምሳ ሺህ ብር/

3.3 የላውንደሪ ማሽን ጥገና ኩሬቲቭ እና ፕሪቬንቲቭ ሜንቴናንስ ግዥ ዓመታዊ ውል 50,000.00/ሃምሳ ሺ. ብር/

3.4 የሰው መድኃኒትና የህክምና መርጃ መሣሪያ ግዥ ብር 30,000.00 / ሰላሣ ሺህ ብር/

3.5 የህትመት ሥራዎች ግዥ 20,000.00 /ሃያ ሺህ ብር/

3.6 የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሙላት ግዥ ዓመታዊ ውል 20,000.00 /ሃያ ሺህ ብር/

3.7 የኬሚካል ርጭት በየ3 ወሩ ግዥ ዓመታዊ ውል 20,000.00 /ሃያ ሺህ ብር/ በባንክ በተረጋገጠ CPO "ለጥሩነሽ ቤጂንግ አጠቃላይ ሆስፒታል" ተብሎ በማዘጋጀት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

4. ተጫራቾች የሚጫረቱበትን ዋጋ በጨረታ ሰነዱ ውስጥ በተዘጋጀው ዋጋ ማቅረቢያ ሰንጠረዥ ላይ ብቻ በመሙላት የድርጅታቸውን ማህተምና ፊርማ አኑረው ፋይናንሽያል እና ቴክኒካል ለእያንዳንዳቸው ኦርጅናልና ኮፒ በማድረግ 4 (አራት ፖስታ) በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ዘወትር በሥራ ቀንና ሰአት ከጠዋቱ 2፡30- 11፡30 ሰዓት ድረስ ለዚሁ ጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡ የጨረታ ሳጥኑ ከታሸገ በኋላ የሚቀርብ የመጫረቻ ሰነድ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
5. ጨረታው በ11ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ተዘግቶ በዛው ዕለት ከጠዋቱ 4፡30 ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በሆስፒታሉ አዳራሽ ውስጥ ይከፈታል፡፡ ተጫራቾች በራሳቸው ፈቃድ ባይገኙ ጨረታው ከመከፈት አያግደውም፡፡ 11ኛው ቀን የሥራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የሥራ ቀን ይከፈታል፡፡
6. ተጫራቾች ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ባቀረቡት የመወዳደሪያ ሃሳብ ላይ ለውጥ ወይም ማሻሻያ ማድረግና ከጨረታው ራሳቸውን ማግለል እንዲሁም ሌላ ተጫራች በሰጠው ዋጋ ላይ ተንተርሶ ዋጋ ማቅረብ አይችሉም፡፡

7 አሸናፊ ተጫራች አሸናፊ የሆነባቸውን እቃዎች ያለምንም አቅርቦት ችግር አስተማማኝ የሆነ የዕቃ ክምችት ያለውና የእቃውን ጠቅላላ ዋጋ 10% ለውል ማስከበሪያነት አስይዞ ተገቢውን ውል በመፈጸም እቃዎቹን በሆስፒታሉ ግቢ ንብረት ክፍል ድረስ በማምጣት ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

8 ሆስፒታሉ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ/ በከፊል/የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**አድራሻ፡-** አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 1 ወይም ልዩ ስሙ ጥምቀተ ባህር ወይም አቃቂ መሿለኪያ ፊት ለፊት

**ለበለጠ መረጃ፡-** ስልክ ቁጥር 0921801144 በሥራ ሰአት መደወል ይቻላል፡፡

## የጥሩነሽ ቤጂንግ አጠቃላይ ሆስፒታል